**DSpace Institution**

**DSpace Repository** | **http://dspace.org**

Ethiopian Languages and Literature - Amharic | Thesis and Dissertations

2024-06

# þÿ è G + ¥ “ è ¥ Í • s Í ï u ` p (! è e s þÿ c x Í 5 + Î }

þÿ u Õ 5 u , L 0

http://ir.bdu.edu.et/handle/123456789/16239

*Downloaded from DSpace Repository, DSpace Institution's institutional repository*

ባህርዳር ዩኒቨርስቲ

ሂዩማኒቲስ ፋኩሊቲ

የኢትዮጵያ ቋንቋ (ዎች)ና ሥነጹሑፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር


# የፈጠራ እና የእውነታ ውህደት በተመረጡ የሀብታሙ አለባቸው ስራዎች

በ


ትዕግስት ፍሰሀ



ሰኔ፣2015

ባህርዳር፣ ኢትዮጵያ

# የፈጠራ እና እውነታ ውህደት በተመረጡ የሀብታሙ አለባቸው ስራዎች

ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት


በ

ትዕግስት ፍሰሀ

አማካሪ

ተስፋዬ ዳኘዉ (ተባባሪ ፕሮፌሰር)



ሰኔ፣2015

ባህርዳር፣ኢትዮጵያ

**ባሕርዳር ዩኒቨርሲቲ**

**ሂዩማኒቲስ ፋኩሊቲ**

**የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል**

## የቴስስ መግለጫ

ይህን ‹‹የፈጠራ እና እውነታ ውህደት በተመረጡ የሀብታሙ አለባቸው ስራዎች›› የተሰኘ የማስተርስ ዲግሪ መመረቂያ ጽሁፍ በደንቡ መሰረት ማማከሬን በማረጋገጥ ለቃል ፈተና እንዲቀርብ ስምምነቴን እገልጻለሁ፡፡

የአማካሪ ስም፡- ተስፋዬ ዳኘው (ተባባሪ ፕሮፌሰር)

ፊርማ፡ -------------

ቀን፡ ------------------

የትምህርት ክፍሉ ሀላፊ ስም ---------- --------------- ፊርማ--------------- ቀን----------

# ባሕርዳር ዩኒቨርሲቲ

## ሂዩማኒቲስ ፋኩሊቲ

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

እኛ ስማችን ከታች የተዘረዘሩት የፈተና ቦርድ አባላት "የፈጠራና የእውነታ ውህደት በተመረጡ የሀብታሙ አለባቸው ስራዎች" የሚለውን መመረቂያ ጽሑፍ ፈትነን፣ የማስተርስ ድግሪ ማሟያ መመረቂያ ጽሑፍ እንዲያሟላ የሚፈለገውን ያሟላ መሆኑን እናረጋግጣለን፡፡

**የፈተና ቦርድ አባላት**

| | | |
|---|---|---|
| **አማካሪ ስም** | **ፊርማ** | **ቀን** |
| ________________ | ________________ | ________________ |
| **የውስጥ ፈታኝ ስም** | **ፊርማ** | **ቀን** |
| ________________ | ________________ | ________________ |
| **የውጪ ፈታኝ ስም** | **ፊርማ** | **ቀን** |
| ________________ | ________________ | ________________ |

# ማረጋገጫ

ይህ ጥናት የእኔ መሆኑንና የተጠቀምሁባቸው ምንጮችንም በአግባቡ መጥቀሴን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም፡-----------------------------------------

ፊርማ፡------------------------------------

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ - አማርኛ - ትምህርት ክፍል የድኅረ ምረቃ መርኃ ግብር

ባሕርዳር ዩኒቨርሲቲ

ሰኔ፣ 2015 ዓ.ም

# ምስጋና

ሁልጊዜ በምህረት የትምኅበኘኝ ስወድቅ አንስተህ እንዳዲስ ነፍስ የምትዘራብኝ ክብር እና ሞገስ የሆንከኝ ቸሩ መድኃኒዓለም ሆይ ተመስገን፡፡ አዛኝቷ ባትመለከቺኝ ኖሮ እንዴት ዛሬ ቆሜ ማመስገን ይቻለኝ ነበር?! እመቤቴ ቅድስት ድንግል ማርያም ሆይ በእኔ ላይ ስለሆነው በምድር ላይ ከሚኖር ሁሉ ቅድሚያ ላንቺ ክብር ምስጋና ይገባል፡፡

በረፈደ ሰዓት ሁሉ ጋሼ እያልኩ ስመጣ ፊትህን ሳታዞርብኝ በትህትና የጥናት ወረቀቴን በማንበብና በፍጥነት አስተያየትህን በመስጠት ለዚህ ላበቃኸኝ አማካሪዬ ተስፋዬ ዳኘው (ተባባሪ ፕሮፌሰር) ምስጋናዬ ይድረስህ፡፡ የመምህር ትርጉም የሆንከው ውድ መምህሬ ጋሽ አንተነህ አወቀ (ተባባሪ ፕሮፌሰር) ምስጋናዬን ብቻ ሳይሆን መውደዴም ጥልቅ ነውና ፈጣሪዬ ረጅም እድሜ ከጤና ጋር ያድልህ፡፡ ቀጥሎ ደግሞ በሃሳብ እና ለጥናቴ ግብዓት የሚሆኑ መጽሐፍቶችን በመስጠትም በመጠቆምም ላገዛችሁኝ ውድ መምህራኖቼ ቴዎድሮስ አለበል፣ ተስፋ ማርያም ገብረ መስቀል(ዶ/ር)፣ ስንታየሁ ገነት(ዶ/ር) እና አየነው ጓዱ(ዶ/ር) ምስጋናዬን ውሰዱ፡፡

አባዬ በቃልህ ቀርጸህ እንደሻማ ቀልጠህ ብርሃን የሆንካት ልጅህ ቃልህን አክብራ ያሰብከውን ሆናለች እና ደስ ይበልህ፡፡ ሞገዱ በዝቶ ከመንገድ እዳይጥለኝ እንደአለት መጠንከርን አንተ ባታስተምረኝ ኖሮ የኔ የደካማዋ ልጅህን እጅ ስትለቅ እንዴት እዚህ መድረስ እችል ነበር?!፡፡ ይሄን ስታነቢ ላባትሽ አደላሽ እንዳትይኝ የኔ እናት ያንቺን ምስጋና እንዴት እረሳለሁ?!ስንፍናዬ ቤት እንዳይሰራብኝ ፣ ትምህርቴን መጨረስ እና አለመጨረሴ እያስጨነቀሽ ከዘመኑ ጋር እንድሄድ ዘመንሽን የሰጠሽኝ ውዷ እናቴ ምስጋናዬን ተቀበይ፡፡ ከቤተሰቡ አንተን ብዘል ምስጋናዬ ሙሉ አይሆንምና ወንድሜ አመሰግናለሁ፡፡ ከአህያ የዋለች ጊደር ፈስ ተምራ ትገባለች እንደሚሉት አበው እሱቤ ደርሼብሃለውና ቶሎ ፒኤችዲህን ጀምር፡፡ ስላደረክልኝ ሁሉ ግን ሳላመሰግንህ አላልፍም፡፡ የሁለተኛ ድግሪ ትምህርቱን ለመጀመር በማገዝ እና እስከ ዛሬዋ ድረስ እየተከታተልክ ለጠየከኝ መባ ተፈራ ባለህበት ምስጋናዬ ይድረስህ፡፡

# ማውጫ

ይዘት ገጽ


ማረጋገጫ _______________ i

ምስጋና _______________ ii

ማውጫ _______________ iii

አጠቃሎ _______________ v

**ምዕራፍ አንድ** _______________ 1

1.1. የጥናቱ ዳራ ---------- 1

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች ---------- 5

1.3. የጥናቱ ዓላማ ---------- 8

1.3.1.የጥናቱ ዓቢይ ዓላማ ---------- 8

1.3.2.የጥናቱዝርዝርዓላማዎች ---------- 8

1.4. ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች ---------- 9

1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ ---------- 9

1.6. የጥናቱ ወሰን ---------- 9

1.7. የጥናቱ ዘዴ ---------- 10

1.7.1.የቴክስትመምረጫመስፈርቶች ---------- 10

1.7.2.የመረጃምንጭእናየመረጃመሰብሰቢዘዴዎች ---------- 11

1.7.3.የመረጃመተንተኛዘዴ ---------- 11

**ምዕራፍ ሁለት** _______________ 13

ንድፈ ሃሳባዊ ዳራና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት _______________ 13

2.1. ንድፈ ሃሳባዊ ዳራ ---------- 13

2.1.1.የእውነታምንነት ---------- 13

2.1.1.1.ማህበራዊእውነታ(Socialistrealism) ---------------------------------------- 17

2.1.2.የፈጠራምንነት------------------------------------------------------------------------ 19

2.1.3.ሀዲስታሪካዊሂስ ------------------------------------------------------------------ 22

2.2. የተዛማጅ ጽሑፍ ቅኝት ------------------------------------------------------------------ 36

2.2.1.ከሀገርውስጥየተፈተሹጥናቶች ---------------------------------------------------------- 36

2.2.2.ከሀገርውጪየተፈተሹጥናቶች----------------------------------------------------------- 39

**ምዕራፍ ሦስት** ______ 41

ትንተና ______ 41

3.1. አህጽሮተ ልብወለድ------------------------------------------------------------------ 41

3.2. ሀዲስ ታሪካዊ ሂስ በቀሳር እንባ እና በየሱፍ አበባ------------------------------------ 42

3.2.1. የፈጠራና የእውነታ ውህደት በቀሳር እንባ እና በየሱፍ አበባ---------------------- 54

3.2.2. የማህበራዊ እውነታ በቀሳር እንባ እና በየሱፍ አበባ-------------------------------- 61

**ምዕራፍ አራት** ______ 64

ማጠቃለያ ______ 64

ዋቢዎች ______ 66

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት “የፈጠራና የእውነታ ውህደት በተመረጡ የሀብታሙ አለባቸው ስራዎች” በሚል ርዕስ የተከናወነ ነው። የጥናቱ ዘዴ ዓይነታዊ የምርምር ስልትን መሰረት ያደረገ ሲሆን መተንተኛው ዘዴው ደግሞ ገላጭ እና ፍካሬ ነው። ጥናቱ በተመረጡት ቴክስቶች ውስጥ የፈጠራና የእውነታ ውህደትከሀዲስ ታሪካዊ ሂስ ንድፈ ሃሳብ አንጻር ቢፈተሽ መልካም ነው በሚል ዕምነት የተደረገ ነው። ጥናቱን ሀዲስ ታሪካዊ ንድፈ ሃሳብን በመጠቀም በልቦለዶች ውስጥ ያለውን ማህበራዊ፣ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያው ጉዳዮች ከአውዱ አንፃር ፈትሿል። የፈጠራ እና የእውነት ውህደት በልቦለድ እና በእውነታ መካከል ያለውን ድንበር እንደሚያፈርስ በትንተናው ለማሳየት የሞከረ ጥናት ነው። የሥነጽሁፍ ሥራ በታሪካዊ እውነታ ላይ ተጽእኖ የማድረግም የመደረግም ሁለቱንም ምርጫዎች የማስተናገድ ሚና አለው እንዳለው በትንተናው ወቅት ለማሳየት ተሞክሯል። ጥናቱ በልቦለዶቹ ውስጥ ፈጠራና የእውነታ ተዋህደው መቅረባቸውን የሚያሳይ ሲሆን በትንተናው ታሪክ ፈጠራና እውነታን አዋህዶ ለማቅረብ ትልቅ ሚና እንዳለው መረዳት ተችሏል። በተጨማሪም በትንተናው የእውነታና ፈጠራ ውህደት አንባቢያን በማይለዩት መልኩ መቅረቡን እና በቁሳር እንባ ላይ በዋና ገጸባህርይነት ለቀረቡት መንግሥቱ ኃ/ማርያም አዲስ እይታን እንደፈጠረ አብራርቷል።

# ምዕራፍ አንድ

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

ሥነጽሑፍ የሰው ሐሳብና ስሜትን በኪነት ኃይል በመግዛት ገዝፎ የሚታይ ከሰው ልጅ ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያለው ጥበብ ነው። የሥነጽሑፍ ምንጭም የሰው ልጅ እውነታ ወይም ሪያሊቲ ነው። እውነታውም በልደትና በሞት መካከል የተዘረጋው ህላዌ ነው። እንዲሁም ሥነጽሑፍ የሰው ልጅ ሃሳብ እና ስሜት ውበት ባለው መልኩ የሚቀርብበት ጥበብ ነው። ስለ ሥነጽሑፍ ዮሐንስ አድማሱ (1961፣1) ሲገልጹ

> "ሥነጽሑፍ ጠቅላላ ዓላማው ማስደሰት ነው። ይህንንም ጉልህ አላማ የሚፈጽመው ሁሉን አቀፍ የሕይወት ኂስ በማቅረብ ነው። ሥነጽሑፍ ጉልህ ዓላማውን ለመፈጸም ጥራትና ወጥነት እንዲኖረው ያስፈልጋል። "በኑጎ ዘመን፥ በቀን ብዛት የማይነቅዝና የማይሻግት" መሆን አለበት። አለበለዚያ አጉል ጉህና ወይም ብስና እንጂ ሥነ ጽሑፍ ሊሆን አይችልም። ሥነ ጽሑፍን ሥነ ጽሑፍ የሚያደርገው የደራሲው የኪነት ኃይል ፥ የማስተዋልና የማንጠር ችሎታ ያስተዋለውንና ያነጠረውን ከሰው ልጅ እውነታ ጋር በቋንቋ ኃይል አገናዝቦና አዋሕዶ" እነሆኝ!"ብሎ የሚያቀርብበት ልዩ ችሎታው ነው። ግልብ ደራሲ ግልብ ተመልካች ነው።ጽሑፉም በዚያው ልክ ግልብ ይችርቻሮ ጽሑፍ ይሆናል" ።

ሥነጽሑፍ ባለብዙ ፈርጅ፣ ባለብዙ ቅርንጫፍና ከአያሌ የዕውቀት ዘርፎች ጋር የሚነካካ የኪነጥበብ ዘርፍ ነው። ቴዎድሮስ (2001፣1) "የሥነጽሑፍ ሁለ-ገብነት፣በይነ-ዲሲፕሊናዊነት ጥንተ ተፈጥሮ አልያም ነባር ባሕርይ ነዉ" በማለት ሥነጽሑፍ የማይገባበት መስክ እንደሌለ ይገልጻሉ። በሥነ-ጽሑፍ ውስጥ እውነታ የገሃዱ ዓለም ርዕሰ ጉዳዮችን ውክልና የሚያመለክት ነው። ይህ አካሄድ በህብረተሰቡ መካከለኛ እና ዝቅተኛ ክፍሎች ላይ ያተኩሩ ተዛማጅ እና ውስብስብ ገጸ-ባህሪያት፣ መቼቶች እና ሴራዎች ላይ በማተኮር እውነታውን በተቻለ መጠን በትክክል ለማሳየት ይሞክራል። ነገር ግን በዚህ ሁኔታ ውስጥ አንድ የፈጠራ ታሪክ ፤ የተለያዩ አፈታሪኮች የተለያዩ ልቦለዶች ይሆናሉ (Lewis፣1978፣39)።

ሥነ ጽሑፍ እንደሙያ መታየት ከጀመረበት ከ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ አዳዲስ ፅንሰ ሃሳቦች፣ ፍልስፍናዎች እና ንድፈ ሃሳቦችን እየፈለቀቀ በየዘመኑ ንድፈ ሃሳቦችን በሚያቀኑ ምሁራን እየታሸ ለአንባቢያን እና ለደራሲያን አዳዲስ ዕይታዎችንና መንገዶችን እየፈጠረ መጥቷል፡፡ በእኛም ሀገር ቢሆን የአማርኛ ልቦለድ መጻፍ ከተጀመረ ብዙ ዓመታትን አስቆጥሯል፡፡ ስለ አማርኛ ልቦለድ አጀማማር Demeke Tassew ( 2014፣1-2 ) እንዲህ ይገልጻሉ፡፡

> Novel writing in Amharic is a century-old practice. There is a consensus among Amharic literary scholars that the novel written under the title Lebb Wälläd Tarik (Fictional Story) by Afawarq Gabrayasus in 1908 is the first Amharic novel to pave the way for the history of modern Amharic literature (Ge'rard, 1971: 5; Molvaer, 1980: 8; Taye, 1995:61; Yonas, 1995:93). Following this novel, a number of novels have been produced in this language. Importantly, present-day writers are also contributing to this history by writing novels that belong to the socio-political and cultural milieu of their time.
>
> "ልቦለድን በአማርኛ መጻፍ የብዙ ዓመታት ልምድ ነው፡፡ በ1908 ዓ.ም *ልብወለድ ታሪክ* በሚል ርዕስ በአፋወርቅ ገ/እየሱስ የተጻፈው ልቦለድ ለዘመናዊ የአማርኛ ሥነ ጽሑፍ ታሪክ መንገድ የሚጠርግ የመጀመሪያው የአማርኛ ልቦለድ እንደሆነ የአማርኛ ሥነ ጽሑፍ ሊቃውንት ይስማማሉ (Ge'rard, 1971: 5; Molvaer, 1980: 8; Taye, 1995:61; Yonas, 1995:93) ፡፡ ከዚህ ልብ ወለድ በኋላ በዚህ ቋንቋ በርካታ ልቦለዶች ተዘጋጅተዋል፡፡ በጣም አስፈላጊው ነገር የዛሬዎቹ ጸሃፊዎች በዘመናቸው ከነበረው ማህበረ-ፖለቲካዊ እና ባህላዊ ምህዳር ጋር የተያያዙ ልቦለዶችን በመጻፍ ለዚህ ታሪክ አስተዋፅዖ እያበረከቱ ነው"፡፡

ከላይ በምንባቡ ላይ የተገለጸው የመጀመሪያውን የአማርኛ ልቦለድ እና ሌሎችም በዛ ዘመን የነበሩ የልቦለድ ስራዎች ከኪናዊ ፋይዳ ይልቅ ማህበረሰቡን ለማስተማር እና መልዕክት ለማስተላለፍ የተጻፉ በመሆናቸው አብዛኞቹ ልቦለዶች ላይ የፈጠራ እና የእውነታ ውህደት

ጎልቶ አይታይባቸውም። ይህንን ሃሳብ (ብሌን፣1982፣20) “ ልቦለዶቹ በምናባዊነት የተሞሉ ከገሀዱ ዓለም በራቁ ታሪኮች የታጨቁ ናቸው። ደራሲው የሚያስበውን ነገር በነሱ ያስተላልፋል እንጂ ከነሱ ባህርይ የወጡ ሁኔታዎችን አያሳይም። በገሀዱ ዓለም ካሉ ሰዎች ጋር ያላቸውን መመሳሰል በምናይበት ጊዜ በጣም ዝቅተኛ ነው” በማለት ይግልጻሉ።

ከ1933-1955 ባለው ዘመን ለስነ ፅሁፍ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረከቱ ደራሲያን ቁጥር የተበራከተበት ወቅት ነዉ። እነዚህም መኮንን እንዳልካቸዉ የደም ዘመን(1945)፣ ግርማቸዉ ተክለሃዋርያት፣ አስፋ ገ/ማርያም እንደወጣች ቀረች (1946)፣ መኮንን ዘውዴ የዓለምሰው እርምጃ (1948)፣ በእምነት ገብረ አምላክ ልጅነት ተመልሶ አይመጣም(1949)፣ ነጋሽ ገብረ ማርያም ሴተኛ አዳሪ ዮፍታሄ ንጉሴ እና ወልደ ጊዮርጊስ ወ/ዮሃንስ እና ሌሎችም ይነሳሉ።

በብዙዎች ዘንድ የመጀመሪያዉ እዉነተኛ ዘመናዊ የአማርኛ ረጅም ልቦለድ ነዉ የሚባለዉ የግርማቸዉ ተክለ ሐዋርያት በ1941 የታተመዉ *አርአያ* የዚህ ዘመን ግኝት ነዉ። በ*አርአያ* ረጅም ልቦለድ ከቀድሞቹ ልቦለዶች በተለየ መልኩ የቀረበ ሲሆን በአቀራረብ ስልቱ፣ በገፀ ባህሪያት አሳሳል፣ በመቼት ገለፃ፣ በቋንቋ አጠቃቀም፣ በአቀራረብ እዉናዊነት እና በሌሎችም ከቀድሞዎቹ የተለየ ነዉ።

ከ1950-1960 ይህ ዘመን ወርቃማ የኢትየጵያ ሥነፅሑፍ ዘመን በመባል የተጠራ ዘመን ነዉ። በስነ ፅሁፋዊ ዉበታቸዉና በቴክንካቸዉ የተሻሉ ልዩ ልዩ የስነ ፅሁፍ ስራዎች በተለያዩ ደራሲያን ቀርበዋል። በአጻጻፍ ቴክኒክ ረገድም እንደ ወረደ ፣ ተዉኔታዊ አቀራረብ ፣ የዘመናዊ ቴክኒክ ወይም ኪን የአፃፃፍ ስልት ጎላ ብሎ መታየት ፣ በንግርና ምልሰት ስራዎችን ማቅረብ፣ ክፍት አጨራረስ ወይም ኦፐን ኢንድንግ የሚባል አጨራረስ ስልት የታየበት ጊዜ ነዉ። የፈጠራ እና የእውነታ ውህደትን ስንመለከት የተሻለ እና የተሞከረበትም ዘመን ነው ማለት እንችላለን።

ከ1967-1983 ይህ ዘመን በአማርኛ ስነ ፅሁፍ በርካታ የትርጉም ስራዎች የተገኙበት ነዉ። በመሆኑም ከእንግሊዘኛ፣ ከፈረንሳይኛ ስነ ፅሁፍ ወደ አማርኛ በኢትዮጵያዊያን በሳህለ ስላሴ ብርሃነ ማርያምና በአማረ ማሞ ተተርጉመዋል። (አንተነህ፣ 173) እንዲሁም ዘመኑ የሶሻሊስት እዉነታዊነት የአፃፃፍ ስልት የተከሰተበት ዘመን በመሆኑ ህዛባዊነት፣ መደባዊነትና የፓርቲ ወገናዊነት የሚሉ መርሆችን መሰረት ያደረጉ ልቦለዶች ተፅፈዋል። በአጠቃላይ የአማርኛ ሥነጽሑፍ ቀስ በቀስ እያደገና በአዳዲስ ቴክኒኮች ብቅ እያለ የመጣ ነው። በልቦለዶቹ ውስጥም

የፈጠራና የእውነታ ውህደትን ስንለመለክት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገና እየጎላ የመጣ ነው። የፈጠራ እና የእውነታ ውህደት ስንል እውነታውና ፈጠራው በልብወለዱ ውስጥ መለየት በሚያዳግት መልኩ አንድ ሆነው ሲቀርቡ ነው። ይህም ማለት ተጨባጭነት የለውም ወይም በገሃዱ ዓለም አልተከሰተም ለማለት ሳይሆን፣ ማንኛውም ዓይነት እውነት በአንድ አካል የምናብ ውጤት የተቀናበረ መሆኑን ለማሳየት ነው (ጸደይ፣2007፣5)። በተጨማሪም ኪናዊ የፈጠራ ኃይል በሁለቱ መካከል ያለውን ድንበር ያሳሳዋል። ምናባዊ ገፀባህርያት ከታሪክ ጋር ተመሳሳይ የሆነ እውነተኛው ማለትም በገሃዱ ዓለም ከሚታወቀው ጋር በትይዩ መግለጫ ይቀርባሉ (Lewis፣1978፣37)።

ጸደይ ወንድሙ (2007፣5) "እውነታ ከድርሰት እኩል ፈጠራ የሚሆነው በገሃዱ ዓለም ውስጥ ያለምንም ብከላ ቁጭ ብሎ ስለማይገኝ፣ በጊዜ ብዛት ሊቀየር ስለሚችል፣ሁሉም እኩል የሚስማማበት ስለማይሆን ነው" ይላሉ። ከዚህ ሃሳብ በመነሳት ሁሉንም የሚያስማማ እውነታ የለም፣እውነታ የጋራ ስምምነት ነው የሚል መደምደሚያ ላይ መድረስ ይቻላል። በዚህ ጥናት የፈጠራና የእውነታ ውህደትን ተንትኖ ለማሳየት ጥቅም ላይ የሚውለው ሀዲስ ታሪካዊ ንድፈ ሃሳብ ነው። እንደ ሀዲስ ታሪካዊ ሂስ ሊቃውንት "ቴክስት" በባህል እና በታሪክ የሚገነባ ነው። ሀዲስ ታሪካዊ ሂስ እንደገና ታሪክን በቴክስት በመጻፍ ለህብረተሰቡ የመተርጎም ፣ የመተንንተን እና የመገምገም ጠቀሜታን ይሰጣል።

Stephen Greenblatt (1989፣24) እንደገለፁት "ሀዲስ ታሪካዊ ሂስ ሥነጽሑፋዊ ንድፈ ሃሳብ እና ሂስ የሆነው በሥነጽሑፋዊ ሥራ በጊዜ፣በቦታ እና በሁኔታዎች ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ነው" ይላሉ። ሀዲስ ታሪካዊ ሂስ አንድን የሥነጽሑፍ ሥራ ከማህበራዊ እና ታሪካዊ አውድ ጋር ያለውን ግንኙነት ለመረዳት የሚያገለግል የጥናት መስክ ነው። በሀዲስ ታሪካዊ ሂስ አተያይ ሁሉንም የሚያስማማ አንድ የሆነ ታሪካዊ እውነት የለም። ታሪክ የትርጉም ጉዳይ እንጂ ፍፁም እውነት አይደለም።

Tyson (2006፣284) እንደገለፁት "በሀዲስ ታሪካዊ ሂስ ድርሰቱ የተመሰረተባቸው መቸቶች፣ ሁኔታዎች... ዙሪያ ያሉ መረጃዎች እኩል ጠቃሚነት ይኖራቸዋል። ምክንያቱም እነዚህ ነገሮች ተደጋጋፊ እና ትርጉም ለማግኘት መሰረታዊ ነጥቦች ናቸው" ይላሉ። ሀዲስ ታሪካዊ ሂስ የሥነጽሁፍ ሥራ በታሪካዊ እውነታ ላይ ተጽእኖ የማድረግም የመደረግም ሁለቱንም ምርጫዎች የማስተናገድ ሚና አለው።

ሀዲስ ታሪካዊ ሂስ ባለፈና አሁን በሚታይ ውስብስብ የባህል፣ የፖለቲካና የድርሰቱ አለም ውስጥ በመግባት እውነታን ማውጣት ነው። ይህ ማለት በአንድ ስራ ታሪካዊ አውድና በዘመናዊ አንባቢ አንብቦ የመረዳትና የመተርጎም መስተጋብር ላይ ትኩረት ያደርጋል። ሥነጽሁፋዊ ቴክስቶች ታሪካዊ አውዶችን እንደሚቀርጹ ሁሉ ታሪኮችም ሥነጽሁፋዊ ቴክስቶችን ይቀርጻሉ፤ የትኛውም ድርስት በታተመበት፣ባህላዊና ፖለቲካዊ አሰራር እንደሚቀረጽ ሁሉ በተራው ዘመንን የመቅረጽ ሀይል አለው ማለት ነው። በተጨማሪም ሀዲስ ታሪካዊ በጸሀፊው ታሪካዊ ሆነ በሀያሲው ታሪክ ውስጥ ሥነጽሑፍ መጠናት እና መተርጎም አለበት በሚል እሳቤ የተመሰረተ ነው። የሥነጽሑፍን ድርሰት በጥልቀት ለመረዳት የታሪክ፣ የፖለቲካ፣ ግለታሪክና መጽሐፎችን ማንበብ ትልቅ ፋይዳ እንዳለው ሁሉ ታሪክንና ፖለቲካን ይበልጥ ለመረዳትም በዘመኑ የተጻፉ ሥነጽሁፎች ከፍተኛ ሚና አላቸው የሚል መርህ አለው።

በዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ የፈጠራ እና የእውነታ ውህደት በተመረጡ የሀብታሙ አለባቸው ስራዎች ላይ ተተንትኖ ቀርቧል። ደራሲ ሀብታሙ አለባቸው *የሱፍ አበባ፣የቄሳር እንባ፣ አውሮራ፣ታላቅ ተቃርኖ፣ሕንፍሽፍሽ፣አንፋሮ፣አስኳላ* የተሰኙ መጽሐፍትን ለንባብ አብቅተዋል። ደራሲው ፖለቲካል ሳይንስ የትምህርት ዘርፍን ያጠኑ ሲሆን በመቀሌ ዩኒቨርስቲ ሲቪክና ኤቲክስን በማስተማር አገልግለዋል። በተጨማሪም በከፍተኛ የመንግሥት መዋቅሮች ላይ በኃላፊነት ደረጃ ፣ የተለያዩ የምርምር ስራዎችን በሀገር ውስጥ እና ከሀገር ውጪ በማቅረብ ሰርተዋል። መጻሕፍቶቹ በጭብጣቸው ይለያዩ እንጂ በዘውግ ተመሳሳይ ናቸው ማለት ይቻላል። ደራሲው ታሪካዊ ክስተቶችን እና በገሀዱ ዓለም የነበሩ ሰዎችን በገፀባህርይነት በመጠቀም ከፈጠራ ጋር ቀላቅሎ በመድረስ የተካነ ነው።

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች

ይህን ጥናት ለማካሄድ ዋነኛው አነሳሽ ምክንያት ለመጀመሪያ ድግሪ ማሟያነት የሰራሁት ጥናት ነው። ጥናቱ "የፈጠራና የእውነታ ውህደት *ከደንቢያ ጎንደር እስከ ዋሽግተን ዲሲ*" በሚል ርዕስ በ2013 ዓ.ም ለመጀመሪያ ድግሪ ሟሟያነት የተሰራ ነው። ያኔ በነበረኝ አካዳሚካዊ እውቀት እና ከጊዜ እጥረት የተነሳ ጥናቱ ከርዕሱ ጋር በሚዛመድ መልኩ አልተሰራም። በዘርፉ በተለይም በርዕሱ ዙሪያ የሁለተኛ ድግሪ ተማሪ ሆኜ ግንዛቤ ስላገኘሁ እና ጥናቱ አዲስ በመሆኑ በዘርፉ ሊያበረክት የሚችለውን አስተዋፅዎ በማሰብ በዚህ ርዕስ ጉዳይ ጥናት

እንዳካሄድ አነሳስቶኛል። አሁን የሚካሄደው ጥናት በሀዲስ ታሪካዊ ሂስ ተብራርቶ የፈጠራ እና የእውነታ ውህደትን ለማሳየት ሞክሯል። እንዲሁም ሌሎች ሰነዶች ጥቅም ላይ በመዋላቸው ለመጀመሪያ ድግሪ ማሟያነት ከተሰራው ጥናት ጋር ከተመሳስሎው ይልቅ ልዩነቱ እጅግ ሰፊ ነው።

ይህን ጥናት ለማካሄድ ሌላው አነሳሽ ምክንያት በዳራው ላይ እንደተገለፀው የሀብታሙ አለባቸው መጻሕፍት እውነታን ከፈጠራ ጋር በማያያዝ ስሜትን በሚይዝ መልኩ የቀረበባቸው ናቸው። እነዚህን ጉዳዮች ደግሞ ሳይንሳዊ መልክ መስጠት ማለትም ሳይንሳዊ ዘዴዎችን (ንድፈ ሃሳቦችን ) እና መርሆዎችን በመጠቀም እነዚህን ጉዳዮች ተጨባጭ አድርጎ መተንተን ሌላው አነሳሽ ምክንያት ነው። ስለ "ፈጠራና እውነታ" ባደረኩት ንባብ በዚህ ርዕስ ጉዳይ ተመሳሳይ ጥናት በሌላ አካል ተካኺዶ ባለመመልከቴ እና ይኼን ክፍተት ደግሞ እንደ ሥነጽሑፍ ተማሪነቴ የመሙላት ኃላፊነት አለብኝ ብዬ ማሰቤ ጥናቱን ለማካሄድ ተጨማሪ ቀስቃሽ ምክንያት ሆኖኛል። እንዲሁም *"የሱፍ አበባ"* እና *"የቁሳር እንባ"* የፈጠራና የእውነታ ውህደት በስፋት የሚታዩበት በመሆኑ መጽሐፉቱ በራሳቸው መጠናታቸው ለሌሎች ጥናቶች በር ይከፈታሉ፤ ለሙግቶች ያነቃሉ የሚለው ሃሳብ ጥናቱን ለማካሄድ ሌላው አነሳሽ ምክንያት ነው።

የእውነታና የፈጠራ ውህደት በአውዱ መሰረት የምናባዊነትን የአስተሳሰብ ሂደቶችን ቢያራምዱም ሁለቱም ግን የተለያየ የፈጠራ ደረጃዎችን ነው የሚያንጸባርቁት። የእውነታ ሰፊውን የማስመሰል ፅንሰ-ሀሳብን የሚያመለክት ሲሆን ፈጠራ ደግሞ በግምታዊ የተሞሉ ክስተቶች ወይም ሁኔታዎች በጠባብ ስሜት ውስጥ ምናባዊነትን መፍጠር ይመለከታል። ይህንን ልዩነት በዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ ለማስረዳት መሞከር በዙሪያችን ያለውን አለም እንዴት እንደምንገነዘብ ጠቃሚ ግንዛቤን ሊሰጥ ይችላል።

በተጨማሪም የሀዲስ ታሪካዊ ንድፈ ሃሳብን በመጠቀም ሀገር ውስጥ የተሰራ ጥናት መመልከት ወይም ማግኘት የቻልኩት በዶክተር አንተነህ አወቀ ዳግም ንባብ በ *አልወለድም* በሚል ርዕስ በ2007 ዓ.ም በባህርዳር ዩኒቨርስቲ የአማርኛ ቋንቋና የባህል ዘርፎች በሶስተኛው አገር አቀፍ ዐውደ ጥናት ላይ ቀርቦ የተሻሻለውን ነው። ይህ ጥናት በደራሲ አቤ ጉበኛ *አልወለድም* ላይ ትኩረቱን ያደረገ ሲሆን ሀዲስ ታሪካዊ ንድፈ ሃሳብን በመጠቀም ትንተናው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቁምታ ላይ በማረፉ ከሚደረገው ጥናት ጋር ተመሳስሎ የለውም። ድህረ ዘመናዊነት በሌሎች ዘርፎች እውነት ናቸው የተባሉትን በመጠራጠር አንፃራዊ እውነት ላይ ትኩረቱን ያደርጋል።

እውነታ የሚፈታው እያንዳንዱ ሰው ስለዓለም ምንነት ባለው ትርጓሜ ልክ ነው። ልክ እንደ ሀዲስ ታሪካዊ ሂስ በድህረ ዘመናዊ እሳቤም ትርጓሜ ሁሉም ነገር ነው። ታሪክ የትርጓሜ ጉዳይ እንጂ ፍፁም እውነት አይደለም የሚለው አባባል የሀዲስ ታሪካዊ ሂስ እና የድህረ ዘመናዊነት ቁልፍ ገጽታ ነው። እነዚህ ሁለቱም የንድፈ ሃሳቦች ተጨባጭ የሆነ ታሪካዊ ግንዛቤን እና የትርጓሜን ሚና ፣ ታሪካዊ ክስተቶችን እና ግንዛቤዎችን በመቅረጽ ላይ ያጎላሉ። ሀዲስ ታሪካዊ ሂስ ፣ በ1980ዎቹ የዳበረ ወሳኝ አካሄድ፣ አንድን ጽሑፍ ከማህበራዊ፣ ባህላዊ እና ታሪካዊ ሁኔታዎች ጋር በትይዩ ማንበብን ያካትታል፣ ይህም 'co-text' በመባል ይታወቃል። ይህ አተያይ አንድ ጽሑፍ ራስ-ሰር ቅርስ ነው የሚለውን ሃሳብ ውድቅ ያደርጋል። ስለዚህም ማንነት በሁሉም ግለሰቦች የሚጋራ ሳይሆን ብዙ ቁጥር እና ድብልቅ መሆኑን ያሳያል ማለት ነው። ድህረ ዘመናዊነት በበኩሉ የፍፁም እውነትን አስተሳሰብ ይቃወማል። ሥነ ጽሑፍ ብዙ ትርጓሜዎች ሊኖሩት እንደሚችሉ እና የትኛውም ዓይነት የሥነ ጽሑፍ ሥራ ዘውግ ሊገለጽ እንደማይችል ይገልፃል። ይህም ማለት አንድ ተጨባጭ የሆነ ትርጓሜ መስጠት አይቻልም። የድህረ ዘመናዊነት ተመራማሪው ዣክ ዴሪዳ በዚህ ጽንሰ-ሀሳብ ላይ በሰፊው ጽፈዋል፣ ሥነ-ጽሑፋዊ ዘውጎች ለብዙ ትርጓሜዎች ክፍት እና የተደራጁ መሆናቸውን ይገልጻሉ።

የድህረ ዘመናዊነትን መገለጫዎች በከፊል በጥናት ዳሰው የተመለከትኩት የነፃነት ማስረሻ (2007) እና የጸደይ ወንድሙ (2005) ጥናት ነው። የነፃነት ማስረሻ ጥናት "የድህረ-ዘመናዊነት የስነ- ጽሁፍ መገለጫዎች በ "የስንብት ቀለማት" በሚል ርዕስ በ 2010 ዓ.ም ባህርዳር ዩኒቨርስቲ ለሁለተኛ ድግሪ ሟሟያነት የተሰራ ጥናታዊ ጽሁፍ ሲሆን ከዚህ ጥናት ጋር የድህረ ዘመናዊነት ንድፈ ሃሳብ በመጠቀም የሚመሳሰል ይሆናል። ከጥናቱ የሚለይበት ምክንያት ይህ ጥናት ድህረ ዘመናዊነት እና ሀዲስ ታሪካዊ ንድፈ ሃሳብን በማያያዝ የፈጠራና የእውነታ ውህደትን ማሳየት ትኩረቱ ሲሆን የነጻነት ጥናት ደግሞ ድህረ ዘመናዊ ንድፈ ሃሳብን ብቻ በመጠቀም በስንብት ቀለማት ላይ የተከሰቱትን የድህረ ዘመናዊ መገለጫዎችን መግለጥ ነው።

የጸደይ ወንድሙ(2005) ጥናት "Space time Realities in Ethiopian post modernist Literature convergence of post modernist Literaty Theory, physics and Mystoicism" በሚል ርዕስ እ.አ.አ. በ2015 ለውጪ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል የዶክትሬት ዲግሪ ለማግኘት የቀረበ ነው። ጸደይ ከደራሲ ስብሀት ገ/እግዚአብሔር ስራዎች መካከል "ከአምስት ስድስት ሰባት" "ተከታትለው ሸው ወደ ቢሾፍቱ" እና "ለገዳዲ" ፣ አጋፋሪ

እንደሻው" እና "ስምንተኛው ጌታ" ፤ ከደራሲ አዳም ረታ ስራዎች መካከልም "ግራጫ ቃጭሎች" እና "እቴሜቴ ሎሚ ሽታ" ፤ ከደራሲ አለማየሁ ገላጋይ "ቅበላ" እንዲሁም ከደራሲ አታሞ ፐልቶ "ኤላን ፍለጋ" ("የአዞ ኮሌጅ") እና "የሲሳይ ልጆች" ("ኬክሮስና ኬንትሮስ") በተሰኙ የልቦለድ *ሥራዎች* ላይ ጥናት አድርገዋል፡፡ ሙሉውን ጥናት ማግኘት ባለመቻሌ ምክንያት የቃኘሁት ከጥናቱ ብሌን፣ገጽ 8፣ ቁጥር 2 (ነሐሴ 2007 ዓ.ም.) ከታተመው እትም "ድህረ- ዘመናዊ የሥነጽሑፍ መገለጫዎች በ*ግራጫ ቃጭሎች* ውስጥ" በሚል ርዕስ የቀረበውን ትንታኔ ነው፡፡ እሱን መሰረት በማድረግ ጥናቱ ከእኔ ጥናት ጋር ከተመሳስሎ ይልቅ ልዩነቱ ሰፊ ነው፡፡

## 1.3. የጥናቱ ዓላማ

ይህ ጥናት ተከታዮቹ ዓቢይ እና ዝርዝር ዓላማዎች አሉት፡፡

### 1.3.1.የጥናቱ ዓቢይ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዓቢይ ዓላማ ፈጠራና እውነታ በተመረጡ የሀብታሙ አለባቸው መጻሕፍት ላይ እንዴት ተዋህደው እንደቀረቡ ተንትኖ ማሳየት ነው፡፡

### 1.3.2.የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች

ይህ ጥናት የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች አሉት፡፡

- ታሪክና ልቦለድ የተዋሃዱባቸውን ፍሬ ነገሮች መለየት፡፡
- በልቦለዶቹ ውስጥ በስፋት የተንፀባረቀው የማህበራዊ እውነታን መግለጥ?
- የፈጠራና የእውነታ ውህደት በስፋት በየትኞቹ ገጸባህርያት ላይ እንደተስተዋለ ማመመልከት፡፡
- በልቦለዶቹ ውስጥ የቀረበው ታሪካዊ እውነታን መግለጥ፡፡

## 1.4. ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች

በዚህ ጥናት ለማሳካት የሚሞከሩ ዋናና ንዑስ አላማዎችን ለማግኘት የቀረቡ የምርምር ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ታሪክና ልቦለድ የተዋሃዱባቸው ፍሬ ነገሮች ምንድናቸው?
- በልቦለዶቹ ውስጥ የማህበራዊ እውነታ እንዴት ቀርቧል?
- ፈጠራና እውነታ በስፋት በየትኞቹ ገጸባህርያት ላይ ተስተውሏል?
- ፈጠራና እውነታ ያላቸው ግንኙነት ምን ይመስላል?
- በልቦለዶቹ ውስጥ ታሪካዊ እውነታ እንዴት ቀረበ?

## 1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ በርካታ ጠቀሜታዎች አሉት፡፡ ከእነሱም ውስጥ የመጀመሪያውና ዋናው ጠቀሜታ ሊሆን የሚችለው በሥነጽሑፍ ቤት ላሉ ተማሪዎች የፈጠራና የእውነታ ውህደትን ማብራራት፤ ምንነታቸውንም በማስረዳት ግንዛቤ መፍጠር ወይም ማዳበር ነው፡፡ እንዲሁም በዘርፉ ያለውን ክፍተት በመሙላት ይሞላል፡፡ በዚህ ርዕስ ዙሪያ ሌሎች ጥናቶች እንዲካሄዱ በር ይከፍታል፡፡ ሀብታሙ አለባቸው በልቦለዶቹ ፈጠራና እውነታን እንዴት አዋህዶ እንዳቀረበው ግንዛቤ ሊያስጨብጥ ይችላል፡፡ ይህም ሥነጽሑፍ የገሀዱ ዓለም ነፀብራቅ መሆኑን ማሳያ ነው፡፡ ልቦለዶችን ከሀዲስ ታሪካዊ ንድፈ ሃሳብን አንጻር ለመረዳት ያስችላል፡፡ ታሪክን ለማስተማር እና ለማስተላለፍ ልቦለድ ያለውን ሚና ዳሰስ ያለ ጥናት ማካኼድ ለሚፈልግ ተመራማሪ እንደ መነሻ ሀሳብ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡ በተጨማሪም ጥናቱን መሰረት በማድረግ ሌሎች ጥናቶች እንዲካሄዱ ሊያበረታታ ይችላል፡፡

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በዋናነት በቤተ መጽሐፍት ውስጥ በሚካሄድ ምርምር ላይ ተመርኩዞ የሚከናወን ነው፡፡ እውነታን ከፈጠራ ጋር አዋህደው የጻፉ በርካታ ደራሲያን ቢኖሩም ለእዚህ ጥናት የተመረጡት ከደራሲ ሀብታሙ አለባቸው የድርሰት ስራዎች ውስጥ *የሱፍ አበባ* እና *የቄሳር እንባ* ናቸው፡፡ እነዚህ መጻሐፍት የተመረጡበት ምክንያት የፈጠራና የእውነታ ውህደትን ሊያሳዩ የሚያስችሉ ታሪኮችን በመያዛቸው እና የሁለቱም ልቦለዶች መቼት የአንድ ዘመን በመሆኑ ነው፡፡ እውነታ በሥነጽሑፍ ሥራዎች ውስጥ ያለውን "እውነት" ማጉላት ትኩረቱ ነው፡፡

በሥነ ጽሑፍ ውስጥ እውነታዊነት ሕይወትን የሚገልጽበት መንገድ ነው። "እውነታዊነት ሥነጽሑፋዊ ዘዴ ነው። በርካታ የእውነታዊነት ዓይነቶች ቢኖሩም በዚህ ጥናት ጥቅም ላይ የሚውለው ማህበራዊ እውነታ ነው። በአጠቃላይ የጥናታዊ ጽሑፉ ወሰን የሚሆነው የፈጠራና የእውነታ ውህደትን በተመረጡት *የሱፍ አበባ* እና *የቄሳር እንባ* መጻሕፍት ላይ ተንትኖ ማሳየት ነው። በትንተና ሂደት ሀዲስ ታሪካዊነት ንድፈ ሃሳብ ላይ ተወስኖ ማሳያ ከሚሆኑ ፅንሰ ሀሳቦች ጋር በማዛመድ ተተንትኖ ቀርቧል። በተጨማሪም በታሪክና በሥነጽሑፍ መካከል ያለው ድንበር እና በምናባዊነትና በእውነታ መካከል ያለው ድንበር የሚሉ ፅንሰ ሃሳቦች ላይ የሚወሰን ይሆናል።

## 1.7. የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናት ዓነታዊ የምርምር ስልትን መሰረት በማድረግ የፈጠራ እና የእውነታ ውህደትን ለጥናቱ በተመረጡ ልቦለዶች ተንትኖ ማሳየት ዓላማው ነው። ዓይነታዊ የምርምር ስልት የተመረጠበት ምክንያት ለጥናት የተመረጡት መጽሐፍትን በጥልቀት ደጋግሞ በማንበብ የፈጠራና የእውነታ ውህደትን ተንትኖ ለማቅረብ አመች ስለሆነ ነው። በተጨማሪም ሀዲስ ታሪካዊ ንድፈ ሃሳብን በመጠቀም ለጥናት በተመረጡ ልቦለዶች ውስጥ ያለውን ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያው ጉዳዮች ከአውዱ አንፃር ይፈትሻል። ሀዲስ ታሪካዊ የትኛውም ቴክስት ከአውድ ውጪ ሊሆን እንደማይችል ያምናል። ልቦለድ ከፓለቲካ፣ ከማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ነጻ ሆኖ ይቆማል ብሎ አያምንም። በታሪክ ጸሐፊው ላይ በወቅቱ ያለው ፍልስፍና፣ፖለቲካዊ ጉዳይ፣የራሱ የጸሐፊው አቋም፣አመለካከት እና በማስረጃነት የሚያገኛቸው ሰነዶች ሁሉ ተጽዕኖ ላይ ይጥሉታል ብሎ ስለሚያምን ታሪክ ፍፁም ሊሆን አይችልም።

### 1.7.1.የቴክስት መምረጫ መስፈርቶች

የጥናቱ የንሞና ዘዴ ዓላማ ተኮር (Purposive sampling) ነው። ይህ ዘዴ ለጥናቱ ግብዓትነት የሚውሉ መረጃዎችን ከጥናቱ ዓላማ ጋር ቃኝቶ ለመሰብሰብ የሚያመች ነው። የፈጠራና የእውነታ ውህደት እንዴት እንደቀረበ ተንትኖ ለማሳየት ከሀብታሙ አለባቸው ስራዎች ውስጥ የተመረጡት *የሱፍ አበባ* እና *የቄሳር እንባ* ልቦለዶች ናቸው። እነዚህ ልቦለዶችን ለመምረጥ ጥቅም ላይ የዋሉት የመምረጫ መስፈርቶች የሚከተሉት ናቸው። የመጀመሪያው ከልቦለድ ስራዎቹ ውስጥ በታሪካዊ እውነታዎችና በፈጠራ የተሞላ ታሪክ የያዙ ልቦለዶችን ለመለየት ተሞክሯል። እንዲሁም በገሀዱዓለም ያሉ እና የነበሩ ሰዎችን በገጸባህሪነት በልቦለዶቹ ውስጥ

መቅረባቸውን ተመልክቷል። በመቀጠል የልቦለዶቹ መቼት እና ታሪካዊ ክስተቶችን በመውሰድ ልቦለዶቹን ለመምረጥ ጥረት ተችሏል። በአጠቃላይ በዚህ ጥናት ከሀብታሙ አለባቸው ስራዎች ውስጥ የሱፍ አበባ እና የቄሳር እንባ ተመርጠው ትንተና ተደርጎባቸዋል።

### 1.7.2.የመረጃ ምንጭ እና የመረጃ መሰብሰቢ ዘዴዎች

የጥናቱ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ሰነድ ፍተሻ ሲሆን በ'ሱ ላይ በመመርኮዝ ሁለት ዓይነት የመረጃ ምንጮች ጥቅም ላይ ውለዋል። እነሱም፡- ቀዳማይ እና ዳህራይ ናቸው። ቀዳማይ የመረጃ ምንጭ ሁነው የሚያገለግሉት የተመረጡት ሁለቱ መጻሕፍት *የሱፍ አበባ* እና *የቄሳር እንባ* ናቸው።

ዳህራይ የመረጃ ምንጮች በመሆን የሚያገለግሉት ለጥናቱ ግብዓትና አጋዥ በመሆን መረጃ የሚሰጡ ሰነዶች፡ እንደ ደም ያዘለው ዶሴ የልዩ አቃቤ ህግ ጽ/ቤት ያዘጋጀው መዝገብ፣ ልዩ አቃቤ ህግ በእነ ኮ/ል መንግሥቱ ኃ/ማርያም ላይ የቀረበው ክስና ፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በ2009ዓ.ም ያሳተመው መጽሐፍ፣ ከኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ-ኢህአዴግ በዶ/ር መራራ ጉዲና በ2002 ዓ.ም የታተመ መጽሐፍ ፣ያ ትውልድ ቅፅ 1 እና ቅፅ 2 ፣ ዳኛው ማነው ፣ "Red Tears" ዳዊት ወ/ጊዮርጊስ የተጻፈ መጽሐፍ እና ሌሎችም ስለወቅቱ የተፃፉ መዛግብት ናቸው። ለትንተና የመረጥኳቸው መጻሕፍት የያዙትን እውነታ ለመፈተሽ ከሌሎች ሰነዶች ጋር በማመሳከር እና ለመተንተኛነት ጥቅም ላይ ያዋልኩት ሥነጽሑፋዊ ንድፈ ሃሳብ ሀዲስ ታሪካዊ ሂስ ጋር ለማሳያነት ይጠቅማሉ ያልኳቸውን መረጃዎች ሰብስቤያለሁ።

### 1.7.3. የመረጃ መተንተኛ ዘዴ

ይህ ጥናት በዋነኛነት ለምርምር በተመረጠው ልቦለድ ውስጥ የእውነታና የፈጠራ ውህደትን በመተንተን አጉልቶ ማሳየት ነው። ስለዚህ በዚህ ጥናት ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለው ሀዲስ ታሪካዊ ሂስ ላይ በመመርኮዝ ገለጻ እና ፍካሬ የመተንተኛ ስልት ነው ማለት ነው። ሀዲስ ታሪካዊ ሂስ ልቦለዶች ከተጻፉበት አውድ እና አንድ ቴክስት ከሌሎች ቴክስቶች ጋር በማገናዘብ ለመረዳት ያስችላል። ሀዲስ ታሪካዊ በየትኛውም የጥናት መስክ የተገደበ አይደለም። ምክንያቱም ሁሉም የአንድ ባህል ክፍሎችን እርስ በርስ ሲቀረጹ ያያል። ታሪክ ትረካ እንጂ ንፁህ ያልተበረዘ የትክክለኛ ምልከታ ስብስብ አይደለም የሚል መርህ አለው (Ann.B.Dobin፣2012፣178)።

የአንድ ማህበረሰብ ታሪካዊ ክስተት እንደ ታሪካዊ ሂስ ተርጓሚው የሚሰጠው ትርጓሜ እንጂ በትክክል የተከሰተው እውነታ አይደለም የሚቀርበው የሚል አቋም አላቸው፡፡ በዚሁ መሰረት የተመረጡት ልቦለዶች ከደራሲው ፈጠራ ጋር ታሪኩ ተዋህዶ መቅረቡን፣ ከተጻፉበት አውድ እና መጻሕፍቶቹን ከሌሎች ቴክስቶች ጋር በማጋናዘብ ትንትናው ይደረጋል፡፡ ለጥናቱ በተመረጡ ቴክስቶች ውስጥ ያሉ ገፀባህርያት ራሳቸውን ችለው ይቀርባሉ፡፡ ይህ በመሆኑ በገፀባህርያቶቹ አማካይነት የሚዳሰሰው *በየሱፍ አበባ* የኢሐአፓ ታጋይ የነበሩ ሰዎች ሲሆኑ *በቁሳር እንባ* ደግሞ ዋና ገፀባህርይ በመሆን የቀረበው የኮ/ሌ መንግስቱ ኃ/ማርያም ህይወት ነው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## ንድፈ ሃሳባዊ ዳራና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

### 2.1. ንድፈ ሃሳባዊ ዳራ

በዚህ ክፍል ከጥናቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጽሑፎች ለጥናቱ ማስኬጃና መቀንበቢያ የሚያገለግሉ ንድፈ ሃሳቦች ቀርበዋል። በንድፈ ሃሳባዊ ዳራዉ የሚዳሰሱት፡- የእውነታ ምንነት ፣ የፈጠራ ምንነት ፣ የሀዲስ ታሪካዊ ምንነት የሚሉት ፅንሰ ሃሳቦች ይብራራበታል።

#### 2.1.1. የእውነታ ምንነት

በሥነ ጽሑፍ ውስጥ ያለው እውነታ ከተፈጥሮ በላይ የሆኑ ነገሮችን በማስወገድ ርዕሰ-ጉዳዩን በእውነት መወከልን ያመለክታል። ይህ ዘውግ፣ ስነ-ጽሑፋዊ እውነታ ተብሎ የሚጠራው በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ላይ በፈረንሳይ ሥነ-ጽሑፍ እና በሩሲያ ሥነ-ጽሑፍ ከተጀመረው ከእውነታው የጥበብ እንቅስቃሴ የመነጨ ነው። እውነታ ምን እንደሆነ እና እንዴት እንደሚገለጽ በኢፒስቴሞሎጂ ጥያቄ መልስ ሳያገኝ ለሁለት ሺህ ዓመታት እንደቆየ ይነገራል። Ramanan (2018፣67) እንደሚገልጹት "እውነታ እምነት ነው። ምክንያቱም የምናየው እውነት የመጨረሻው እውነታ ሊሆን ስለማይችል" ይላሉ። እውነታ (Reality) ነባራዊ ሀቅ በመሆኑ ሁለንተናዊ የሆነ ህልውና አለው፤ ሊታሰብ፣ሊታወቅ ፣ ሊተላለፍ እና ሊረጋገጥ የሚችል በመሆኑ ማንኛውም የዕለት ተዕለት የኑሮ ሁኔታ መወከል ይችላል።

ሥነ-ጽሑፋዊ እውነታዎች የተለመዱ ነገሮችን እንደነበሩ ለመወከል ይሞክራል, የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎችን እና ልምዶችን ያሳያል። በእውነተኛ ህይወት ውስጥ እንዳሉት ተዛማች እና ውስብስብ ገጸ-ባህሪያትን የዕለት ተዕለት ልምዶችን በማሳየት እውነታውን ይወክላል። በሥነጽሑፍ ውስጥ የሚቀርቡ እውነታዎች ከልቦለዱ ባሻገር በገሀዱ ዓለም ያለውን ህይወት ቁልጭ አድርገው ያሳያሉ። ሥነጽሑፋዊ እውነታ በገሀዱ ዓለም ህይወት ውስጥ ያሉትን ዕለታዊ ልምዶችን በማሳየት እውነታውን የሚወክል የሥነጽሑፍ እንቅስቃሴ ነው። በዋነኛነት መካከለኛ እና ዝቅተኛ የሕብረተሰብ ክፍሎችን፣ የሚታወቁ ሰዎችን፣ ቦታዎችን እና ታሪኮችን

ያሳያል። ታሪክን በድራማ ወይም በሮማንቲክ ከማሳየት ይልቅ በተቻለ መጠን እውነታውን ቁልጭ አድርጎ ለማሳየት የሚጥር ነው ( Taghizadeh፣2014፣1630) ።

በሥነጽሑፍ አውድ ውስጥ አንድ ቴክስት በቅደም ተከተል እና በክስተቶች የተሞላ ከሆነ ተጨባጭ መሆን ይችላል። ምክንያቱም ገፀባህርያቱን ፣ ታሪኩን ወይም መቼቱን ከገሀዱ ዓለም ጋር ስለሚገናኝ ቴክስቱ በእውነታ ይቀነበባል። Iser (1971፣ ) እውነታን ሲገልጹ “ እውነታ የታሪኩ መነሻ እና መድረሻ ነው። ታሪኩ ከጽሑፉ ጋር ያለው መስተጋብር እውነተኛ ወደሆነ ልምድ በመምራት አንባቢው በራሱ ለእውነታው ምላሽ እንዲሰጥ ማድረግ ይቻላል” ይላሉ። በሌላ አነጋገር ልቦለድ ከገሀዱ ዓለም ሃሳቦችን ይወስዳል። ይህ የወሰደውን ሃሳብ በማቅረብ እውነታን ያብራራል። ይሁን እንጂ ሃያሲያን እውነታውን መግለጽ ብዙውን ጊዜ እውን እንዳልሆነ። ይህ ክርክር ብዙውን ጊዜ ትክክለኛውን ነገር በትክክል አናገኝም በሚለው ሀሳብ ላይ የተመሰረተ ነው። እውነታውን ለማቅረብ፣ እንዴት እንደምናስታውሰው እና እንዴት እንደምናገኘው “እውነተኛ” የሆነውን ጉዳይ እንስላለን። እውነታ በሥነጽሑፍ ሥራዎች ውስጥ ያለውን “እውነት” ማጉላት ትኩረቱ ነው። በሥነ ጽሑፍ ውስጥ እውነታዊነት ሕይወትን የሚገልጽበት መንገድ ነው፤ በሥነ-ጽሑፍ ውስጥ ያለው እውነታ በዕለት ተዕለት ልምዶች እና ገጸ-ባህሪያት ላይ በማተኮር ህይወት እንዳለ በትክክል ለመወከል የሚሞክር ዘውግ ነው። ታሪክን በተቻለ መጠን በእውነት እና በተጨባጭ ለመንገር የሚያስችል ዘዴን ይሰጣል። እውነታዊነት ሥነጽሑፋዊ ዘዴ ነው። ይህ ማለት ደራሲው የእውነታ ነጸብራቅ እና የሰው ልጅ ህይወት ማጥናት ነው” (Sobirova, Z ፣ 2019 ፣ 189)። እውነታዊነት ከጭፍን ጥላቻ፣ ከርዕዮተ ዓለም ወይም ከርዕዮተ ዓለም የፀዳ ሁሉንም የሕይወት ዘርፍ እውነታዎችን መግለጽ መቻል ነው።

እውነታዊነትን በሥነጽሑፍ የመግለጽ እንቅስቃሴ በ19ኛው ክ/ዘ አጋማሽ በፈረሳይ የተጀመረ ሲሆን ከትንሽ ጊዜ በኋላ ወደ እንግሊዝ፣ሩሲያ እና ዩናይትድ እስቴት ተስፋፋ። እውነታዊነት ለሮማንቲሲዝምን እንቅስቃሴ ምላሽ ለመስጠት የፈለቀ ጽንሰ ሃስብ ነው። የሮማንቲሲዝም ዘመን ወይም የሮማንቲክ ሥነ ጽሑፍ ከገሀዱ ዓለም በራቁ በሚያስደንቁ ታሪኮች ይታወቃል። ስለ እውነታዊነት ጅማሮ Maryam F, A. (2022 ፣ 325) እንደሚገልጹት

> Realism is a literary-artistic school that became popular in Europe and America in the mid-nineteenth century. A school that emphasized the objectivity and reality of society and as if it

considered itself as one of those people; As he believed that in order to state the realities of society, there is no need for complicated language and language should be simple and transferable in order to depict a correct image of society

እውነታዊነት በ19ኛው ክ/ዘ አጋማሽ ላይ በአሜሪካ እና በአውሮፓ የስነጥበብ ትምህርት ቤቶች  ታዋቂነትን አጊንቷል፡፡ የህብረተሰቡን እውነታ እና ተጨባጭ ነገሮችን አፅንዖት በመስጠት እራሱን ከማህበረሰብ እንደ አንዱ አካል አድርጎ ይቆጥራል፡፡ የህብረተሰቡን ነባራዊ ሁኔታ ለመግለጽ ውስብስብ ቋንቋ ሳይሆን የህብረተሰቡን ትክክለኛ ገጽታ የሚያሳይ ቀላል እና ግልጽ ቋንቋ መጠቀም እንዳለበት ያምናል፡፡

የእውነታዊነት እንቅስቃሴ በመጀመርያ በፈረንሳይ ከጀመሩት ውስጥ ጉስታቭ ኮርቤት ፣ Jean-Francois Millet፣  Honore Daumier እና Corot ታዋቂዋ የእውነታዊነት እንቅስቃሴ አራማጅ ኤሚሌ ዞላ ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ከፈረንሳይ አልፎ በአጭር ጊዜ ውስጥ በአውሮፓ እና በአሜሪካ ተቀባይነትን አጊንቷል፡፡  ጆርጅ ኤልዮት በእንግሊዝ ያለውን እንቅስቃሴ የመራች ሲሆን "Adam Bede" በሚለው ስራዋ የእንግሊዝ ገበሬዎችን እውነተኛ ምስል ለማሳየት ሞክራለች፡፡

የእውነታዊነት እንቅስቃሴ በአሜሪካ ለእውነታ ውክልና እና የገፀባህርያት ድርጊቶችን ተጨባጭ ለማድረግ አጽንዖት ሰጥቷል፡፡ Mukesh Williams (nd ፣56) እንደሚገልጹት "በ1880ዎቹ እና በ1890ዎቹ በአሜሪካ ልቦለዶች ውስጥ የዳበረው የእውነታዊነት ጽንሰ ሃሳብ በመካከለኛው መደብ ህይወት እያደገ የመጣውን የድል አድራጊ ቡርጂየስ አፈ ታሪክ እና እንከን የለሽ ታሪኮችን የሚቃወም ነው" ፡፡  ዊልያም ዲን ሃውልስ በአሜሪካ የእውነታዊነት እንቅስቃሴ አራማጅ ሲሆን በስራዎቹ የአሜሪካንን ህይወት ፣ ጉዞ እና ሌሎች ጉዳዮችንም ይገልጻል፡፡ በአጠቃላይ እውነታዊነት የሰውን ልጅ የህይወት ልምድ ለመወከል የሮማንቲሲዝምን ጽንሰ ሃሳብ በመቃወም የፈለቀ ጽንሰ ሃሳብ ነው፡፡ ይሄንንም Ali Taghizadeh ( 2014፣ 1629)

The main difference between the novel and the romance is the way in which they view reality. The novel renders reality closely and in comprehensive detail. We come to see these people in their real

complexity of temperament and motive. … Character is more important than action and plot, … The events that occur will usually be plausible, given the circumstances, … By contrast the romance, following distantly the medieval example, feels free to render reality in less volume and detail. It tends to prefer action to character, and action will be freer in a romance than in a novel, encouraging as it were, less resistance from reality.

በልቦለድ እና በሮማንቲሲዝም መካከል ያለው ዋነኛው ልዩነት እውነታውን የሚመለከቱበት መንገድ ነው፡፡ ልቦለድ እውነታውን በቅርበት እና በስፋት ያቀርባል፡፡ እነዚህን ሰዎች በባህሪያቸው ውስብስብነት እና ተነሳሽነት ልናያቸው እንችላለን፡፡ ገፀባህሪያት ከድርጊት እና ሴራ የበለጠ አስፈላጊ ናቸው፣ … ከሁኔታዎች አንፃር የሚከሰቱ ክስተቶች ብዙውን ጊዜ አሳማኝ ይሆናሉ፣… በአንፃሩ ደግሞ ሮማንቲሲዚም ፣ የመካከለኛው ዘመን ምሳሌን በመከተል፣ እውነታውን በትንሽ መጠን እና በዝርዝር ለማቅረብ ነፃነት አለው፡፡ እውነታዊነት ከሮማንቲሲዝም በተሻለ መልኩ ተግባርን ከገጸ ባህሪ የመምረጥ ዝንባሌ ይኖረዋል፡፡

ሌላው የእውነታዊነት ገፅታ ከታላላቅ የፍቅር ሰዎች እና የጀግንነት ተግባሮቻቸው ውስጥ አለመገኘት ነው፡፡ ከሰው በላይ የሆኑ የፍቅር ገፀ-ባህሪያትን ፣ አስደናቂ እና ድንቅ ገጠመኞቻቸውን በመሳል ላይ እውነታዊነት ፍላጎት የለውም፤ከዚያ ይልቅ በዕለት ተዕለት ሕይወት ውስጥ ያሉ እውነተኛ ውጣ ውረዶች ላይ ያደላል ፡፡ በተጨማሪም በእውነታዊነት ልብ ወለድ ውስጥ ያሉ ገጸ-ባህሪያት በተለምዶ የታችኛውን እና የመካከለኛ ክፍሎችን አባላትን ይወክላሉ (Ali Taghizadeh ( 2014፣ 1629) ፡፡

ሥነ-ጽሑፋዊ እውነታ ብዙ ገጽታ አለው፡፡ በተለያዩ ጸሃፊዎች ጽሑፎች ውስጥ ስድስት የተለያዩ የእውነታዊነት ዓይነቶች አሉ፡፡ Magical Realism፣ Social Realism፣ Naturalism፣ Psychological Realism፣ Kitchen Sink Realism እና Socialist Realism በዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ የሚዳሰሰው ግን የእውነታዊነት ዓይነት የማህበራዊ እውነታ(Socialist realism) ነው፡፡

### 2.1.1.1. ማህበራዊ እውነታ(Socialist realism)

ማህበራዊ እውነታ ህብረተሰቡን በትክክለኛው መንገድ የሚግልጽ የእውነታዊነት ፅንሰሃሳብ ዓይነት (ዘውግ) ነው። ይህ ዘውግ በሠራተኛው ክፍል ሕይወት ላይ የሚያተኩር ሲሆን የዕለት ተዕለት ህይወትን ያሳያል። በደራሲው የመግለጽ ችሎታ እና በቃላት ኃይል የማህበራዊ እውነታ መዋቅርን መግለጽ ይቻላል።

ማህበራዊ እውነታ በተለያዩ መንገዶች ለሩሲያ አብዮት ፣ ለሶቪየት ኮሙኒዝም ፣ ለማርክሲዝም እና ለሌሎች ለተለያዩ ጽንሰ ሃሳቦች ምላሽ የመስጠት ዘዴ ነው። Arpit Dave (2019፣ 12) "ማህበራዊ እውነታ ማለት በሥነጽሑፍ ማኅበራዊ እውነታን ማሳየት ነው። እንዲሁም በሥነጽሑፍ በሚገለጸው ማህበረሰብ እና በገሀዱ ዓለም ባለው ማህበረሰብ መካከል አንድ የሆነ ግንኙነት መኖር አለበት" በማለት ይገልጻሉ። በተጨማሪም ማህበራዊ እውነታ እንደ ሁኔታው የሚገለጽ ሳይሆን እውነታን የሚያሳይ መሆን አለበት ይላሉ። ማህበራዊ እውነታ በሶቪየት ሩሲያ የተጀመረ የሥነጽሑፍ ቲዎሪ ነው። Luuel Epner (n.d ፣ 114) እንደሚከተለው ሲገልጹ

> "Even during the period under discussion socialist realism was the only accepted creative method in soviet leaturature. As we know, the notation of socialist realism first appred in the Soviet Union at the beginning of the 1930s. In the statuse of of the writers union of soviot Eistonia issued in 1943, it was defined as follows, 'socialism realism (…..) demands from the artist an authentic and historically precise depiction of reality in its revolutnary development".

> "ማህበራዊ እውነታ በሶቪየት ሥነጽሑፍ ውስጥ ብቸኛው ተቀባይነት ያለው የፈጠራ ዘዴ ነበር። የማህበራዊ እውነታ ፅንሰ-ሀሳብ በ1930ዎቹ መጀመሪያ ላይ በሶቭየት ህብረት እንደታየ ይታወቃል። እ.ኤ.አ. በ 1943 በወጣው የሶቪየት ኢስቶኒያ የፀሐፊዎች ህብረት ፣ ማህበራዊ እውነታ እንደሚከተለው ተገልጿል፤

"ማህበራዊ እውነታ ከደራሲው በእድገቱ ውስጥ ያለውን የእውነታ እና የታሪካዊ ትክክለኛነትን ይጠይቃል።

ማህበራዊ እውነታ እንደ ሥነጽሑፍ እንቅስቃሴ በ19ኛው እና በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ በኢንዱስትሪ እና በከተሞች መስፋፋት ለመጣው ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ እኩልነት ምላሽ ሆኖ ታየ። የሰራተኛውን እና የድሆችን እውነታ ለማሳየት እና ማህበራዊ ኢፍትሃዊነትን እንደ ድህነት ፣ ጭቆና እና ብዝበዛ ያሉ የሥርዓት ጉዳዮችን ለማጋለጥ ሞክሯል። በሥነጽሑፍ ብዙን ጊዜ የሥራ መደብ ገፀባህርያትን በመጠቀም ትግላቸውን ፣ ልምዶቻቸውን እና የህይወታቸውን አስከፊነት በተጨባጭ ለማሳየት ይሞክራል። እንዲሁም እንደ መደብ ግጭት፣ ዘር እና የፆታ ልዩነት፣ ኢንደስትሪላይዜሽን እና የካፒታሊዝም ተፅእኖ በህብረተሰብ እና በግለሰቦች ላይ ባሉ ማህበራዊ ጉዳዮች ሊያተኩር ይችላል። Arpit Dave (2019፣ 13) ስለ ማህበራዊ እውነታ አጀማመር ሲያስረዱ

> “The theory of Socialist Realism was adopted by the Congress of Soviet Writers in 1934. Approved by Joseph Stalin, Nickolai Bukharin, Maxim Gorky and Andrey Zhdanov, 84 Socialist Realism demanded that all art must depict some aspect of man’s struggle toward socialist progress for a better life”.
>
> “የሶሻሊስት ሪያሊዝም ፅንሰ-ሀሳብ በ1934 በኮንግረስ በሶቪየት ፀሐፊዎች ተቀባይነት አግኝቷል። በጆሴፍ ስታሊን፣ ኒኮላይ ቡኻሪን፣ ማክስም ጎርኪ እና አንድሬይ ዠዳኖቭ የማህበራዊ እውነታ አራማጆች ተቀባይነት አጊንቶ ማህበራዊ እውነታ በሁሉም ኪነጥበብ ማህበራዊነት ለሰው ልጅ የተሻለ እድገት የሚያደርገውን ትግል እንዲያይ ጠይቋል”።

የሶሻሊስት እውነታ በዓለም ዙሪያ በስነ-ጽሁፍ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ አሳድሯል። ተጽኖውም በተለያዩ የሥነ ጽሑፍ ዓይነቶች ላይ ይታያል። ንቅናቄው የሰራተኛውን ክፍል፣ የኢንዱስትሪ ሰራተኞችን እና የወታደሮችን አዎንታዊ ምስሎችን ለማስተዋወቅ እና በሶሻሊስት ስርዓት ስር ያሉትን የተራ ህዝቦችን ህይወት ለማሳየት ሞክሯል። በተጨማሪም በሥነ ጽሑፍ ብዙውን ጊዜ የሥራ መደብ ገፀ-ባሕሪያትን ያሳያል፤ እናም ተጨባጭ እና ዝርዝር መግለጫዎችን በመጠቀም የሕይወትን አስከፊነት ለማስተላለፍ ተጋድሎአቸውን እና ልምዳቸውን ይዳስሳል። የመደብ

ግጭት፣ የዘር እና የፆታ ልዩነት፣ የኢንደስትሪላይዜሽን እና የካፒታሊዝም ተፅእኖ በህብረተሰብ እና በግለሰቦች ላይ ባሉ ማህበራዊ ጉዳዮች ላይም ሊያተኩር ይችላል። የማህበራዊ እውነታ ዘውግ በኅብረተሰቡ ላይ ወሳኝ አስተያየቶችን በመስጠት ኢ-እኩልነትን የሚያራምዱ እና የሚያስጠብቁ ማህበራዊ አወቃቀሮችን ላይ በእንደዚህ አይነት ስራዎች በተለይም የስራ መደብ ህይወት ላይ ባተኮሩ ታሪኮች ጎላ ብለው ይታያሉ።

በአብዛኛውን ጊዜ "social" and "socialist" እውነታዊነት እንደ አንድ ይታያሉ። "social" እውነታዊነት በሥነጽሑፍ የሚነሱ ርዕሰ ጉዳዮችን ፣ ማህበራዊ ጠቀሜታ ያላቸው የዕለት ተዕለት የሰው ልጅ የሥራ ሁኔታዎችን የሚገልጽ ነው። "socialist" እውነታዊነት ደግሞ ማህበራዊ እውነታን እንደሁኔታው ሳይሆን እንደራሱ የሚያሳይ መሆን አለበት ብሎ የሚያምን እና የተለመደውን የማርክሲስት አካሄድ የሚከተል ነው ( Arpit Dave፣ 2019፣ 13)። በዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ እንደአስፈላጊነቱ ሁለቱም ማለትም "social" and "socialist" እውነታዊነት ጥቅም ላይ ይውላሉ።

### 2.1.2. የፈጠራ ምንነት

"ፈጠራ" የሚለው ቃል በርካታ ትርጉሞች አሉት። በሥነ ጽሑፍ ውስጥ የሚያመለክተው በጸሐፊው የተፈጠሩ፣ የተፈለሰፉ እና የተሰሩ ሥራዎችን ነው። እነዚህ ስራዎች በተለምዶ እንደ ሴራ፣ ገጸ-ባህሪያት፣ ቅንብር እና ጭብጥ ያሉ ክፍሎችን በሚያካትቱ ትረካዎች ወይም ታሪኮች ተለይተው ይታወቃሉ። ሥነ-ጽሑፍ ውብ የሆነውን የጥበብ ክፍል ለመሸመን የሚያስችሉ በርካታ ዘውጎች አሉት። በእነዚህ ዘውጎች የፈጠራ ጽሑፍ አንባቢን የሚያሳትፍ፣ የሚያነቃቃ ወይም የሚያስደንቅ፣ ስሜትን የሚቀሰቅስ እና አስደሳች ወይም አሳዛኝ ታሪኮችን ለመንገር ጥቅም ላይ የሚውል ዘዴ ነው። የሥነጽሑፋዊ ፈጠራ ምንነትን Nalya Ovshieva (2019) ሲገልጹ "ሥነጽሑፋዊ ፈጠራ ከአጻጻፍ ዘዴ አንጻር እንደ ምናባዊ ወይም የፈጠራ ጽሑፍ የተፀነሰ ነው" ይላሉ። ሥነጽሑፋዊ ፈጠራ ውስጥ ምናብ ፣ መነሳሳ እና ግኝት ጎልተው ይታያሉ። አዳዲስ ሀሳቦችን ወይም ነገሮችን በአዲስ ማዋቅር ያለፉትን ልምዶች እንደ አዲስ ቅጽ እንደገና የመፍጠር ችሎታ ነው። Marshall Hahn ( 3፣ 1968) እንደሚከተለው ይገልጻሉ

> "Ribot (1906), In his classic work, The Creative Imagination, stated that man is creative, or able to create, because of (a) the motor

activities produced by appetites, tendencies and desires, and (b) the possibilities of spontaneous revival of images that become grouped in the new combinations. Wertheimer (1945) similarly proposed that creative thinking is the successful transposition of a member from one configuration to another

“ሪቦት (1906) The Creative Imagination በተሰኘው ስራው ፣ የሰው ልጅ ፈጠራ ወይም መፍጠር የሚችልበት ምክንያት ሀ) በምግብ ፍላጎት ምክንያት እንዲኖረን በሚደረግ እንቅስቃሴ ፣ በፍላጎቶች እና ዝንባሌዎች ፣ ለ) በአዲስ ጥምሮች በሚሰበሰቡ ድንገተኛ ምስሎች የመነቃቃት አጋጣሚዎች እንደሆነ ይገልጻሉ። ዌርታይመር (1945) በተመሳሳይ መልኩ የፈጠራ አስተሳሰብ አንድን አካል ከአንድ ውቅር ወደ ሌላ ውቅር በተሳካ ሁኔታ መለወጥ እንደሆነ ገልጿል”።

ፈጠራ የሚያመለክተው በእውነተኛ ህይወት ክስተቶች ላይ ያልተመሰረቱ ነገር ግን ከጸሐፊው አስተሳሰብ የተፈጠሩ ጽሑፎችን ነው። በገሃዱ ዓለም ውስጥ የማይገኙ ገጸ-ባህሪያትን፣ መቼቶችን፣ ሁነቶችን እና ትረካዎችን መፍጠርን ያካትታል። ደራሲያን ብዙ ጊዜ ለመዝናኛ፣ ለዳሰሳ ጭብጥ ወይም ለሥነ ጥበባዊ አገላለጽ የሆኑ ታሪኮችን ለመጻፍ የፈጠራ ችሎታቸውን ይጠቀማሉ። ፈጠራ አዲስ ዘይቤዎችን ወይም አንድን ነገር የማድረግ ዘዴዎችን ማግኘት ሲሆን በብዙ መንገዶች ማሰብ ያስችላል። ስለዚህ የተሻሉ የአስተሳሰብ ክህሎቶችን ለማዳበር ይረዳል። ሥነጽሑፍ በራሱ ሌላውን የተግባር ገፅታ ማለትም የፈጠራ ችሎታን በመቀበል ወደ አለም መድረሻ ነው። ሥነጽሑፍ የፈጠራ አንድ ገጽታ ነው፤ የፈጠራ ስራዎች በዋናነት የረጅም እና አጫጭር ልብወለዶችን መልክ ይይዛሉ።

በልብ ወለድ እና በኢ-ልብ ወለድ መካከል ያለው ቁልፍ ልዩነት ልቦለድ ታሪኮችን እና ምናባዊ ፈጠራዎችን የሚያካትት ሲሆን ይህም የተፈጠሩ ዓለሞችን እና ገጸ-ባህሪያት ያሳያል። በአንፃሩ፣ በኢ-ልብወለድ ደግሞ እውነታዊ መረጃዎችን እና የገሃዱ ዓለም እውቀትን በማቅረብ ላይ ያተኮረ ነው። በአጠቃቀም ረገድ፣ ልቦለድ ብዙውን ጊዜ ግላዊ ነው፣ ይህም ማለት በደራሲያን ግላዊ ስሜቶች እና አስተያየቶች በእጅጉ ይነካል። የልቦለድ ታሪክ በተለያዩ አመለካከቶች (በመጀመሪያ ሰው፣ ሶስተኛ ሰው፣ ወዘተ) ሊሰጥ ይችላል። ገላጭ ቋንቋዎችን እና ሥነጽሁፋዊ መሳሪያዎችን ፣ምሳሌዎችን እና ዘይቤዎችን በመጠቀም ተመልካቹን በታሪኩ ውስጥ ያሳትፋል።

ፈጠራ (ልቦለድ) እውነታውን ያጋነናል ወይም ያዛባ ይሆናል። አሊያም ታሪኩ ሙሉ በሙሉ የጸሐፊው ፈጠራ ሊሆን ይችላል። እሱ በፀሐፊው ዘይቤ ወይም ማሳካት በፈለገው ጉዳይ ላይ የተመሠረተ ነው። በልቦለድ ውስጥ ያለው ታሪክ በጸሐፊው የተፈጠረ ነው ነገር ግን በተጨባጭ መንገድ ቀርቧል። ልቦለድ የተለያዩ ግላዊ ጉዳዮችን ስለሚመለከት ለአንባቢው የተለያዩ ትርጉሞች ክፍት ነው። ፈጠራ ለልብ ወለድ እድገት ወሳኝ ሚና ይጫወታል። በፈጠራ ደራሲዎች የእውነታን ድንበሮች አልፈው አዲስ አለምን፣ ገፀ-ባህሪያትን እና ትረካዎችን መፍጠር ይችላሉ። በገሃዱ ዓለም ሊዳሰሱና ሊከወኑ የማይችሉ ነገሮችን በደራሲው የፈጠራ ችሎታ ማካተት ይቻላል። ይህንን ሃሳብ Lovecraft, H.P. (1927)

> The oldest and strongest emotion of mankind is fear, and the oldest and strongest kind of fear is fear of the unknown. It is through imagination that authors are able to tap into this fear and evoke powerful emotions in readers. Imagination allows authors to explore concepts and ideas that may not exist in the real world but are nonetheless deeply impactful.
>
> የሰው ልጅ ጠንካራና ከጥንት የነበረ ስሜት ፍርሃት ነው፤ ከጥንትም የነበረው እና ጠንካራው የፍርሃት አይነት ደግሞ የማይታወቅ ፍርሃት ነው። ደራሲያን ይህ ፍርሃት ውስጥ ገብተው በአንባቢዎች ውስጥ ኃይለኛ ስሜቶችን ለመቀስቀስ የቻሉት በፈጠራ ነው። ፈጠራ ደራሲያን በገሃዱ አለም ላይኖሩ የሚችሉ ነገር ግን ጥልቅ ተፅእኖ ያላቸውን ፅንሰ-ሀሳቦችን እንዲመረምሩ ያስችላቸዋል።

በልብ ወለድ ውስጥ ፈጠራን መጠቀም ደራሲያን የማህበረሰቡን ባህል እና እሴቶች እንዲቃወሙ ያስችላቸዋል። ይህም አንባቢዎች ከራሳቸው እውነታ ገደብ በላይ እንዲያስቡ ያነሳሳቸዋል። በዚህ መንገድ በልብ ወለድ መስክ ውስጥ ለአዳዲስ ፈጠራዎች መነሻ ሆኖ ያገለግላል። ለደራሲዎችም የማሰብ ነጻነትን ስለሚሰጥ አንባቢዎችን የሚማርክ እና የተረት ታሪክን ወሰን የሚያልፍ ዓለምን ይፈጥራል።

## 2.1.3.ሀዲስ ታሪካዊ ሂስ

በ20 ክ/ዘ የተለያዩ ንድፈ ሃሳቦች በተከታታይ ብቅ አሉ። እንደ ቅርጻዊያን ፣ መዋቅራዊያን ፣ ዲኮንስትራክሽን እና ሀዲስ ሂስ( new criticism)። ሀዲስ ታሪካዊ ሂስ ለእነዚህ ንድፈ ሃሳቦች ሰፋ ያለ ምላሽ ለመስጠት የፈለቀ ንድፈ ሃሳብ ነው። ሀዲስ ታሪካዊ ሂስ በአሜሪካዊው ሃያሲ Stephen Greenblatt በ“Renaissance Self-Fashioning: from More to Shakespeare”(1980) በሚለው መጽሐፍ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ እንደተገኘ ይነገራል። የሀዲስ ታሪካዊ ሂስ አቀንቃኞች እንደሚሉት ቋንቋውን እና የጽሑፉን መልዕክት ለመረዳት ብቻ መሞከር የአንድ ሳንቲምን አንድ ጎን ብቻ ማየት ነው። የአንድን ጽሑፍ ትርጉም ለማግኘት ከሁኔታው ጋር ማየት ያስፈልጋል። ታሪካዊ ሁኔታው እንዴት ተተረጎመ? እና አተረጓጎሙ ስለ ደራሲው ምን ይነግረናል? በሚለው ጥያቄ ላይ ትኩረት ያደርጋል። በዚህ ዕንሰ ሃሳብ ሁሉንም የሚያስማማ ታሪካዊ እውነት የለም፤ ሁሉም እውነታ የአተያይ ጉዳይ ነው። ይህንን ሃሳብ Tyson (2006፣282) እንደሚከተለው ይገልጻሉ።

> “Most of us raised to think about history in the traditional way would read an account of a Revolutionary War battle written by an American historian in 1944 and ask, if we asked anything at all, “Is this account accurate?” or “What does this battle tell us about the ‘spirit of the age’ in which it was fought?” In contrast, a new historicist would read the same account of that battle and ask, “What does this account tell us about the political agendas and ideological con- flicts of the culture that produced and read the account in 1944?” New histori- cal interest in the battle itself would produce such questions as, “At the time in which it was fought, how was this battle represented (in newspapers, magazines, tracts, government documents, stories, speeches, drawings, and photographs) by the American colonies or by Britain (or by European countries), and what do these representations tell us

about how the American Revolution shaped and was shaped by the cultures that represented it?"

"አብዛኞቻችን ታሪክን በባህላዊ መንገድ በማሰብ ነው ያደግነው። በ1944 በአንድ አሜሪካዊ የታሪክ ምሁር የተፃፈውን የአብዮታዊ ጦርነት ታሪክ ስናነብ "ይህ ዘገባ ትክክል ነው?" ብለን አንድ ነገር እንጠይቃለን ወይም "ይህ ጦርነት ስለተካሄደበት 'የዘመኑ መንፈስ' ምን ይነግረናል? ። በአንጻሩ አንድ የሀዲስ ታሪካዊ ተመራማሪ ስለዚያ ጦርነት ተመሳሳይ ዘገባ አንብቦ "ይህ ዘገባ ስለ ፖለቲካ አጀንዳዎች እና ርዕዮተ ዓለማዊ ጉዳዮች ምን ይነግረናል? ሲል ይጠይቃል። በተጨማሪም ሀዲስ ታሪካዊ እንዲህ ያሉ ጥያቄዎችን ያስነሳል_ ትግሉ በተካሄደበት ወቅት ይህ ጦርነት ( በጋዜጦች፣መጽሔቶች፣የመንግሥት ሰነዶች፣ ታሪኮች፣ ንግግሮች፣ሥዕሎች እና ፎቶግራፎች) እንዴት ይገለጻል? የአሜሪካ ቅኝ ግዛቶች ወይም በብሪታንያ (ወይንም በአውሮፓ አገሮች) እና እነዚህ ውክልናዎች የአሜሪካ አብዮት እንዴት እንደቀረጹ እና እሱን በሚወክሉት ባህሎች እንደተቀረጸ ምን ይነግሩናል?"

ሀዲስ ታሪካዊነት በዋናነት የፅንሰ ሀሳቦች እና የሀሳቦች ውጤት ነው። አንድ የሥነጽሁፍ ስራ እንደተለየ የስነጥበብ ወይም የጽሁፍ ስራ ሳይሆን የጊዜ፣ የቦታ እና የታሪካዊ ሁኔታዎች ውጤት ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል በሚል መነሻ መሰረት የተገኘ ሥነጽሁፋዊ ንድፈ ሀሳብ ነው። ሥነጽሑፋዊ ትንተና እና ትርጓሜ ከተለያዩ የድህረ መዋቅራዊ ጽንሰ-ሀሳቦች የተዋሃደ ሲሆን በተለይም የሉዊስ አልቱሰር የማርክሲስት ርዕዮተ ዓለም ፣ ሚሼል Foucault የንግግርና ኃይል እና የአንትሮፖሎጂ ክሊፎርድ ገርትዝ ውጤት ነው። ሉዊስ አልቱዘር፣ ፈረንሳዊው ፈላስፋ እና ድንቅ ማርክሲስት ሲሆን እስጢፋኖስ ጄይ ግሪንብላትን በእጅጉ የሚነካ ምልክታዊ የንባብን ዘዴ ፈጠረ። "Symptom" (ምልክቱ) የሚለው ቃል የህክምና ቃል ሲሆን በመጀመሪያ ሲግመንድ ፍሮይድ ንቃተ-ህሊና የሌለውን ስነ-ልቦና ለመግለጽ ቃሉን ተጠቅሞበታል (Xiaotang Lyu፣ 2021፣ 1075)።

ሀዲስ ታሪካዊ ሂስ ባለፈና አሁን በሚታይ ውስብስብ የባህል፣ የፖለቲካና የድርሰቱ አለም ውስጥ በመግባት እውነት ማውጣት ነው። ይህ ማለት በአንድ ስራ ታሪካዊ አውድና በዘመናዊ አንባቢ አንብቦ የመረዳትና የመተርጎም መስተጋብር ላይ ትኩረት ያደርጋል። ሥነጽሁፋዊ ቴክስቶች ታሪካዊ አውዶችን እንደሚቀርጹ ሁሉ ታሪኮችም ሥነጽሁፋዊ ቴክስቶችን ይቀርጻሉ፤

የትኛውም ድርስት በታተመበት፣ባህላዊና ፖለቲካዊ አሰራር እንደሚቀረጽ ሁሉ በተራው ዘመንን የመቅረጽ ሀይል አለው ማለት ነው፡፡

ሀዲስ ታሪካዊ በጸሀፊው ታሪካዊ ሆነ በሀያሲው  ታሪክ ውስጥ ሥነጽሑፍ መጠናት እና መተርጎም አለበት በሚል እሳቤ የተመሰረተ ነው፡፡ ይህን ለማስረዳት የሥነጽሑፍን ድርሰት በጥልቀት ለመረዳት የታሪክ፣የፖለቲካ፣ ግለታሪክና መጽሐፎችን ማንበብ ትልቅ ፋይዳ እንዳለው ሁሉ ታሪክንና ፖለቲካን ይበልጥ ለመረዳትም በዘመኑ የተጻፉ ሥነጽሁፎች ከፍተኛ ሚና አላቸው የሚል መርህ አለው፡፡

የታሪክ ተመራማሪዎች ታሪኩ እንዴት እንደ ተፈጠረ ሲጠይቁ የሀዲስ ታሪካዊ ሂስ ምሁራን ግን በተፈጠሩት ታሪኮች ውስጥ ያለውን ግንኙነት እና በታሪኩ ውስጥ ያለውን ትርጓሜ እንዴት እንደሆነ ይጠይቃሉ፡፡ ለአብዛኛዎቹ ባህላዊ ወይም የቀደመው የታሪክ ተመራማሪዎች፣ ታሪክ ተከታታይ፣ ቀጥተኛ፣ የምክንያት ግንኙነት ያላቸው ክስተቶች ናቸው፡፡  የሀዲስ ታሪክ ተመራማሪዎች፣ በተቃራኒው፣ በጣም መሠረታዊ ከሆኑ የታሪክ እውነታዎች በስተቀር ግልጽ መዳረሻ አለን ብለው አያምኑም፡፡ ትኩረታቸው የታሪክ ጉዳይ ሳይሆን የታሪክ ትርጉም ጉዳይ ነው ( Tyson፣2006 )፡፡

ሀዲስ ታሪካዊ ሂስ በወቅቱ አዲስ ከመሆኑ የተነሳ የሰዎችን ታሪክ ለመመርመር እና ለመለየት አስቸጋሪ ነበር፡፡ አንዳንድ ጊዜ ሀዲስ ታሪካዊነት ሂስ በሶሺዮሎጂ እና በሥነ-ልቦና ወይም በኢኮኖሚክስ ላይ የተመሰረተ ይመስላል፡፡ ነገር ግን በየትኛውም የጥናት መስክ የተገደበ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ሁሉም የአንድ ባህል ክፍሎችን እርስ በርስ ሲቀረጹ ያያል (Ann.B.Dobin፣2012፣177)፡፡

ሀዲስ ታሪካዊ ሂስ ቅርጻውያንን እና መዋቅራውያን የሚከተሉትን ፍልስፍና በመቃወም የተነሳ ሲሆን የአንድን ሥነጽሑፍ ትርጉም ከስራው ብቻ ማግኘት ይቻላል የሚለውን ሃሳብ በመቃወም የአንድን ቴክስት ትርጉም ለማግኘት ብቸኛው መፈለጊያ መንገድ ጽሑፍ ብቻ እንዳልሆነ ለማሳየት የፈለቀ ፅንሰ ሃሳብ ነው፡፡ ሀዲስ ታሪካዊ ሂስ የሚገለጸው በትይዩ የፅሁፍ ንባብ socio-cultural እና ታሪካዊ ሁኔታዎች ላይ ሲሆን co-text ላይ ይመሰርታል፡፡ ሀዲስ ታሪካዊ ሂስ Louis Montrose እንደገለጸው፣ “texuality of history and the historicity of texts”ይመለከታል፡፡ ሀዲስ ታሪካዊነት ሂስ ከተለምዷዊ ታሪካዊ ጥናት በጣም የተለየ ነው፡፡ ምናልባትም መሰረታዊ ግምቶቹን እና መርሆቹን ለማቅረብ በጣም ጥሩው መንገድ

ከሚያውቁት ቀዳሚው ከብሉይ ታሪካዊ ጋር በማነፃፀር መጀመር ነው። የብሉይ ታሪካዊ ተመራማሪዎች በተወሰነ ጊዜ እና ቦታ ላይ የተከሰተውን እውነተኛ ነገር ማግኘት ያሳስባቸዋል። የሰው ልጆች ያለፈ ታሪክን በተቻለ መጠን ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ፤የተከሰተውን ነገር በትክክል መግለፅ እና ተጨባጭ አድርጎ ማቆየት ግባቸው ነበር (Ann.B. Dobin፣2012፣178) ።

የሀዲስ ታሪካዊ ምሁራን የብሉይ ታሪካዊ መርህ እና ዓላማን ይቃወማሉ። ለምሳሌ ማንም ሰው በተወሰነ ጊዜ እና ቦታ ምን እንደተፈጠረ በትክክል ሊያውቅ ይችላል የሚለውን የብሉይ ታሪካዊ መርህ አጥብቀው ይቃወማሉ። ሊታወቅ የሚችለው በቅርፆችና በታሪኮች ውስጥ የተላለፈውን ነው። ታሪክ ትረካ እንጂ ንፁህ ያልተበረዘ የትክክለኛ ምልከታ ስብስብ አይደለም። ስለዚህ ሁሉም ታሪክ በተጨባጭ የሚታወቅ እና የተቀመጠ፤በባህላዊ አውድ የተነቀሰ እና የሚመዘገበው ታሪክ ሥልጣን ያለው ሰው ስለሆነ በርካታ ያልተነገሩ አቅም የሌላቸው ክስተቶችን ይዘነጋል (Ann.B. Dobin፣2012፣178) ።

የታሪክ ተመራማሪዎች በተወሰነ ጊዜ እና ቦታ ላይ የተከሰተውን ነገር ማግኘት ያሳስባቸዋል። ብሉይ ታሪካዊ ኢስ የሰው ልጅ ያለፈውን ታሪክ ያካተቱ ታሪኮች ትክክለኛ ሂሳቡን በተቻለ መጠን በእርግጠኝነት ማረጋገጥ እንደሚችሉ የተከሰተውን ነገር በትክክል መግለጽ ነበር ይቻላል ብለው ያስቡ ነበር። ይህን ሃሳብ Ann.B. Dobin (2012፣178) ሲያስረዱ

> To do so meant maintaining an objective stance, a position of distance from the scene of action that would allow them to see and state the truth about people and events. If they were successful in doing so, they would, by extension, manage to capture the sense of an entire age. They could find the essence of a period, the worldview that would unlock the meaning of that period's literature, art, politics, social behavior, and the rest. In looking at the broad sweep of history, they viewed the narratives as being linked to one another in a causal sequence that, it was assumed, would carry the world forward in a positive, progressive manner.
>
> "ይህን ለማድረግ ተጨባጭ አቋም በመያዝ ከድርጊቱ እና ከሰዎች በመራቅ እውነቱን መመልከት እና መናገር ይቻላል። ይህን በማድረጋቸው የተሳካላቸው

ከሆነ ነገሩን በማራዘም፣ በሁሉም የእድሜ ደረጃ ላይ ያሉትን  ስሜት መያዝ ይችሉ ነበር። የወቅቱን ምንነት፣ የዘመኑን ሥነ-ጽሁፍ፣ ሥነ-ጥበብ፣ ፖለቲካ፣ ማህበራዊ ባህሪ እና የተቀረውን ትርጉም የሚከፍተውን የአለም አተያይ ማግኘት ይችላሉ። ሰፊውን የታሪክ ልህቀት ሲመለከቱ፣ ትረካዎቹ እርስ በእርሳቸው የተቆራኙ እንደሆኑ አድርገው ይመለከቱት የነበረበት ምክንያት ዓለምን በአዎንታዊ፣ ተራማጅ መንገድ ወደፊት እንደሚያራምድ ይገመታል"።

የብሉይ ታሪካዊ ንድፈ ሃሳብ ከታሪካዊነት ጽንሰ-ሀሳብ ጋር እጅጉን ይዛመዳል። እሱም ታሪክ የሰው ልጅ ልምድ ወሳኝ አካል ነው የሚለውን እምነት ያመለክታል።  በዚህ አመለካከት መሠረት ታሪክ ያለፈ ታሪክ ብቻ ሳይሆን ሕይወታችንንና በዙሪያችን ያለውን ዓለም የሚቀርጽ ኃይል ነው። በተጨማሪም የብሉይ ታሪካዊ ሂስ አራማጆች የአንድን ማህበረሰብ ታሪካዊ ክስተት ያለምንም አድሎ እንዳለ ማቅረብ ይቻላል የሚሉ ሲሆን፣ ሀዲስ ታሪካዊ ሃያሲዎች ደግሞ ለአንድ ታሪካዊ ሂስ ተርጓሚው የሚሰጠው ትርጓሜ እንጂ በትክክል የተከሰተውን እውነታ አይደለም ብለው ሀሳብን ይሞግታሉ።

ታሪክ እውነት፣ተጨባጭ እና ፍጹም ነው ብለው ብሉይ ሲያስቡ በሀዲስ ታሪካዊ ግን ታሪክ የፍጹምነትን ደረጃ አያገኝም። ምክንያቱም ታሪክ የትርጉም ጉዳይ ነው። በታሪክ ጸሐፊው ላይ በወቅቱ ያለው ፍልስፈና፣ፖለቲካዊ ጉዳይ፣የራሱ የጸሐፊው አቋም፣ አመለካከት እና በማስረጃነት የሚያገኛቸው ሰነዶች ሁሉ ተጽእኖ ላይ ይጥሉታል። ስለዚህ የጸሐፊው ግላዊ ስሜት ስለሚንፀባረቅበት ታሪክ ፍፁም ሊሆን አይችልም። ይህንን ሃሳብ Tyson(2006፣ 283) ሲገልጹ።

> The first and most important reason for this difficulty, new historicists believe, is the impossibility of objective analysis. Like all human beings, historians live in a particular time and place, and their views of both current and past events are influenced in innumerable conscious and unconscious ways by their own experi- ence within their own culture. Historians may believe they're being objective, but their own views of what is right and wrong, what is civilized and uncivilized, what is important and unimportant,

and the like, will strongly influence the ways in which they interpret events.

"የሀዲስ ታሪካዊ ሂስ ተመራማሪዎች ተጨባጭ የሆነ ትንተና መስጠት የማይቻል እንደሆነ ያምናሉ። እንደማንኛውም ሰው የታሪክ ተመራማሪዎችም በተወሰነ ጊዜ እና ቦታ ላይ ይኖራሉ። ስፍር ቁጥር በሌለው የንቃተ ህሊና እና በማይታወቁ መንገዶች በራሳቸው ሙከራ ይጽፋሉ። ስለዚህ ወቅታዊ እና ያለፉት ክስተቶች የአመለካከት ውጤቶች ጭምር ናቸው። የብሉይ ዘመን ምሁራን ተጨባጭ ናቸው ብለው ያምኑ ይሆናል። ነገር ግን የራሳቸው አመለካከት ትክክልና ስህተት የሆነውን፣ የሰለጠነና ያልሰለጠነውን፣ አስፈላጊ እና አስፈላጊ ያልሆነው እና የመሳሰሉት ነገሮች ክስተቶችን የሚተረጉሙባቸው መንገዶች ላይ ተጽዕኖ ያሳድራሉ"።

የሀዲስ ታሪካዊ ሂስ አራማጆች የሚያምኑት ከብዙ ሀቲቶች ውስጥ ታሪክ አንዱ እና ግላዊ እንደሆነ ነው። ታሪክ ታሪክን በሚኖሩት ማህበረሰቦች ይወሰናል፤ቅርጹንም ይይዛል። ሀዲስ ታሪካዊ ሒስ በአንድ ስራ ታሪካዊ አውድና በዘመናዊ አንባቢ አንብቦ የመረዳትና የመተርጎም መስተጋብር ላይ ትኩረት ያደርጋል። የጽሑፉን ባህላዊ ሁኔታ በመመርመር ለመረዳት ይፈልጋሉ።

Tyson (2006፣284) እንደገለፁት "በሀዲስ ታሪካዊ ድርሰቱ የተመሰረተባቸው መቸቶች፣ ሁኔታዎች... ዙሪያ ያሉ መረጃዎች እኩል ጠቃሚነት ይኖራቸዋል። ምክንያቱም እነዚህ ነገሮች ተደጋጋፊ እና ትርጉም ለማግኘት መሰረታዊ ነጥቦች ናቸው" ይላሉ።ሀዲስ ታሪካዊ የሥነጽሁፍ ሥራ በታሪካዊ እውነታ ላይ ተጽእኖ የማድረግም የመደረግም ሁለቱንም ምርጫዎች የማስተናገድ ሚና አለው። ሀዲስ ታሪካዊ የማንበብና የመረዳት ዘዴ ሲሆን ጽሑፋዊም ሆኑ ጽሑፋዊ ያልሆኑ ነገሮችን ጎን ለጎን የምናነብበትና የምንረዳበት መንገድ ነው። አንድን ሥነጽሑፍ ስንተረጉም ጽሑፉ ወደተፈጠረበት ወይም መነሻ ወደሆነው አውድ ወስዶ መመልከትና መመለስ ብቻም ሳይሆን የሚጠኑ ጥናቶች በሙሉ ግምት ውስጥ የሚገቡት ያለ ሌላ ተጨማሪ ጥናት በአንድ ጽሑፍ ላይ ትርጉም ያለው ነገር እንደማይገኝ በማረጋገጥና በማሳየት ጭምር ነው።

ሀዲስ ታሪካዊ ሂስ ከሌሎች የሥነጽሑፍ ሂስ በተለየ መልኩ ከንድፈ ሃሳብ ምስረታ ላይ ይልቅ ለሥነ-ጽሑፍ ልምምድ የበለጠ ትኩረት ይሰጣል፤ እና ለተለያዩ ውክልናዎች የተለያዩ ሀሳቦች አሉት። ነገር ግን የሀዲስ ታሪካዊ ሊቃውንት አሁንም የሀዲስ ታሪካው ዋና አካል ብለው የሚያምኑት በታሪክ መካከል ያለው ግንኙነት ፣ ጽሑፍ እና በታሪካዊ መካከል ያለው የጋራ ሥነጽሑፋዊ ጽሑፎችን ትኩረት ይሰጣል። ሁሉንም ሊቃውንት የሚያስማማ የጋራ የሀዲስ ታሪካዊ እሳቤዎች በማለት Xiaotang Lyu (2021፣1077) እነዚህን ያስቀምጣሉ።

1. Every expressive act (including literature) is embedded in a network of material practices;
2. Every act of unmasking, critique, and opposition uses the tools it condemns and risks falling prey to the practice it exposes;
3. Literary and non-literary “texts” circulate inseparably;
4. No discourse, imaginative or archival, gives access to unchanging truths nor expresses inalterable human nature;
5. A critical method and language adequate to describe culture under capitalism participate in the economy they describe.

ከላይ ያለው የሀዲስ ታሪካዊ ሂስ ትንተና ተጨባጭ የሆነ እና ቀጣይነት ያለው ታሪክ እንደሌለ ያሳየናል። ታሪክ በጽሑፋዊነት የተሞላ ስለሆነ ያለፈን ጊዜ በትክክል ሊወክል አይችልም። እና በእውነተኛ እና በንጹህ መልክ ለእኛ ይገኛል። እና የሀዲስ ታሪካዊ የታሪክ ትርጓሜ በተወሰነ ደረጃ ከድህረዘመናዊነት ጋር የተዋሃደ ነው። ምንም እንኳን ሀዲስ ታሪካዊነት በሥነ ጽሑፍ ሂስ ዘርፍ ብዙ ተቀባይነት አግኝቶ በተግባር ላይ ቢውልም፣ አሁንም ድክመቶች አሉበት። የተለያዩ ሥነጽሑፋዊ ሂሶች የሥነጽሑፋዊ ስራዎችን ለመረዳት እና ለመተርጎም የተለያዩ መንገዶች ቢኖሩም ሀዲስ ታሪካዊ ሂስ ግን ጽሑፎችን በጥልቅ እንድንተነትን እድል ይሰጣል።

እንደ Stephen Greenblat አተያይ የሀዲስ ሂስ መሰረታዊ ጭብጦች የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው። አንደኛ ሥነጽሑፍ ታሪክ ነው። ማለትም አንድ የሥነጽሑፍ ስራ በመጀመሪያ ከአንድ ሰው አእምሮ ውስጥ የሚፈጠሩ መደበኛ ችግሮችን ለመፍታት ወይም የሆነ ነገር ለማግኘት ተብሎ የተመዘገበ ጉዳይ አይደለም። ከአንድ በላይ በሆኑ ባለ ምጡቅ አእምሮ ባለቸው ሰዎች ቅርጹን የሚይዝ እንጂ። ሥነጽሑፍን ለመረዳትም ትክክለኛው መንገድ ሥነጽሑፍን በፈጠረው ማህበረሰብ እና ባህል ላይ መመስረት ነው።

ሁለተኛ ልክ እንደ ሥነጽሑፍ ሁሉ የሰው ልጅ በራሱ ማህበራዊ ምስርት/ግንብ / ነው፡፡ የማህበረሰብ እና የፖለቲካ ኃይል ፍንጣቂ ክምችት ነው፡፡ ይህ አይነት አረዳድ በእርግጥ በታሪክ ላይ የለም፡፡ የትኛውም ባለታሪክም ይሁን ሐያሲ እሱን ከፈጠረው ማህበረሰብ በላይ ሊገልጽ አይችልም፡፡ የሚገልጸው የሚጽፈው በተገነባበት በራሱ አቅም ልክ ነው፡፡ በራሱ ፍልስፍና በራሱ ሀሳብ ልክ ነገሮችን መግለጽ ይችላል፡፡ አቅሙ ከሚሸከመው በላይ ሊያነሳና ሊጽፍ አይችልም፡፡

ሦስተኛ የሀዲስ ታሪካዊ ሂስ ዋና ዓላማ በአንድ በተወሰነ ጊዜ በጊዜው ስለ እሱ የተጻፈው ጽሑፍ ታሪክ እውነት ስላልሆነ እንደገና በወቅቱ የሚኖሩት ሰዎች ይኖሩትና ይሆኑት የነበረውን አጠቃላይ ሁኔታ መልሶ ማሳየት ነው፡፡ ዛሬ ላይ የወከላቸውን ጽሑፍ በተቃርኖ በመቆም ጽሑፉ ያልያዛቸውን እውነታዎች ቆፍሮ በማውጣት ማሳየት ነው፡፡ ከዚህም በመነሳት እንደ ሀዲስ ታሪካዊ ሐያሲን አተያይ ታሪክ የአንድ ስራ ማረጋገጫ ተጨባጭ ማስረጃ ሆኖ መታየት የለበትም ብለው ያስባሉ፡፡ ሌላኛው የሀዲስ ታሪካዊ ሂስ አቀንቃኝ Louis A. Montrose ደግሞ ሀዲስ ታሪካዊ ሂስን እንዲ ሲሉ ብያኔ ይሰጣሉ፡፡ Xiaotang Lyu (2021፣1077)

> the new historicism as “a reciprocal concern with the historicity of texts and the textuality of history.” The historicity of texts shows us the social and material embedding of all kinds of writing and the historical, social and material embedding of all kinds of reading. And the textuality of history has two aspects of connotations. On one hand, “we can’t get access to a full and authentic past, to a lived material existence which is not mediated by the surviving textual traces of the society in question” and the surviving textual traces are preserved and effaced to some extent. On the other hand, the scholars who profess the humanities are based on their descriptive and interpretive texts used those preserved traces to compose the documents selectively

> “ሀዲስ ታሪካዊ እንደ የጽሑፎችን ታሪካዊነት እና የታሪክን ጽሑፋዊነት በተመለከተ የተገላቢጦሽ አስተሳሰብ አለው፡፡ ይህም የጽሑፎች ታሪካዊነት ፣የሁሉም አይነት ጽሑፎችን ማህበረሰባዊ እና ቁሳዊ ጉዳዮችን መካተት እና የሁሉም አይነት ንባብ ደግሞ ታሪካዊ ፣ማህበራዊ እና ቁሳዊ ጉዳዮችን መካተቱን ያሳየናል፡፡ የታሪክ ጽሑፋዊነት ደግሞ ሁለት ትርጓሜዎች አሉት፡፡ አንደኛ “ሙሉ የሆነ እና ትክክለኛ ያለፈ ታሪክ ላይ

ጥያቄ ውስጥ ባለው የሕብረተሰብ ህልውና ውስጥ መድረስ አንችልም። በሕይወት የተረፉት ጽሑፋዊ ዱካዎች ወይም መረጃዎችም በተወሰነ ደረጃ ጠፍተዋል። በሌላ በኩል ደግሞ ሊቃውንት ሰነዶችን ሲመርጡ ተጨባጭ እና ትርጓሜዎች ላይ የተመሰረቱ ናቸው ብለው አይናገሩም።

Louis A. Montrose እንዳለው ታሪክ ዓላማው ተጨባጭ የእውነታ ስብስብ መሆን አይደለም። ነገር ግን የተፀነሱ እና የተተረጎሙ ጽሑፎች ነው። በተጨማሪም፣ ሁሉም ጽሑፎች መሰረት ንግግር ነው፤ እሱም የአንድን ዘመን የቃል አሠራሮች ያቀፈ ነው። ባህላዊ እና ታሪካዊ ሁኔታዎችም በሥነ ጽሑፍ ውስጥ ያለውን እውነታ በመረዳት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ያሳድራሉ። ደራሲያን በስራዎቻቸው ውስጥ ያካተቱትን ጭብጥ፣ ገፀ-ባህሪያት እና የትረካ አወቃቀሮችን ሲቀርጹ ባህላዊ አውድ፣ በአመለካከታቸው እና በስራቸው ውስጥ ለማንሳት በመረጡት ጭብጦች ላይ ተጽእኖ ያደርጋሉ። በተጨማሪም በታሪካዊው አውድ የታሪኩ ክስተቶች የተከሰቱበትን ዳራ ያቀርባሉ። ይህም የወቅቱን ማህበረ-ፖለቲካዊ ፣ የቴክኖሎጂ እድገቶችን እና የህብረተሰቡን ባህል እና እሴቶችን ይጨምራል። እውነታዊነት አንባቢያን ገፀ ባህሪያቱን እና ሁነቶችን እንዲገነዘቡ ስለሚረዳቸው ታሪካዊ አውድ የስነ-ጽሁፍ ስራን ትርጉም በእጅጉ ይነካዋል። ይሄንን ሃሳብ Grace Fleming (2019) https://www.thoughtco.com/what-is-historical-context-1857069

> Historical context is an important part of life and literature, and without it, memories, stories, and characters have less meaning. Historical context deals with the details that surround an occurrence. In more technical terms, historical context refers to the social, religious, economic, and political conditions that existed during a certain time and place. Basically, it's all the details of the time and place in which a situation occurs, and those details are what enable us to interpret and analyze works or events of the past, or even the future, rather than merely judge them by contemporary standards.
>
> "ታሪካዊ አውድ ለሥነጽሑፍ እና ለህይወት አስፈላጊ አካል ነው፤ ትዝታዎች, ታሪኮች እና ገፀ ባህሪያት ከታሪካዊ አውድ ውጪ ያነሰ ትርጉም አላቸው።

ታሪካዊ አውድ በአንድ ክስተት ዙሪያ ያሉትን ዝርዝሮች ይመለከታል። ታሪካዊ አውድ በቴክኒካል አገላለጽ ይበልጥ የሚያመለክተው በተወሰነ ጊዜና ቦታ የነበሩትን ማህበራዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ሁኔታዎችን ነው። በመሰረቱ፣ አንድ ሁኔታ የተከሰተበት ጊዜ እና ቦታ ሁሉም ዝርዝሮች ናቸው፤ እነዚህ ዝርዝሮች አሁን ባለው ጉዳይ ብቻ ከማተኮር ይልቅ ያለፈውን፣ አልፎ ተርፎም የወደፊቱን ስራዎችን ወይም ክስተቶችን ለመተርጎም እና ለመተንተን የሚያስችሉን ናቸው"።

ታሪካዊ አውድ ለሥነ-ጽሑፍ ሥራዎች መሰረት ሆኖ ያገለግላል። የወቅቱን ሶሺዮፖለቲካዊ፣ ቴክኖሎጅያዊ፣ ባህላዊ እና ስነ-ምግባራዊ ገጽታን በመረዳት አንባቢዎች የጽሑፉን ሁነቶች እና የገፀ-ባህሪያትን ሙሉ ጠቀሜታ መረዳት ይችላሉ። ይህ የማስተዋል ጥልቀት ከፊት ለፊት ከተነገረው በላይ የሆነ ትርጉም ያለው ትርጓሜ እንዲኖር ያስችላል።

በ18ኛው ክ/ዘ የሁለቱ በአንድ ድንበር መካለል ሳይሆን በትረካ ውስጥ ከእውነታ ጋር ያለው ግኝኙነት አሳሳቢነት ትኩረት አጊንቶ ነበር። በባህሪው የታሪክ እውቀት እንደ ዘውግ ሁለቱንም የመለያየት አደጋን በመሳየት ችግር ይፈጥራል። ይህ ችግር በብዙ ዘመናዊ ሥነጽሑፋዊ ንድፈ ሃሳብ እና ፍልስፍና ከ"Hayden White" እስከ "Paul Veyne" ትልቅ ችግር ፈጥራል። የኂለኛው ታሪክ ሲጠራ "እውነተኛ ልቦለድ" ይባላል፤ይህ አጠራር ሁለቱ ዘውጎች የተጋሩትን ነገር እያሳየ ነው። ይህም ማለት ሁለቱም የተመሳሳይ ንግግር ቅደም ተከተል አካል ናቸው። ደራሲያን እና የታሪክ ተመራማሪዎች አንዳቸው የሌላውን ስራ በተደጋጋሚ ሲጠቀሙ ይስተዋላሉ። ነገር ግን ታሪካዊ ክስተቶችን ፣ ገፀባህሪያትን እና አንባቢዎችን ባሳተፈ እና ያለፈውን ጊዜ ትርጉም እውነታዎችን በሚያስተላልፍ መልኩ ማቅረብ አዳጋች ነበር (Currie፣ 2013፣78)።

በ19ኛው ክ/ዘ ከ"Ranke's scientific history" በፊት ሥነጽሑፍ እና ታሪክ የአንድ ዛፍ ቅርንጫፎች ተደርገው ይቆጠሩ ነበር። ከዚያ መለያየት መጣ በመለያየታቸው ዛሬ ላይ የተለያዩ የሥነጽሑፍ እና የታሪክ ጥናቶችን አስገኝተዋል። ምንም እንኳን እውነተኛ ልቦለድን እና የ Rankean historicism ቢጋሩም። በተጨማሪም በእውነታ ዙሪያ ለመፃፍ ብዙ ተመሳሳይ እምነቶች እና አጋጣሚዎች አሏቸው። አሁን እየተገዳደረ ያለው የሥነጽሑፍ እና ታሪካዊነት የድህረ ዘመናዊ ፅንሰ ሀሳብ፣ሥነ-ጥበብ፣የቅርብ ጊዜ የታሪክ ንባቦች እና ልብ ወለዶች ሁለቱ

የአጻጻፍ ስልቶች ከሚጋሩት ነገር የበለጠ እንዴት እንደሚለያዩ ትኩረት ተሰቶታል (Currie፣ 2013፣72)።

ታሪክ የአንድ ነገር ማጣቀሻ ሳይሆን በራሱ ፅንሰ ሃሳብ ነው፤ ያለፈው ወይም እንደ ጊዜያዊ ሂደት ያለ ነገር ስለሆነ ከቁስ ይልቅ ፅንሰ ሃሳብ መሆኑን ያስረዳል። ያለፈው ወይም ያለው ነገር ምን ነበር? በዚያ ቦታ መደረጉ እንቆቅልሽ ሆኖ ሊቀርም መፍትሔ ሊሆንም ይችላል። የተገመተ ሃሳብ ወይም ግምታዊ ባህርይው ይሆናል። ነገር ግን ግምታዊ ወይም አጋጣሚ መሆን ያለበት ልቦለድ ነው። ይህም ማለት አጋጣሚው ወይም ግምቱ  የተከሰተው ምን ሊሆን እንደሚችል? ወይም የሆነ ጊዜ ምን ሊከሰት ይችላል?፣በአንድ ቦታ፣ባሁን ጊዜ፣ ባለፈ ጊዜ እና ወደፊት ጊዜ (Hayden፣2014፣x)።

የታሪክ ተመራማሪዎች በጥንቃቄ መረጃን በማሰባሰብ እና በመተንተን ያለፈውን አጠቃላይ እይታ ለመገንባት መሞከራቸው  በጠንካራ ዘዴዎቸው ሲሆን አንዳንዴም እርስ በርሱ የሚቃረኑ ማስረጃዎችን በማጣራት ወጥ የሆነ ታሪካዊ ትረካ ላይ ለመድረስ ከባድ ስራ ይሆናል።  የታሪክ ምሁራን ሲነሱ ቀዳሚው Hayden White ነው። ስለ እሱ Herman Paul (2011) እንደሚከተለው ገልጸዋል

> Hayden White is a controversial figure in the world of history. Study any textbook on the theory and philosophy of history, and you will be assured that his 1973 book *Metahistory* marked a revolutionary turning point in historical theory. It marked what came to be known as the 'linguistic turn' in historical theory, and has inspired legions of acolytes whose reverence for the master at times verges on embarrassing. Yet at the same time his influence on the actual practice of history and historical writing has been virtually zero. As Paul puts it in his introduction, Dominic LaCapra's paean that 'no-one writing history in this country has done more to wake historians from their dogmatic slumber than Hayden White.

> “ሃይደን ዋይት በታሪክ አለም ውስጥ አከራካሪ ሰው ነው። ስለ ታሪክ ንድፈ ሃሳብ እና ፍልስፍና ማንኛውንም የመማሪያ መጽሃፍ እና እ.ኤ.አ. በ 1973 የፃፈው *ሜታሂስተሪ* በታሪካዊ ንድፈ-ሀሳብ ውስጥ አብዮታዊ ለውጥ እንዳመጣ ማረጋገጫ ነው። በታሪካዊ ፅንሰ-ሀሳብ ውስጥ ‘’linguistic turn” ተብሎ የሚታወቀውን ምልክት በመጠቀም አንዳንድ ጊዜ ለጌታው ያላቸውን አክብሮት ወደ መተው የሚወስዱትን ክስተቶች ለማሳየት ተጠቅሞበታል። ሆኖም ግን በተመሳሳይ ጊዜ በታሪክ እና በታሪክ አጻጻፍ ትክክለኛ አሠራር ላይ ያለው ተጽእኖ ዜሮ ነው። Paul በመግቢያው ላይ እንዳስቀመጠው ‘Dominic LaCapra’s paean’ በዚህች አገር ታሪክን የሚጽፍ የታሪክ ተመራማሪ ከሃይደን ዋይት የበለጠ ከዶግማ ለማላቀቅ ጥረት አላደረገም” ።

Hayden White በሥነ ጽሑፍ እና በታሪክ መካከል ያለውን ግንኙነት በማጥናት ሙሉ የህይወት ዘመኑን አበርክቷል ማለት ይቻላል። የሀዲስ ታሪካዊ ሂስ ሊቅ መሆኑን በፍጹም ባይቀበልም፣ የታሪክ አካዳሚያዊ ሀሳቦቹ ግን ከሀዲስ ታሪካዊ ሂስ ጋር ተመሳሳይ ናቸው። በሜታሂስቶሪ ንድፈ ሃሳብ ላይ ያደረገው ስልታዊ ምርምር በሀዲስ ታሪካዊ ሂስ ንድፈ ሃሳብ ላይ አስተዋጽኦ አድርጓል። ታሪክ የትረካ ዘገባ ፣ የማይቀር ምሳሌያዊ እና ፈጠራዊ ነው። ታሪክ ለእኛ ተወክሏል እና በንግግራዊ ትረካ ምክንያት ትክክለኛውን ያለፈውን ማግኘት አይቻልም። ታሪክ በእኛ ስለተወከለ እና በንግግራዊ ትረካ ምክንያት ትክክለኛውን ማለትም ተጨባጭ የሆነውን ያለፈውን ክስተት ማግኘት አይቻልም። የሥነጽሑፋዊ ጽሑፎች ግንኙነት ፣ባህላዊ እና ታሪካዊ አውድ ብቻ ሳይሆን ሥነጽሑፋዊ ጽሑፎች እና የቀድሞ ጽሑፎችም እንዲሁ እርስ በርስ የተያያዙ ናቸው የሚል አመለካከትን ይይዛል።

Hayden White (2014፣5) “የSebald መጽሐፍ “real- world” ላይ ታሪክ እና ሰነድ “እውነታን” ከልቦለድ ስለሚመድበው ተጨባጭ ለማድረግ አስቸጋሪ ያደርገዋል” በማለት ሁለቱ ፅንሰ ሃሳቦች እንደሚወሳሰቡ ያሳየናል። ሥነጽሑፋዊ አፃፃፍ በታሪክና በልብወድ መካከል ያለው ግንኙነት እርስ በእርስ የሚደጋገፉ እና የሚቃረኑ ስለሆነ ልዩነት ለማጣራት እና የበለጠ እምነትን ማግኘት ነው። በዘመናዊው ዘመን እና ከዛ በፊት በነበሩ ድርሰቶች ውስጥ ድርሰቱና ደራሲው የፈጣሪ እና የተፈጣሪ ዓይነት ግንኙነት ነበር ያላቸው። ፀደይ ወንድሙ (2007፣5) ይህን ሃሳብ ሲያስረዱ

“ይህንንም ሲያደርጉ ምክንያታቸው በድርሰቱ ዓለም ውስጥ ያለው እውነታ እና እውነታ ቅንብር ወይም ሰው ሰራሽ መሆኑን ማሳየት እና በዚህም እውነታ እና በልብወለድ መካከል ያለውን ግንኙነት ለማጠየቅ ነው። እንደ ድህረ ዘመናዊ አስተሳሰብ በልብ ወለድ እና በእውነታ መካከል ያለው ድንበር ስስ ነው። እውነታው ልብ ወለድ ለመሆን፣ልብ ወለዱ እውነታ ለመሆን ይችላሉ። ማንኛውም እውነት ልብ ወለድ ነው። ይህም ማለት ተጨባጭነት የለውም ወይም በገሃዱ ዓለም አልተከሰተም ለማለት ሳይሆን፣ ማንኛውም ዓይነት እውነታ በአንድ አካል የተቀናበረ መሆኑን ለማሳየት ነው”።

ሥነጽሑፍ በቃላት ኃይል  ጥልቅ ትርጉሞችን የማስተላለፍ፣ በሀገሮች ላይ ተጽእኖ የማሳደር እና እንቅስቃሴዎችን የመፍጠር፣ ሰዎችን የማነሳሳት አቅም አለው። የሥነጽሑፍ እና የታሪክ ጥናት ስለ ሰው ልጅ ሁኔታ እና በአለም ውስጥ ያለን ቦታ ያለንን ግንዛቤ ያሳድጋል። ሥነጽሑፍ እና ታሪክ በተለያዩ ጊዜያት እየሰፉ እና እየተለጠጡ የሚሄዱ ዘውግ በመሆናቸው አንዱ ባንዱ ድንበር ውስጥ ተካሏል። የታሪክ አፃፃፍ ቀስ በቀስ በትረካ መልክ ያለፈውን የሚወክል ፤ በጣም የተለመደ እና ወደ ሥነጽሑፋዊ ያመራል። ይህ ማለት ግን ክስተቶችን ፈፅሞ እንዳልተከሰቱ ያደርጋል ማለት አይደለም። በ 20 ኛው ክፍለ ዘመን የታሪክ ማስረጃዎች መስፋፋት የታሪክ ተመራማሪዎች የቃል ወጎችን ፣ የአርኪኦሎጂ ግኝቶችን ፣ እንደ የግል ሰነዶች እና የአካባቢ መዛግብትን የመሳሰሉ ባህላዊ ያልሆኑ የመረጃ ምንጮችንም ጨምሮ ሰፋ ያሉ ቁሳቁሶችን እንዲመረምሩ አስችሏቸዋል።

ሥነጽሑፍ አንድ ሰው ወደ ኋላ እንዲመለስ እና በምድር ላይ ስላለው ሕይወት ከእርሱ በፊት ከተጓዙት ሰዎች እንዲማር ያስችላል። ታሪክ በሚመዘገብባቸው መንገዶች በጽሑፍ ወይም በንግግር መልክ እንማራለን። በአጠቃላይ ከታሪክም ሆነ ከሥነጽሑፍ የምንማረው ነገር አለ። ያለፉ ክስተቶች፣ሂደቶች፣ሰዎች፣ተቋማት እና ነገሮች አሁን ላይ ህይወት ያላቸው ነገሮች በሚታዩበት መንገድ ሊታዩ ወይም በቀጥታ ሊታወቁ አይችሉም። ስለዚህ የታሪካዊ እውነትነት በተሳሳተ ቦታ ላይ በሚኖረው ስህተት ተጨባጭ ማድረግ አዳጋች ይሆናል።

ሥነጽሑፍ ያለፈውን ጊዜ እንድንመለከተ እድል እና  ከእኛ በፊት ከነበሩት ሰዎች ልምድ እድንወስድ ያስችለናል። ታሪክ ደግሞ በጽሑፍ ሰነዶችም ሆነ በቃል ትረካዎች  ግንዛቤ ይሰጣል። ሁለቱም ታሪክ እና ሥነጽሑፍ ስላለፉት ክስተቶች፣ ግለሰቦች፣ ማህበረሰቦች እና ሁነቶች ጠቃሚ መረጃን ይሰጣሉ። ነገር ግን፣ ቀጥተኛ ምልከታ ባለው የተፈጥሮ ውስንነት እና

በተዛባ አተረጓጎም ምክንያት ይህንን መረጃ ማግኘት ፈታኝ ነው። ታሪካዊ እውነት በአሁኑ ጊዜ የገሀዱን ዓለም ሰዎች የመመልከት ያህል ቀጥተኛ አይደለም። ምክንያቱም የተሳሳቱ አመለካከቶች፣ ስህተቶች እና አድልዎዎች ወደ ታሪካዊ ዘገባዎች ዘልቀው ሊገቡ ይችላሉ፤ ይህም የሁኔታዎችን ትክክለኛ አካሄድ ለማወቅ አስቸጋሪ ያደርገዋል።

ጸደይ ወንድሙ (2007፣5) "እውነታ ከድርሰት እኩል ፈጠራ የሚሆነው በገሃዱ ዓለም ውስጥ ያለምንም ብከላ ቁጭ ብሎ ስለማይገኝ፣ በጊዜ ብዛት ሊቀየር ስለሚችል፣ሁሉም እኩል የሚስማማበት ስለማይሆን ነው" ይላሉ። ከዚህ ሃሳብ በመነሳት ሁሉንም የሚያስማማ እውነታ የለም፣እውነታ የጋራ ስምምነት ነው የሚል መደምደሚያ ላይ መድረስ ይቻላል። በታሪክ እና በሥነጽሑፍ መካከል ያለው ግንኙነት በሁለቱም መካከል የሚገኝ በጽሑፋዊ ዲስኮር፣ታሪክ አጻጻፍ፣ስለ ታሪክ የተጻፉ እና ምናባዊ ጽሑፎችn መጻፍ ነው። ምክንያቱም የታሪክ አጻጻፍ ከሥነጥበባት ዘውግ ወይም ክፍል ጋር የተያያዘ የአጻጻፍ ስልት ነው።

## 2.2. የተዛማጅ ጽሑፍ ቅኝት

ከእዚህ ጥናት ጋር ቅርበት ያላቸው ጥናታዊ ጽሑፎች ሲቃኙ አካሔዱ ሁለት አቅጣጫን የተከተለ ነበር፡፡ የመጀመሪያው በሀገር ውስጥ ለጥናቱ የመረጥኳቸው ንድፈ ሃሳቦችን በመጠቀም የተጠኑ ጥናቶችን መፈተሽ እና በመረጥኳቸው ሁለቱ ልቦለድ ላይ የተደረገ ጥናት እንዳለ መቃኘት ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ከሀገር ውጪ በጥናቱ ጥቅም ላይ የዋሉ ንድፈ ሃሳቦችን በመጠቀም የተሰሩ ጥናቶችን መፈተሽ ነው፡፡

### 2.2.1.ከሀገር ውስጥ የተፈተሹ ጥናቶች

ባደረኩት ቅኝት የደራሲ ሀብታሙ አለባቸው ሁሉም መጽሐፉት ተጠንተው አልተመለከትኩም፡፡ ለእዚህ ጥናት የተመረጡት ሁለቱ (*የሱፍ አበባ* እና *የቄሳር እንባ*) መጽሐፍት ላይ የተካሄደ ጥናት የለም ወይም በእኔ የፍተሻ ጥግ አልተመለከትኩም፡፡ ነገር ግን በሁለቱም ልቦለድ ላይ የተካሄደ አጭር ሂስ በፍተሻዬ ወቅተ ተመልክቻለሁ፡፡

በ*የሱፍ አባባ* ላይ የተካሄደው አጭር ሂስ ሲሆን በሂሱ ላይ የሚነሱ ጥያቄዎች እና እይታዎች ይህ ጥናት በሰፊውና እና በተጨባጭ የሚተነትን በመሆኑ በከፊልም ቢሆን ይመሳሰላሉ ማለት ይቻላል፡፡ በሂሱ ላይ በ*የሱፍ አበባ* ላይ ደራሲው ያነሳቸው ጉዳዮች እውነት ቢሆኑም እንኳን ተዓማኒነት የላቸው በማለት ያሔሳል፡፡ የደራሲው የፈጠራ ስራዎች እንጂ የኢሕአፓ እውነተኛ ታሪክን እንዳልጻፈ እና የተጻፈውም የኢሕአፓ ታሪክ ሳይሆን የደራሲው ፈጠራ እንደሆነ ለማሳይት ይሞክራል፡፡ ይህ ሂስ ከሚደረገው ጥናት ሰፊ ልዩነት እንዳለው ግልፅ ነው፡፡ ይህ ጥናት በሁለቱ መጽሐፍት ላይ የፈጠራና የእውነታ ውህደትን ተንትኖ ለማሳየት ንድፈ ሃሳቦችን እና የተለያዩ ለጥናቱ ግብዓት የሚሆኑ ቴክስቶችን በመጠቀም ሰፊ እና ጥልቅ ትንትናን ይሰጣል፡፡

https://tesfabelaynehh.blogspot.com ላይ የተቀመጠው *ዕይታ የቄሳር እንባ* እና *አውሮራ* የተሰኘው መጻሕፍት ላይ የተካሄደ ቢሆንም *የቄሳር እንባ* ደግሞ ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ የሚካሄድበት መጽሐፍ በመሆኑ ተመልክቼዋለሁ፡፡ ዕይታው በመጽሐፉ ጭብጥ ዙሪያ ያተኮረ ሲሆን *"የ‹‹ቄሳር እንባ› ለመንግሥቱ ኃይለማርያም ‹‹ትግላችን›› መጽሐፍ የተጻፈ ምላሽ ይመስለኛል፡፡ ‹‹ትግላችን››ን አንብቦ የተናደደ ሰው ሊጽፈው የሚችለው፤ በልብ ወለድ አጻጻፍ መልክ የተጻፈ፤ ከ1966 አብዮት ወዲህ የተከሰተውን የትውልድ መላሸቅ፤ የሕብረተሰብ*

ዝግመት እና የአገር ውድቀት- በ"ልግመተ ኢትዮጵያ" ስያሜነት የተተየበ ጽሑፍ ነው" በማለት አስቀምጧል። በአጠቃላይ የመጽሐፉን ጭብጥ እና ለደራሲው አድንቆት የተገለፀበት ጽሑፍ በመሆኑ ከእዚህ ጥናት ጋር የሚያዛምድ ግንንኙነት የለውም።

በአጥኚዋ የፈጠራና የእውነታ ውህደት *ከደንቢያ ጎንደር እስከ ዋሽግተን ዲሲ* በሚል ርዕስ በ2013 ዓ.ም ለመጀመሪያ ድግሪ ሚሟያነት የተሰራ ጥናት በተዛማጅ ጽሑፍ ቅኝት ወቅት ተፈትሿል። ይህ ጥናት ከሚካሄደው ጥናት ጋር ከተመሳስሎው ይልቅ ልዩነቱ ሰፊ ነው። ጥናቱ ምንም ዓይነት ንድፈ ሃሳባዊ ማዕቀፍ የሌለው እና የእውነታና ፈጠራ ውህደት እንዴት የሚለውን የሚለውን የማይመልስ (የማያሳይ) ነው። ይህ ጥናተ ደግሞ ይህን ክፍተት ለመሙላት ይሞክራል። ከቀድሞው ጥናተ በተለየ መልኩ የፈጠራ እና የእውነታ ውህደትን ተንትኖ ለማሳየት ሀዲስ ታሪካዊ ሂስን እና የድህረ ዘመናዊነት መገላጫዎችን በመጠቀም ይተነትናል።

በንድፈ ሃሳብ ደረጃ ድህረ ዘመናዊነትን እና ሀዲስ ታሪካዊ ንድፈ ሃሳቦብን በማጣመር የተሰሩ ጥናቶችን ለመቃኘት ባደረኩት ሙከራ ማግኘት አልቻልኩም። ሀዲስ ታሪካዊ ንድፈ ሃሳብን በመጠቀም የተሰራ ጥናት መመልከት ወይም ማግኘት የቻልኩት በዶክተር አንተነህ አወቀ ዳግም ንባብ በአልወለድም በሚል ርዕስ በ2007 ዓ.ም በባህርዳር ዩኒቨርስቲ የአማርኛ ቋንቋና የባህል ዘርፎች በሶስተኛው አገር አቀፍ ዐውደ ጥናት ላይ ቀርቦ የተሻሻለውን ነው። ይህ ጥናት በደራሲ አቤ ጉበኛ *አልወለድም* ላይ ትኩረቱን ያደረገ ሲሆን ሀዲስ ታሪካዊ ንድፈ ሃሳብን በመጠቀም ትንተናው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቁምታ ላይ በማረፉ ከሚደረገው ጥናት ጋር ተመሳስሎ የለውም።

የድህረ ዘመናዊነት ንድፈ ሃሳብን በመጠቀም የተጠኑ ጥናቶች የመጀመሪያው የጸደይ ወንድሙ ሲሆን "Space time Realities in Ethiopian postmodernist Literature convergence of postmodernist Literaty Theory, physics and Mystoicism" በሚል ርዕስ እ.አ.አ. በ2015 ለውጪ ቋንቋዎችና *ሥነጽሑፍ* ትምህርት ክፍል ለዶክትሬት ዲግሪ ለማማያነት የቀረበ ሲሆን ጸደይ ከደራሲ ስብሀት ገ/እግዚአብሔር ስራዎች መካከል "ከአምስት ስድስት ሰባት" "ተከታትለው ሸው ወደ ቢሾፍቱ" እና "ለገዳዲ"፣ አጋፋሪ እንደሻው" እና "ስምንተኛው ጌታ"፤ ከደራሲ አዳም ረታ ስራዎች መካከልም "ግራጫ ቃጭሎች" እና "እቴሜቴ ሎሚ ሽታ"፤ ከደራሲ አለማየሁ ገላጋይ "ቅበላ" እንዲሁም ከደራሲ ኦታሞ ፐልቶ "ኤላን ፍለጋ" ("የአዞ ኮሌጅ") እና "የሲሳይ ልጆች" ("ኔክሮስና ኔንትሮስ") በተሰኙ የልቦለድ *ሥራዎች* ላይ

ጥናቷን አድርጋለች። ሙሉውን ጥናቷን ለማግኘት ያደረኩት ሙከራ ባለመሳካቱ ምክንያት የቃኘሁት ብሌን፣ ገጽ 8፣ ቁጥር 2 (ነሐሴ 2007 ዓ.ም.) ከታተመው እትም "ድህረ- ዘመናዊ የሥነጽሑፍ መገለጫዎች በግራጫ ቃጭሎች ውስጥ" በሚል ርዕስ የቀረበውን ትንታኔ ብቻ ነው። እሱን መሠረት በማድረግም ጥናቱ ከእኔ ጥናት ጋር ካለው ተመሳስሎ ይልቅ ልዩነቱ ሰፊ ነው ማለት እችላለሁ።

በመሆኑም ጸደይ ሥራዎቹን የተነተኑት ከድህረ ዘመናዊነት የሥነጽሑፍ መገለጫዎች መካከል፣ እንበለ ልቦለድ፣ በቀጣዩ በር በኩል የሚገባበት ዓለም (Wolrd Next- door) ፣ በቋንቋና በእውነታ መካከል ያለው ግንኙነት እና "ሁሉም ነገር ፅሁፍ (text) ነው" በተሰኙት ጽንሰ ሃሳቦች ሰፊና ትልቅ የሆነ ትንታኔዎችን በመስጠት ነው። በመሆኑም ይህ ጥናት ከጸደይ ወንድሙ ጥናታዊ ፅሑፍ እንበለ ልብወለድ ፅንሰ ሃሳብን በመፍታታት ሲመሳሰል ሌሎቹ መገለጫዎችን በጸደይ ጥናት ያልተነሱ በመሆናቸው እና በዋናነት ደግሞ ጥናቱ ከተነሳበት ዓላማ አንፃር ልዩነታቸው ይሰፋል።

የነፃነት ማስረሻ ጥናት "የድህረ- ዘመናዊነት የስነ- ጽሁፍ መገለጫዎች በ "የስንብት ቀለማት" በሚል ርዕስ በ 2010 ዓ.ም ለሁለተኛ ድግሪ ማማያነት የተሰራ ሲሆን ከድህረ ዘመናዊነት ንድፈ ሃሳብ በመጠቀም እና የድህረ ዘመናዊነት መገለጫዎችን በማብራራት ያብራራል። ከዚህ ጥናት የሚመሳሰልበት ከድህረ ዘመናዊ መገለጫዎች ውስጥ የፈጠራና የእውነታ ውህደትን በማንሳቱ ሲሆን የሚለይበት ምክንያት ሀዲስ ታሪካዊ ንድፈ ሃሳብን በመጠቀም የፈጠራና የእውነታ ውህድትን ማሳየት ትኩረቱ ሲሆን የነጻነት ጥናት ደግሞ ድህረ ዘመናዊ ንድፈ ሃሳብን ብቻ በመጠቀም *በስንብት ቀለማት* ላይ የተከሰቱትን የድህረ ዘመናዊ መገለጫዎችን መግለጥ ነው።

የምስራቅ ጠና "Postmodernism in Selected Ethiopian Diasporic Novels in English" በሚል ርዕስ እንደ እ.አ.አ በ2019 አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለውጪ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል ለዶክትሬት ዲግሪ ለማማያነት የቀረበ ሲሆን ትኩረቱ በእንግሊዘኛ የተፃፉ የተመረጡ የዲያስቦራ ልቦለዶችን በድህረ ዘመናዊ ባህርይ እና የድህረ ዘመናዊነት መገለጫዎችን በመጠቀም መፈተሽ ነው። ከእኔ ጥናት የሚለያይበት መንገዱ ሰፊ ነው። በዋናነት የምስራቅ ጥናት በተመረጡ ልቦለዶች ውስጥ የተነሱ የድህረ ዘመናዊ ጉዳዮችን ያደምቃል፣ በተመረጡት ልቦለዶች ውስጥ ጊዜያዊ እና ውስጣዊ የሆኑ የትረካ ጦርነቶችን

ይዳስሳል። የእኔ ጥናት ደግሞ በልብወለድና በታሪክ መካከል ድንበር የናዱ ፍሬ ነገሮችን ይዳስሳል፤ የፈጠራና የእውነታ ውህደትን ተንትኖ ያሳያል።

## 2.2.2.ከሀገር ውጪ የተሬተሹ ጥናቶች

"Fact and Fiction in Autoconfession: A Theoretical Confrontation" በሚል ርዕስ በ2021 በAgron Y. Gashi የተሰራ ጥናታዊ ፅሑፍ ሲሆን ትኩረቱ በራስ ኑዛዜ ውስጥ በልብ ወለድ እና በእውነታ መካከል ያለው የንድፈ ሃሳባዊ ግጭት የሚካሄደው በግለ-ባዮግራፊ አከባቢ እንደሆነ መመርመር እና ፅንሰ ሃሳቦቹን በወቅቱ ግጥሞች ላይ መዳሰስ ነው። የGashi ጽሁፍ የህይወት ታሪክ ከስነፅሁፍ ዘውግ እንዴት እንደተሻሻለ ለመፈተሽ ወሳኝ ምሳሌዎችን እና ታሪካዊ አመለካከቶችን ሳይጠቀም ብዙ ባህላዊ ልማዶችን፣ የስደት፣ የማንነት፣ የአሰቃቂ ሁኔታ እና የኢንተርኔት ራስን አቀራረብን ጨምሮ ለመፈተሽ ሞክሯል። የሕይወት ታሪክን በደራሲው ፣ በተራኪው እና እየተብራራ ባለው ገፀ ባህሪ መካከል እንደ ተቋማዊ የግንኙነት ተግባር አድርጎ የሚመለከተውን "autobiographical pact" ጽንሰ-ሀሳብ እና ይህ ስምምነት በዘመናዊው ደራሲ ተግባር እና በመካከለኛው መፈጠር እንዴት ተጽዕኖ እንደሚያሳድር ያብራራል። ይህ ጥናት ከእኔ ጥናት የሚለየው በትኩረት ሲሆን የእኔ ጥናት በሀብታሙ አለባቸው የሱፍ አበባ እና የቄሳር እንባ የተሰኙ መፃሕፍት ላይ የተገለፁ ታሪካዊ እውነታዎች እና የደራሲው ፈጠራ መዋሃዳቸውን ተንተኖ ማሳየት ነው። በተጨማሪም ጥናቱ ወደ ግለ ባዮግራፊ ፅንሰ ሃሳብ ያዘነበለ በመሆኑም እኔ ከማካሂደው ጥናት በሰፊው ይለያል። ነገር ግን የእውነታ እና የልቦለድ(የፈጠራ) መካከል ያለውን ድንበር መፈተሽ ሁለቱም ጥናቶች የሚጋሩት በመሆኑ ይመሳሰላሉ።

"Historiographic Metafiction as a Postcolonial Narrative Strategy in Michael Ondaatje's Warlight" በሚል ርዕስ በ2020 በ Dirk van Rens ለEnglish Language and Culture School of Humanities University of Eastern Finland ለሁለተኛ ድግሪ ማማያነት የቀረበ ጥናት ሲሆን ትኩረቱ "Michael Ondaatje" በምን ያህል መጠን historiographic metafiction በመጠቀም ከድህረ ቅኝ ግዛት አንፃር ታሪክን በልቦለዱ ላይ ተጠቅማል የሚለውን መመርመር ነው። ይህ ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር historiographic metafiction ፅንሰ ሃሳብ በመጠቀም እና በታሪክ እና በሥነፅሑፍ መካከል ያለውን ድንበር

በመፈተሽ ይመሳሰላል። ከእኔ ጥናት ከሚለይበት ምክንያት ጥናቱ በግኝ ግዛት የተፃፈ ልብወለድ ላይ ትኩረቱ በማድረጉ እና historiographic metafiction በተፈጥሮው ከፍተኛ የሆነ የ intertextual ባህርይ እንዳለው ለማሳይት በመሞከሩ ነው።

"The Practice of Adaptation: Turning Fact and Fiction into Theatre" በሚል ርዕስ በ2012 በ Janis Balodis ለዶክተሬት ማማየነት በQueensland University of Technology የተሰራ ጥናት ሲሆን ትኩረቱ ፀሀፊያን ነባር ቴክስቶችን ከእውነታ እና ከልብወለድ ጋር በማጣጣም ለቴያትር የሚመች ቅርፅ መፍጠር ወይም ማሳየት ነው። ጥናቱ ከእኔ ጥናት ጋር ከሚገኛኝበት ይልቅ የሚለያይበት መንገድ ሰፊ ነው። እውነታ እና ፈጠራን የሚለው ሃሳብን በመቃኘቱ ከእኔ ጥናት ሃሳብ ጋር ስላመሳሰለው ነው በዚህ ክፍል የተፈተሸው። ከሀገር ውጪ በንድፈ ሃሳብ ደረጃ ከእኔ ጥናት ጋር የሚመሳሰሉ በርካታ ጥናቶች ተካሄደዋል። ነገር ግን በቀጥታ ከእኔ ጥናት ጋር የሚመሳሰል ጥናት ተካሂዶ አልተመለከትኩ።

# ምዕራፍ ሦስት

## ትንተና

ይህ ምዕራፍ ለጥናት የመረጥኳቸውን የሀብታሙ አለባቸው *የሱፍ አበባ* እና *የቁሳር እንባ* ልቦለዶች የፈጠራ እና የእውነታ ውህደትን ለማሳየት በሀዲስ ታሪካዊ ንባባ አማካኝነተ የተነተንኩበት ነው። በዚህ ክፍል አህጽሮተ ልቦለድ ፣ የሀዲስ ታሪካዊ ትንተና በየሱፍ አበባ እና በቁሳር እንባ ፣ የፈጠራ እና የእውነታ ቅይጥ ፣ የማህበራዊ እውነታ እና የፈጠራ ውህደት በሚሉ ንዑሳን ርዕሶች ከልቦለዶቹ ማሳያ ቅንጭብ ሃሳቦች በመውሰድ ተተንትነውበታል።

## 3.1. አህጽሮተ ልብወለድ

በደራሲ ሀብታሙ አለባቸው የተደረሰው *የቁሳር እንባ* ልቦለድ በዚህ ጥናት ጥቅም ላይ የዋለው በ2013 ለንባብ የበቃው አስረኛ እትም ሲሆን 383 ገጾች ያሉት እና በደርግ ዘመነ መንግስት ላይ ያተኮረ ነው። ሌላኛው የዚሁ ደራሲ ስራ *የሱፍ አበባ* በ2008 ዓ.ም የታተመና እና በ379 ገጾች ተወስኖ የቀረበ ነው። የሁለቱም ልቦለዶች የታሪክ መቼት በ1966 _1983 ዓ.ም በነበረው የደርግ ዘመን ላይ ያጠነጥናል። *የቁሳር እንባ* የኮሎኔል መንግሥቱ ኃ/ማርያምን የህይወት ታሪክ እና ደርግ ከአመሰራረቱ እስከ ውድቀቱ ድረስ ያለውን ሂደት በእውነታና በምናብ ተዋህዶ የቀረበበት ታሪካዊ ልብወለድ ነው። በዋና ገፀባህርይነት የቀረቡት መንግሥቱ ኃ/ማርያም ከልጅነታቸው ጀምሮ ሀገር ለቀው እስኪወጡ ድረስ የነበረውን የህይወት ታሪካቸውን ከእውነታ ጋር ምናባዊነት ተቀላቅሎ ስልጣን ወዳድ፣ጨካኝ እና አላዋቂ ተደርገው ተስለው እናገኛለን። እንዲሁም በላይነህ እና ሐምራዊት በተሰኙት በረዳት ገፀባህርይነት አማካይነት የመንግስቱ ኃ/ማርያምን ጭካኔ እና ሁሉንም ስልጣን በመቆጣጠር ፈላጭ ቆራጭነታቸውን ያሳያል። የሐምራዊት ሳቂታነት እና ከባላይነህ ጋር ሲሰደዱ ያለውን የስደት ሂወት በአዕምሯችን እንድንስለው ያደርገናል። የሁለቱ ገጸባህርያት የፍቅር ታሪክ የስደት ታሪካቸው ከደርግ ታሪክ ጋር እየተያያዘ የቀረበበት ነው።

*በየሱፍ አበባ* ላይ ደግሞ ዋና ገፀባህርይ ሰመረ ሲሆን በፊት ላይ የኢሕአፓ አባል በኂላ ላይ የቋሚ ኮሚቴ በመሆን የሚያገለግል ነው። ኢሕአፓ የታሪኩ ማጠንጠኛ ነው። ሰመረ ለኢሕአፓ የሚሰራቸው ስራዎችን፣ የሚፈጽማቸው ተልዕኮዎች እና የቋሚ ኮሚቴ ስብሰባዎች ላይ ሲካፈል በገሀዱ አለም ካሉ እና ከነበሩ የኢሕአፓ መስራች ብርሃነ መስቀል፣ ክፍሉ ታደሰ እና

ዘርዑ ክህሽን እና ከሌሎችም ጋር በመሆን ስለኢሕአፓ ይወያያሉ፡፡ ሰመረ የኢሕአፓ ድብቅ ቦታ በጋራዥ ውስጥ ሲሰራ የጋራዡን አከራይ ልጅ ቢታኒያን ይወዳታል፡፡ ከቢታኒያ ጋር እየተግባቡ ሲሄዱ እሷም የኢሕአፓ ህቡዕ አባል መሆኗን ያውቃል፡፡ የሁለቱ የፍቅር ታሪክ ከኢሕአፓ ታሪክ ጋር እየተዋሀደ የቀረበ ነው፡፡ ሰመረ የቢታኒያን ፍቅር እና ውበትን ሲገልጽ ምስል ከሳች ከመሆኑ የተነሳ በአዕምሯችን እንድንስለው ያደርገናል፡፡ በሰመረ የኢሕአፓን ስህተቶች ናቸው እያለ የሚሞግታቸው እና በጥናት መልክ የሚያዘጋጃቸው ጽሑፎች በልቦለዱ ውስጥ ጎልተው ይታያሉ፡፡ እንዲሁም ኢሕአፓ በደርግ እየታደነ ሲገደል እና በስተመጨረሻም የኢሕአፓ ዕጣ ፈንታን የሚያሳይ ልቦለድ ነው፡፡ በአጠቃላይ ሁለቱም ልቦለዶች በምናባዊ ገጸባህርያት እና ታሪኮች በገሀዱ ዓለም ያሉ እና የነበሩ ሰዎችን በገጸባህይነት በመጠቀም ምናባዊነትና እውነታ ተዋህደው የቀረቡባቸው ታሪካዊ ልቦለዶች መሆናቸውን ከዚህ በታች በቀረበው ክፍል ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

## 3.2. *ሀዲስ ታሪካዊ ሂስ በቆሳር እንባ እና በየሱፍ አበባ*

*ሀዲስ ታሪካዊ ሂስ* ልቦለዱን ከድርሰቱ፣ከደራሲውና ድርሰቱ ከተጻፈበት ዐውድ ጋር በማገናዘብ መረዳት ያስችላል፡፡ እንዲሁም አንድን ድርሰት ከሌሎች ድርሰቶችና መዛግብት ጋር በማገናዘብ ለመተንተን ያመቻል፡፡ ለማሳየነት የማቀርባቸው ቅንጭቦች በአንድ በኩል ፈጠራን የሚገልጹ ሲሆኑ በሌላ በኩል ደግሞ እውነታን የሚያንጸባርቁ ሃሳቦች ላይ ትኩረት ያደርጋሉ፡፡ ትንተናዬን በ*ቆሳር እንባ* ማሳያነት ልጀመር፡፡ *የቆሳር እንባ* ላይ ዋና ገጸባህርይ በመሆን ኮሎኔል መንግሥቱ ኃ/ማርያም ቀርበዋል፡፡ የቀረበው ታሪካቸው ከፈጠራ እና እውነታ ጋር ተዋህዶ መቅረቡን ለማሳየት *ሀዲስ ታሪካዊ ሂስ* ንባብን መሰረት በማድረግ ከሌሎች ሰነዶች እና መዛግብት ጋር እያገናዘብን እንመለከታን፡፡ የመንግሥቱ ኃ/ማርያም ሀገር ጥሎ መጥፋት እንዴት እንደቀረበ እንመልከት፡፡

> "ውስጣቸው በተጻጻራሪ ሐሳቦች ተናጠ፡፡ 'የምሄደው ወደ ኬንያ ነው፡፡ አስቸኳይ ስብሰባ አለብኝ፡፡ የደርሶ መልስ ጉዞ ነው፡፡ አውሮፕላን የምታዘጋጁልኝ ይህን ግምት ውስጥ አስገብታችሁ ነው......' ብላቸው ምን ችግር ይኖረዋል? ራሳቸውን ጠየቁት፡፡ ጥቂት ሴኮንዶች ወስደው መልስ

አፈላለጉ፡፡ ጥያቄያቸውን ተከትሎ በአየር መንገዱ የማርኬቲንግ ክፍል የሚፈጠረው ነገር ታያቸው፡፡ የማርኬቲንግ መኮንኑ ዝም ብሎ የታዘዘውን ይፈጽማል፡፡ በመስኮቱ ብቅ ብሎ አውሮፕላኑን ይመለከታል፡፡ ልክ ጎማዎቹ መሬት እንደለቀቁ ወደ ሌሎቹ ሠራተኞች ይሮጣል፡፡ ድምጹ ቁርጥርጥ እያለበት ይነግራቸዋል፡፡ "ጉድ ነው! መንግሥቱ ኃ/ማርያም አገር ጥሎ ጠፋ"! ከዚያማ አገሩ ሁሉ ስልክ በስልክ......፣ አዲስ አበባ በወሬ ማዕበል ትወዛወዛለች" ኖ! ኖ! ኖ! ትንፍሽ ማለት የለብኝም፡፡ በዚህ በመሀሉ አንድ ተአምር ሊፈጠር ይችላል" (የቄሳር እንባ ፣ 380)፡፡

ከፍ ብሎ የቀረበው ሃስብ የደራሲው ፈጠራ ጎልቶ የታየበት ነው፡፡ መንግሥቱ ኃ/ማርያም ከሀገር ጥለው መውጣታቸውን እና ሊወጡ ሲሉ ከራሳቸው ጋር የሚያደርጉትን የሃሳብ ሙግት እና ሰው እንዲ ሊል ይችላል ብለው በምናባቸውን የሚያስቡት ጉሉ ደረሲው ከእውነታ ጋር አዋህዶ አሳይቶናል፡፡ እውነታው በተለያዩ መዛግብት እና መጻሕፍት ላይ በየጊዜው የሚነሳ ዲስኩር ቢሆንም ለማሳያነት ገነት አየለ ከመንግሥቱ ኃ/ማርያም ጋር ቃለ ምልልስ አድርጋ *የሌተናል ኮሎኔል መንግሥቱ ኃ/ማርያም ትዝታዎች* በሚል ርዕስ የደረሰችውን መጻሕፍ ላይ እንዴት እንደቀረበ እንመልከት፡፡

"ብላቴይ ነው የምሄደው ነው ያልኩት፡፡ ደግሞ ነው፡፡ ኬንያ ሄጄ ፕሬዝዳንት አራፕ ሞይን ለማነጋገር ነው፡፡ ማንም እንዲሰማ አልፈለኩም፣ማንም እንዲያውቅ አልፈለኩም፡፡ቢችሉ......ፕሬዝዳንቱን እያነጋገርኳቸው እያለ መልክተኛው አንድ ነገር ቀስ ብሎ በጆራቸው ነገራቸው፡፡ ከአዲስ አበባ ሬዲዮ ስልጣን በገዛ ፍቃዴ ለቅቄ የመሄዴ ነገር ተነግሮ እሱን ሪፓርት እያደረገ ነው" (ገነት፣1994፣ 347_48)

"ሁኔታዎች የተለወጡት ብላቴ ለመድረስ ትንሽ ሲቀረን፣ፕሬዝዳንቱ ፓይለንቱን አስጠርተው ቀጭን ትዕዛዝ ሲሰጡት ነው፡፡ 'ከፍተኛ ስብሰባ ስላለብኝ ወደ ናይሮቢ ሂድ አሉት'፡፡ 'ወደዚያ እንሄዳለን ስላልተባልኩኝ ካርታ አልያዝኩም' አለ ፓይለቱ፡፡ አጃቢዎቹ ደነገጡ፡፡ እኔም ደነገጥኩ፡፡ እሳቸው ግን ፍንክች ሳይሉ 'የምቀርበት አይደለምና እንደፈለክ ሂድ'፡፡ ዛሬ ናይሮቢ መድረስ አለብኝ፡፡ ይሄው ነው' አሉት፡፡ በዚህ ሁኔታ ነው እንግዲህ ኬንያ የደረስነው፡፡ በበኩሌ ማታውኑ

> ወደዚምባብዌ ከተጓዘው ግሩብ ጋር እንድሄድ መንግሥቱ ጠይቀውኝ ነበር"(ገነት፣ 1994፣51)

የኮሎኔል መንግሥቱ ኃ/ማርያም ሀገር ጥሎ መጥፋት ከላይ ያለው በቁሳር እንባ ከፈጠራ ጋር ተዋህዶ የቀረበው ሲሆን ከፍ ብሎ በመጀመሪያ የተገለጸው ገነት አየለ በወቅቱ የነበሩትን ጓድ ቃለ መጠይቅ ስታደረግ ያገኘችው ምላሽ ነው:: በስተመጨረሻ የተቀመጠው ደግሞ ከራሳቸው ከመንግሥቱ በቃለ መጠይቅ አገኘሁት ብላ ያሰፈረችው ነው:: ወያኔ አዲስ አበባን ለመቆጣጠር እየተቃረበ በነበረበት ወቅት ከሀገር መውጣታቸው እውነታ ነው:: ከሀገር የወጡበት ምክንያት ተጨባጭ አድርጎ ማቅረብ አይቻልም:: ምክንያቱም በሀዲስ ታሪካዊ  ታሪክ የፍጹምነትን ደረጃ አያገኝም:: እንዲሁም በሀዲስ ታሪካዊ ምሁራን አተያይ አንድ የተከሰተ ታሪክ በተወሰነ ጊዜ እና ቦታ በትክክል ምን እንደተፈጠረ ሊታውቅ አይችልም:: ነገር ግን ሊታወቅ የሚችለው በቅርያችና በታሪኮች ውስጥ የተላለፈው ክስተት ብቻ ነው:: ይሄንን ሃሳብ Ann.B.Dobin (2012፣178 ) ሲገልጹ

> "The new historicists, most of them literary scholars, have challenged and resisted the assumptions and goals of traditional historicism. They deny, for example, that anyone can ever know exactly what happened at a given time and place. All that can be perceived is what has been handed down in artifacts and stories, making history a narration, not a pure, unadulterated set of precise observations.
>
> "አብዛኞቹ የሀዲስ ታሪካዊ ሂስ ሊቃውንት የብሉይ ጽንሰ ሃሳቦችን ተቃውመዋል:: ከታቃወሙት ጽንሰ ሃስብ መካከል ለምሳሌ ማንም ሰው በተወሰነ ጊዜና ቦታ የሆነውን ነገር በትክክል ሊያውቅ ይችላል የሚለውን ሃሳብ አጥብቀው ይቃወማሉ:: ሊታወቅ የሚችለው በቅርሶች እና ተረቶች ውስጥ የተላለፈው ብቻ በመሆኑ ታሪክን ተረክ ያደርገዋል:: ታሪክ ንጹህ, ያልተበረዘ የትክክለኛ ምልከታ ስብስብ አይደለም"::

የተለያዩ ጸሐፊያን የደርግ ታሪክን ሲጽፉ ሁሉም ሳይጠቅሱት የማያልፉት የጀነራሎቹን የግድያ ዲስኩር ነው:: ይህ የጀነራሎቹ ግድያ መፈጸው እውነታ ሲሆን ማን እንደገደላቸው እና እንዴት

እንደተገደሉ ግን በትክክል የሚገልጽ መረጃ የለም:: ምክንያቱም ከፍ ብዬ ያነሳሁት የ Ann.B.Dobin ሃሳብ ይገልጸዋል:: በቆሳር እንባ ይህ ታሪክ ኮሎኔል መንግሥቱ ኃ/ማርያም ለስልጣን ካላቸው ጥም የተነሳ ተቀናቃኝ ይሆኑብኛል ብለው ያሰቧቸውን ጀነራሎች እንደገደሉ ከፈጠራ ጋር እንዴት ተዋህዶ እንደቀረበ እንመልከት

> "ሻለቃ መንግሥቱ ሶሻሊዝም ካወጁ ወዲህ ወደሞስኮ ሲበሩ የመጀመሪያ ጊዜያቸው ነው:: ከእነ መቶ አለቃ አለማየሁ ኃይሌ ጋር የገቡበት የሥልጣን ትንቅንቅ ፋታ አልሰጣቸው:: እነርሱን ሲያስወግዱ እፎይ አሉ:: ይሄ እፎይታ ግን አሁንም ብዙ አልቆየ:: የሶማሊያ ወረራ መጣ:: አሜሪካ 60ዎቹ ሚኒስትሮች ከተገደሉ በኋላ ፊቷን ኢትዮጵያ ላይ አዙራለች":: (የቁሳር እንባ ፣ 79)

ሁሉም ታሪክ ጸሐፊያን ባላቸው የግል አመለካከት እና በሰነድነት በሚያገኟቸው መረጃዎች ተፅእኖ ውስጥ እንደሚወድቁ ይታወቃል:: የጀነራሎቹን ግድያ እውነትነት ለመፈተሽ ሌሎች ከሎሎች መዛግብት ውስጥ የልዩ አቃቤ ህግ ጽ/ቤት ያሳተመውን መጽሐፍ ላይ እንዴት እንደተገለጸ እንመልከት

> "ጥር 26 ቀን 1969 የእነ ሌ/ኮሎኔል መንግሥቱ ኃ/ማርያም ቀን ሆነ:: ጀነራል ተፈሪ በንቲ፣ሌ/ኮሎኔል አሥራት ደስታ፣ሌ/ኮሎኔል ህሩይ ኃ/ስላሴ፣ ሻምበል ሞገስ ወ/ሚካኤል፣ሻምበል ተፈራ ደነቀ፣ ሻምበል ዓለማየሁ ኃይሌና አስር አለቃ ኃይሉ በላይ የተባሉት የደርግ አባላት በሌተናል ኮሎኔል መንግሥቱ ኃ/ማርያም ትዕዛዝ ከቤተመንግሥት ስብሰባ ላይ ተይዘው ተረሸኑ:: የስልጣን ሽኩቻው መቋጫ አግኝቶ የረዥም ጊዜ ሕልሙ እውን ሁኖ ሌ/ኮሎኔል መንግሥቱ ኃ/ማርያም የደርጉ ዋና ሊቀመንበር ሆነ"::(የልዩ አቃቤ ህግ፣2000፣102)::

ከላይ የተገለጸው የጀነራሎቹ ግዲያ በቆሳር እንባ ላይ ግዲያው መፈጸሙ እና በመንግሥቱ ኃ/ማርያም ትእዛዝ መሆኑን በድጋሚ የተዘጋው ዶሴ ላይም ተገልጿል:: ገነት አያሌው ደግሞ መንግሥቱ ኃ/ማርያም ጋር ባደረገቸው ቃለ ምልልስ ላይ ያስፈረችው ውሳኔው የግላቸው ሳይሆን ሙሉ የደርግ አባላት ተሰብስቦ የወሰነው እንደውም እሳቸውም ግድያውን እንደተቃወሙ የሚገልጽ ነው:: ስለዚህ የጀነራሎቹ ግድያ እውነት መፈጸሙ እውነታ ሲሆን ይህ እውነታ ከፈጠራ ጋር ተዋህዶ የቀረበው መንግሥቱ ለስልጣን ካላቸው ጥም የተነሳ እንደሆነ ደራሲው በፈጠረው በላይነህ በተሰኘ ገጸባህርይ አማካይነት እንደሆነ እንመልከት::

"አብዮቱና ዲሞክራሲ እዚሁ ደርግ ውስጥ መጀመር አለበት ብለው ተነሱ። ሞት ምላሻቸው ሆነ። አሚሚታቸው ደግሞ በፊሪ ዱላ ተቀጥቅጠው ነው። ካልሞቱ ሰላም አላገኝም እሚል ፍርሃት የወለደው ጭካኔ ሰለባ አደረጋቸው" (የቄሳር እንባ፣92)

ከፍ ብሎ የተገለጸው ሃስብ በላይነህ የተሰኘው ገጸባህርይ የመንግሥቱ ኃ/ማርያም ሰራተኛ እና የሚስታቸው ዘመድ በመሆን ቤታቸው ውስጥ እየኖረ የሳቸውን ሚስጥር የሚያጋልጥ ሲሆን ስለጀነራሎቹ ግድያ ሃስቡን በጽሑፍ በሚገልጽበት ወቅት ፈጠራውን ማየት እንችላለን "ብድግ ብሎ ወደ መስታወቱ ሄደ። የፊቱን ገጽ አስተዋለ። ጠይምነቱ የጨመረ መሰለው። የተቆላለፈ ለስላሳ ጸጉሩን በጠርበጠር አደረገ። ተመልሶ ወደ ወንበሩ በጥቶ ጽሑፉን ቀጠለ...."(የቄሳር እንባ፣92) በማለት ይገልጻል። ስለጀነራሎቹ ግድያ ለማጻፍ ምንያህል እንደተጨነቀ እና የመንግሥቱ ኃ/ማርያም የስልጣን ጥም እና ጭካኔ እንዳስፈራውም እንዳስተከዘውም ከድርጊቱ እናያለን። ይህን ድርጊቱን ደራሲው በፈጠራ ምሳላዊ እይታን እንዲፈጥር አድርጎ አቅርቦታል። በተጨማሪም በዚሁ ገጸባህርይ አማካኝነት የመንግሥቱ ኃ/ማርያም ጭካኔና የስልጣንን ወዳድነት መንስዔን ከሥነልቦና ጋር ተያይዞ እንደሚከተለው ሲተነተን እናያለን

*"ያገኘኋቸው መረጃዎች የሚነግሩኝ አንድ ትልቅ ነገር አለ። የኮሎኔል መንግሥቱ የፓለቲካ ስብዕና በትምህርት ወይም በንባብ ወይም በሌላ ሥልጠና የተቀረጸ አይደለም። ይልቁንስ በኢትዮጵያ ሰፍኖ የነበርው ማኀበራዊ ቅራኔ ውጤት ነው። **የፓለቲካ ንቃታቸው ሕዝቡ እሳቸውን ለሚያይበት መነጽር የተሰጠ ምላሽ ነው**"* (የቄሳር እንባ፣103)።

ከላይ በላይነህ በተሰኘ ገጸባህርይ አማካኝነት የመንግሥቱ ኃ/ማርያም ጭካኔና የስልጣንን ወዳድነት ከሥነልቦና ጋር ተያይዞ የተተነተነው የደራሲው የፈጠራ ውጤት ነው። መንግሥቱ ኃ/ማርያም ጨካኝ እና በብዙ ሰዎችን የግዲያ ወንጀል የመወንጀላቸውን ዲስኩር እንደ እውነታ በመያዝ ለዚህ ድርጊታቸው እንደምክንያትነት የተነሳው ሃሳብ ፈጠራ ነው። ምክንያቱም የግድያ ወንጀል ፈጽመዋል ወይም እንዲፈጸም አድርገዋል ተባለ እንጂ ያንን የሚያስረዳ እና ለምን እንዳደረጉት ማብራራት ስለማይቻል። ይህንን መንግሥቱ ኃ/ማርያም የልጅነት አስተዳደግ፣ በመልካቸው ይባሉትን እና ይደርስባቸው የነበረው ነገር ደራሲው ያሳየናል

"ሕፃን መንግሥቱ በ1944 ዓ.ም የአሥራ ሁለት ዓመት ልጅ ነበር። በዚህ ወቅት ደብረማርቆስ ከተማ ሄዶ ነበር። አራተኛን ክፍል ጨርሷል። የአዲስ አባባ ልጅ ስለነበረ በብዙ ነገር ለየት አለባቸው፣ ለደብረ ማርቆስ ልጆች። ቆዳ ጫማና ካልሲ አድርጓል። ከመጠን በላይ ንቁ ነው። የብዙ ሕፃናትን ትኩረት ሳይፈልገው ሳባ። አልፏቸው ሲሄድ ታዲያ ትኩር ብለው ከፊትም ከጀርባም ያጠኑትና፣ 'ይቺ የማናት ንቁ ሻንቆ?' ሲሉ ሲሰማ ንድድ ይለዋል" (የቄሳር እንባ፣104)

የፈጠራ ጽሑፍ አንባቢን የሚያሳትፍ፣ የሚያነቃቃ ወይም የሚያስደንቅ፣ ስሜትን የሚቀሰቅስ እና አስደሳች ወይም አሳዛኝ ታሪኮችን ለመንገር ጥቅም ላይ የሚውል ዘዴ ነው። ከዚህ አንጻር ከፍ ብሎ የቀረበው ሃሳብ ጽሑፉን ለማንበብ የሚያነሳሳ እና የበለጠ ለማወቅ ስሜትን የሚቀሰቅስ ነው። መንግሥቱ በልጅነታቸው የነበራቸውን መልክ እና ይደርስባቸው የነበረው ነገር እንዳየነው ያህል እንዲሰማን እና እንድናስበው በሚያስችል መልኩ የቀረበ ነው። እንዲሁም ወደ ደብረማርቆስ አከባቢ ከማህበረሰቡ ለየት ያለ ሰው ሲመጣ ያለውን የማህበረሰቡን አመለካከትም አሳይቶናል። ይሄን ሃስብ የማህበራዊ እውነታ በሚለው ንዑስ ርዕስ ክፍል በሰፊው እንመለከተዋለን።

ፈጠራ በምናብ የተፈጠሩ ገጸ-ባህሪያትን፣ ሁነቶችን እና መቼቶችን ያመለክታል። በ*ቄሳር እንባ* ልቦለድ ውስጥም ውስጥ ስለመንግሥቱ ኃ/ማርያም እና ልግመት ኢትዮጵያ ብሎ በላይነህ የተሰኘው ገጸባህርይ የሚጽፋቸው ሃሳቦች በሙሉ የፈጠራ ውጤት መሆናቸውን መረዳት ይቻላል። በላይህነህ ስለ መንግሥቱ ኃ/ማርያም እና ስለ ሥርዓታቸው የጻፈበት ማስታወሻ ደብተር ሲጠፋ ሀገሩ ጥሎ ሊሰደድ ሲል እንዲሰደድ ያደረገው በፈጠረው ሁነቶች ነው። እነዚህ የደራሲው የፈጠራ ሁነቶች ደግሞ በላይነህ ሲጽፋቸው የነበሩት ናቸው። ምክንያቱም ማስታወሻ ደብተሩ ጠፍቶ ለስደት የዳረገው በማስታወሻ ደብተሩ ላይ ያሰፈራቸው ጽሑፎች ስለሆኑ። በልቦለዱ ውስጥ ከእውነታ ጋር እየተዋሃዱ የሚቀርቡት እያንዳንዱ የፈጠራ ውጤቶቹ ለታሪኩ ጉልህ አስተዋጻኦ ያላቸው ፣ በምክንያትና ውጤት ደግሞ የተሳሰሩ ናቸው።

እስካሁን ያየነው የእውነታ እና የፈጠራ ውህደትን ለትንተና በተመረጠው የሱፍ አበባ ልቦለድ ላይ ደግሞ ለማሳያነት ከሚቀርቡ ቅንጭቦች ጋር በማዛመድ እንመለከት። የሀዲስ ታሪካዊ አቀንቃኞች ታሪክ ከብዙ ሀቲቶች ውሰጥ አንዱ እና ግላዊ እንደሆነ ይገልጻሉ። በ*የሱፍ ኣበባ* ላይ የተስፋዬ ደበሳይ ታሪክን የተገለጸው እንደሚከተለው ነው

> “ ‘የመጣው ይምጣ!’ ወጥቼ ወደ መኪናዬ ተጣደፍኩ። በመሀሉ ባላሰብኩት ደመነፍሳዊ ግፊት ወደ ኪዳኔ ህንጻ ዞር አልኩ። ነፋስ ሽቅብ አንስቶ መልሶ ቁልቁል የወረወረው ቆርቆሮ ነበር የመሰለኝ። አይደለም። እየተምዘገዘገ የወረደው ሰው ነው። ከሰውም ደግሞ ዶክተር ተስፋዬ ደበሳይ! ከአምስተኛ ፎቅ ላይ እየተንሳፈፈ ወርዶ ድንጋዩ ንጣፍ ላይ ሲወድቅ ጧ! የሚል ድምጽ እንደ ጥይት ፈነዳ” (የሱፍ አበባ፣376)

ከፍ ብሎ የቀረበው ሃሳብ ምን ያህል ታሪክ፣ ሀቲት እና ምናባዊነት ተቀላቅሎት እንደሚቀርብ ለማሳየት የተስፋዬን አሟሟት በሌሎች ታሪክ ጸሐፊያን እንዴት እንደቀረበ እንመልከት። የ *ዳኛው ማነው* ደራሲ ታደለች እንደምትገልጸው “በመኪና ከቦታ ቦታ ሲዘዋወር በክትትል ሲደረስበት፣ ከነበረበት ኪዳኔ ህንፃ ፎቅ ዘሎ ተሰዋ። ምን ያድርግ እንዳለውም ጊዜው ዘግይቶበት ነበር” (ታደለች፣2012፣284) በማለት በራሷ አተያይ እንዲህ ገልጻለች። እንዳርጋቸው ጽጌ ደግሞ ስለተስፋዬ አሟሟት እንደሚከተለው ይገልጻሉ

> “ደርጎችና ተባባሪዎቻቸው በነፍሱ አይደለም አጥንቱን ጭምር እንዲያገኙት አልፈለገም። በተለመደው የሀገሩ ጀግኖች ባህል ‘መሪ እጁን ለጠላት አይሰጥም’ አለ። በጁ መሳሪያ ስላልነበረ ከሰባተኛ ፎቅ የህንጻውን ጠንካራ መስታወት በሰውነቱ ሰብሮ ቁልቁል ወረደ” (እንዳርጋቸው፣ 2011፣566)

ከላይ የተመለከትናቸው ምንባቦች ላይ የታሪክ ጸሐፊዎች የመሞቱ እውነታን ከምናብ ጋር ቀላቅለው አቅርበው ነው። እውነታው የተስፋዬ ከፎቅ ላይ መሞት ነው። ሁሉም ይህን ገልጸዋል። ነገር ግን የራሳቸውን ምናብ እየቀላቀሉ መጻፋቸውን በቀረበው ምንባብ መረዳት ይቻላል። እንዳርጋቸው ጽጌ ከላይ የገለጹት የተስፋዬ አሟሟት ‘መሪ እጁን ለጠላት አይሰጥም’ አለ ይላሉ ይህ አባባላቸው ግን ከፎቅ ላይ የወደቀው እንደዛ አስቦ ይሆናል የሚለው የሳቸው ግምት ወይም እይታ እንጂ እውነታው አይደለም። ታደለች እንደገለጸችው ተስፋዬ ምንም አማራጭ ስላነበረው ላይሆን ይችላል። እሷ ምንም አማራጭ ስላነበረው ብላ የገለጸችው የግል አመለካከቷን መሆኑን መረዳት ይገባል። *የሱፍ አበባ* ላይ ደግሞ አሟሟቱን ቁሞ የተመለከተው ሰመረ ደራሲው ስለ ተስፋዬ አሟሟት የተለያዩ የታሪክ መጻሕፍትን ሲያነብ በምናቡ የተፈጠረበትን ምስል በዋና ገጸባህርይ በሰመረ በኩል አንጸባርቋል። ስለ አሟሟቱ የተገለጸበት መንገድ ምስል ከሳች ከመሆኑም በላይ ፈጠራው ጎልቶ የሚታይበት ነው። ከ5ኛ ፎቅ ላይ

አወራረዱን እና ወርዶ አወዳደቁን ሲወድቅ ያለውን ድምጽ ጭምር በፈጠራ ቀርቧል። ፈጠራ ነገሮችን በምስላዊ መንገድ ለመግለጽ ከማመቸቱም በላይ ሁነቶችን በቦታው እና በሰዓቱ የነበርን ያህል እንዲሰማን ለማድረግ አመቺ ነው። ይህንንም ዘዴ ነው ከፍ ብሎ በቀረበው ምንባብ ላይ እንደተገለጸ መረዳት የሚቻለው።

በሀዲስ ታሪካዊ አተያይ ታሪክ የትርጉም ጉዳይ ነው ብለናል። በ*የሱፍ አበባ* ላይ ስለ ኢሕአፓ መስራች ብርሃነ መስቀል መጨረሻ የተለያዩ ዲስኩሮች አሉ። ባለቤቱ ታደለች በ*ዳኛው ማነው* ላይ ስለ ብርሀነ መስቀል ስትገልጽ "ከ ሀ ና ለ ጋር ተወያይተውና ተነጋግረው ይቅርና አይተዋቸው እንኳ እንደማያውቁ ቢያስረዱም፣ በሚወዱት ፓርቲያቸውና ግልጽ ባልሆነ መንገድ ተገለሉ። ቀስ ብለውም ተሰደዱ፣አንጃ በመባልም ተገደሉ" (ታደለች፣2012፣275) በሚወደው በራሱ ፓርቲ አባሎች መገደሉን ትገልጻለች። *የሱፍ አበባ* ላይ ደግሞ ድሕረ ታሪክ ተብሎ በተቀመጠው የመጨረሻው ክፍል ላይ ስለ ብርሀነ መስቀል መጨረሻ እንዲህ ይገለጻል

> "ቢታኒያ እየተንደፋደፈች ስትመጣ ወደ ጓደኞቿ ስልክ መደዋወልና መረጃ መሰብሰብ ጀመረች። አንድም ደስ የሚል ወሬ ሰምታ አሰምታኝ አታውቅም። አበበች በቀለ ታስራ ቆይታ በኋላም መገደሏን፣ **ብርሃነ መስቀል** የተወሰነ የታጠቀ ቡድን ይዞ ሸዋ መግባቱን፣ ዘርዐ ክህሽንና ሚስቱ ታደለች ኪዳነማርያም (ለምለም) ከኤርትራ ተመልሰው ወልቃይት መሆናቸውን፣ክፍሉ ታደሰ ደግሞ ጭራሽ የት እንደገባ አለመታወቁን ነገረችኝ" (የሱፍ አበባ ፣377)።

ከፍ ብሎ በቀረበው ሃሳብ እና በ *ዳኛው ማነው* ላይ አንድ ታሪክ እንዴት እንደቀረበ ልብ ማለት ያስፈልጋል። በየሱፍ አበባ ላይ የኢሕአፓ እና የደርግ ጦርነት ሲባባስ ሰመረ እና ቢታኒያ ተደብቀው እየኖሩ ጦርነቱ ወደ ማለቅ ሲደርስ ስልክ በመደወል መረጃዎችን ሰብስባ ለሰመረ ትነግረዋለች። ይህ ሂደት በፈጠራ የተሞላበ እና በጦርነቱ ወቅት ግን የኢሕአፓ አባላት ያሉበትን እውነታ ነው ከነስማቸው የተገለጸው። ስለዚህ ፈጠራ እና እውነታውን ተዋህደዋል ማለት ይቻላል። በተጨማሪም ገነት አየለ ከመንግሥቱ ኃ/ማርያም ጋር ቃለ ምልልስ ባደረገችበት መጽሐፍ ላይ ደግሞ መንግሥቱ ስለብርሃነ መስቀል ሲናገሩ በስተመጨረሻ ሰሜን ሸዋ አከባቢ ገበሬዎች ገድለውት ተገኘ ሲሉ ሰምቻለው ይላሉ። እንዲሁም አስማማው ኃይሉ ስለብርሀነ መስቀል ሲገልጽ

> "ደርግ አስሮት እያለ እስኪገደል ድረስ 'በደርግ ቤተ መንግሥት ገብቶ ለደርግ እየጸፈ ነው' የሚል ዜና ነበር የሚነገረን። እውነታው ቆይቶ ሲገለጽ ግን በደርግ ምሕረት እንዳልተሰጠውና በሞት እንደተቀጣ ነው" (አስማማው፣ 2003፣38)።

ከላይ አንድ ታሪክ በተለያዩ ጸሐፊያን እንዴት እንደቀረበ በተመለከትነው መሰረት ሀዲስ ታሪካዊ እንደሚለው ታሪክ የትርጉም ጉዳይ እንጂ በትክክል የተከሰተው አይደለም። ምክንያቱም ታሪክ ከምናባዊነት ነጻ ሁኖ ሊቀርብ ስለማይችል። በ*የሱፍ አበባ* ላይ ቀርቦ የተመለከትነው ታሪክም ከፈጠራ ጋር ተዋህዶ እንጂ ትክክለኛ ምልከታ እንዳልሆነ መረዳት ይቻላል። ሌላው *የቄሳር እንባ* እና *የሱፍ አበባ* በእውነተኛ ሰዎች እና ክስተቶች ላይ በተመሰረተ ታሪኮች የታጨቁ ናቸው። *የቄሳር እንባ* ላይ ከመንግሥቱ ኃ/ማርያም ጀምሮ ባለቤታቸው ወ/ሮ ውባንቺ፣ ልጆቻቸው ትምህርት፣ትእግስት እና አንድነት፣ጀነራል ተፈሪ ባንቲ እና ሌሎችም ገጸባህርያት በገሀዱ አለም የነበሩ እና ያሉ ናቸው። ይሄ ብዙ ጊዜ በእውነታው ላይ ተመርኩዞ የበለጠ ትኩረት የሚስብ ትረካ ለመፍጠር የፈጠራ ውጤቶችን ለመጨመር ስለሚያስችል ነው። *የቄሳር እንባ* ላይ መንግሥቱ ኃ/ማርያም ከሀገር በወጡበት ወቅት ስለሀገራቸው ቅርጽ ከውጭ ዜጋ በመስማታቸው ሀገራቸውን ለመጎብኘት በመነሳሳታቸው ጉብኝት ያደርጋሉ። በሚጎበኙበት ወቅትም የሚስብ ታሪክ ለመፍጠር ፈጠራዊ ክስተት እንደሚከተለው ተጨምሯል።

> "መንግሥቱ ጭለማ የዋጠውን ቦታ እንዳዩ ቀጥ ብለው ቆሙ። "እውጭ አውጥታችሁ ብታሳዩኝ ምን ችግር አለው?" አንደኛውን ጠየቋቸው፣ ኧረ ምንም ችግር የለውም፣ እናወጣልዎታለን.....። ለሁሉም ሰው በቀላሉ ብድግ ተደርጎ የሚወጣ ነገር መስሏቸው ነበር። ይህን ያህል ክብደት የተደረገባቸው ለስርቆት እንዳይመቹ ነው። መነኮሳቱ እየተጯጯሁ..... እየተንገዳገዱ..... እያቃሰቱ የአጼ ፋሲልን አጽም አምጥተው አስቀመጡ። ተመልሰው ገቡ። የአጼ ዳዊትን አጽም ሲያመጡ ግን አቅም ከዳቸው። በአንደኛው መነኩሴ በኩል ሚዛኑ ተበላሸ። ሳጥኑ አምልጧቸው መሬት ላይ ወደቀ። ጓ!! እንደ ጥይት ጮኸ። **መንግሥቱ ከምንም አልቆጠሩትም።** አየት አድርገው ጨረሱ። ምንም አላመነቱም። ቁልቁለቱን መውረድ ጀመሩ" (የቄሳር እንባ፣139)

ከፍ ብሎ የቀረበው ሃሳብ ላይ መንግሥቱ ከሀገር በወጡበት ጊዜ በርካታ ታሪኮችን ከውጪ ሀገር ዜጋ ሲሰሙ እና ሲቆጩ ቀጣይ የሚያደርጉትን ለማወቅ ለማንበብ ያነሳሳል።

በተጨማሪም እንደተመለስኩ ሀገሬን ኃበኛለሁ ብሎ ጉብኝት ሲያደርጉ በተለይ በጣና ገዳማት ያላቸው የጉብኝት ሁኔታ ፈጠራው ጎልቶ ታይቶበታል፡፡ የመኮሳቱ አኳኋን እና የመንግሥቱ ምላሽ የአንባቢን ትኩረት የሚስብ የፈጠራ ውጤት ነው፡፡

ለአንባቢያን በልብወለድ ውስጥ ቀጥተኛ አድራሻ ወይም የሚያውቁትን ክስተቶችን በግልፅ ይገለጻል፡፡ ደራሲ በዓሉ ግርማ ኦሮማይን ከጻፈ በኋላ ስለመሰወሩ ወይም ስለመሞቱ በቀጥታ አንባቢያን የሚያውቁት ክስተት ነው፡፡ ይህን እውነታ ከፈጠራ ጋር በመቀላቀል እንደሚከተለው ቀርቧል

> "ከዚህ በኋላ ግን ያስደነገጣቸው ዜና የመጣው የደራሲ በዓሉ ግርማ መሰወርና መገደልን ተከትሎ ነበር፡፡ ኪዳነምህረት ባህታ እድር ተቀምጠው ወሬውን ሰሙ፡፡ በዚህ ላይ ትምህርትና ትእግስት በዓሉን በጣም ይወዱታል፡፡ ኮሎኔል መንግስቱን በልጆቻቸው መሀል ጠበቅ አድርገው ጠየቋቸው፡፡ '**ተይው ውቤ፣ የእጁን ነው ያገኘው**! አሏቸው፡፡ ትኩር ብለው በድንጋጤ ዐይተዋቸው ከንፈራቸውን በሐዘን መጠጡ፣ ጽም!" (የቁሳር እንባ ፣38)

ይህ ምንባብ አንባቢያን የሚያውቁትን ክስተት በመጥቀስ ከፈጠራ ጋር በመቀላቀል አንባቢያን በእውነታ እና በፈጠራ መካከል ያለውን ድንበር ለመለየት ይቸገራሉ፡፡ በገሀዱ አለም በዓሉ ግርማ በኦሮማይ የድርሰት ስራው ምክንያት በደርግ እንደተገደለ ይታመናል፡፡ ይህንን ገነት ከመንግሥቱ ኃ/ማርያም ጋር ባደረገችው ቃለ ምልልስ ላይም መንግሥቱ እንዲገደል ትእዛዝ እንዳልሰጡ ነገር ግን ከቤቱ እንደወጣ እንዳልተመለሰ ይናገራሉ፡፡ ይህን ምልከታን እንደ እውነት በመውሰድ ከፈጠራ ጋር በማዋሃድ በመንግሥቱ ኃ/ማርያም ትእዛዝ መገደሉ ተግልጿል፡፡ ይህንንም በደርግ ስለተገደሉ ሰዎች ምስጋናው እና በላይነህ የተሰኙ ገፀባህርያት ሲያውሩ ይገልጽና የበዓሉ አሟሟት ላይ ሲደርስ ግን "በላይነህ ስለበዓሉ ግርማና አቤ ጉበኛ አሟሟት ሊጠይቀው ከምላሱ ደርሶ ትዕግስት ስትመጣ ስላያት ዝም አለ" (የቁሳር እንባ፣98) በማለት ይገልጻል፡፡ ይህን ያቀረበበት ምክንያት ስለ መሞቱ እንጂ ስላሟሟት ተጨባጭ መረጃ ባለማግኘቱ ነው፡፡ ፈጠራና እውነታ ተዋህደው ሲቀረቡ አንባቢያን ለመለየት ስለሚቸገሩ የቀረበውን ምንባብ እውነት አድርገው ይቀበላሉ፡፡ ስለበአሉ አሟሟትም በብዙ አንባቢያን ዘንድ በመንግሥቱ ኃ/ማርያም መገደሉ ይታመናል፡፡ ነገር ግን ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ስለአሟሟቱ ተጨባጭ የሆነ ታሪክ የለም፡፡

ተጨባጭ እና ምናባዊ ነገሮች ምን እንደሆኑ በግልፅ መረዳት ስለማይቻል ተጨባጭ ታሪካዊ ክስተቶችን ከፈጠራ ጋር በማዋሃድ እንዴት እንደቀረበ እንመልከት። በ *የሱፍ አበባ* ላይ ከገጽ 248_256 ድረስ መንግሥቱ ኃ/ማርያምን ለመግደል የተደረገውን ሙከራ በሰመረ ፍቅረኛ ቢታኒያ በኩል በፈጠራ እና እውነታ ተዋህዶ እንደሚከተለው ቀርቦ እናያለን

> "በሯን በርግጄ ገባሁ። በሕይወት አገኘኋት። ቢጃማዋን ለብሳ ሬዲዮ ስትጎረጉር ደረስኩ። ከመጠን በላይ ተረባብሻለች። ለበርካታ ሴኮንዶች እንደተቃቀፍን ቆየን። የተላቀቅነው ወንድ የሬድዮ ጋዜጠኛ "አድማጮቻችን፣አሁን የደረሰን ዜና አለ! ሲል ነው። ሄዳ ሬዲዮውን አንስታ ይዛው ቆመች። ጸረ አብዮትና ጸረ ሰላም ዓላማ የሚያራምደው ኢሕአፓ የተሰኘው አናርኪስት ቡድን ቅጥር ነፍሰገዳዮች የደርጉን ተቀዳሚ ምክትል ሊቀመንበር ሻለቃ መንግሥቱ ኃ/ማርያም ለመግደል በከፈቱት ተኩስ ምክትል ሊቀመንበሩ ቆስለው ሆስፒታል መግባታቸውን የደርግ ጽሕፈት ቤት አስታወቀ። ይሁንና አደጋው ለሕይወታቸው አስጊ አለመሆኑ ሐኪሞች አረጋግጠዋል" (ሀብታሙ፣257)።

ይህ ከፍ ብሎ የቀረበው ምንባብ የመንግሥቱ ኃ/ማርያም በኢሕአፓ በተከፈተባቸው ተኩስ መመታታቸው እውነታ ሲሆን ከዚህ እውነታ ጋር ተዋህደው የቀረቡት የቢታኒያን ንግግር እና ድርጊት ፈጠራ ወይም ፈጠራዊ ክስተቶች ናቸው።

በተጨማሪም ፋክሽን የሚለውን ጽንሰ ሃሳብ ብንመለከት የእውነተኛ ህይወት ክስተቶችን እና ሰዎችን ለልብ ወለድ ታሪክ መሰረት አድርጎ ይጠቀማል። የፋክሽን ስራዎች ብዙ ጊዜ ታሪካዊ ክስተቶችን ይመረምራሉ፣ በታዋቂ ታሪኮች ወይም ገፀ ባህሪያት ላይ አዲስ እይታን ይሰጣል። በ*ቆሳር እንባ* የደርግ መንግሥት በነበረበት ወቅት በ1977 ዓ.ም የተከሰተውን የረሃብ አደጋ፣ በመንግሥቱ ኃ/ማርያም ላይ የተደረገውን መፈንቅለ መንግሥት ፣ ከኤርትራ ጋር የነበረውን ጦርነት እና የህውሓት ወይም የወያኔን አመጣጥ እና የነበረውን ሂደት እንዲሁም ሌሎችንም ታሪካዊ ክስተቶችን ይፈትሻል። የቀይ ኮከብ ዘመቻን ለማክሸፍ ህውሓት ቁልፍ ሚና መጫወቱን መንግሥቱ ሲሰሙ ነገሬ ብለው ስለህውሓት መከታተል ጀመሩ። በማለት የህውሓት አመሰራረትን እንደሚከተለው ተገልጿል

> "አራተኛ ተራ ቁጥር ላይ የነበረው አረጋዊ በርሄ ነው:: ስለእሱ ሰነዱ የሚለውን አስታወሱት:: የአድዋ አከባቢ ተወላጅና ሙሉ በሙሉ ትግራዊ...........አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፓለቲካል ሳይንስ ያጠና.....የወታደራዊ ክንፋን ያዋቀረና የመራ......በአስተሳሰብ ግትርና ጀብደኛ ......የፓለቲካ ክንፋን ለሚመሩት ስብሀት ነጋ፣ አባይ ፀሐዬና መለስ ዜናዊ ጋር የሚወዛገብ.......ሽምቅ ውጊያ በአብዛኛው ወታደራዊ ጉዳይ ነው ብሎ የሚያምን....."እያለ ይቀጥላል (የቄሳር እንባ፣57)

ከላይ በምንባቡ ላይ የተገለጹት ሰዎች በገሀዱ አለም የነበሩ አንዳንዶቹ አሁንም ድረስ ያሉ የህውሓት አመራር ላይ የነበሩ ናቸው:: ደራሲው የህውሓትን ታሪክ ከአመሰራረቱ ጀምሮ ለመፈተሽ ሞክሯል:: ከላይ እንደተገለጸው ፋክሽን ያለፉ ታሪካዊ ክስተቶችን ደግሞ ለመፈተሽ ያስችላል::

የፈጠራና የእውነታ ውህደት መንግሥቱ ኃ/ማርያን አዲስ እይታን ሰጥቷቸዋል:: የደርግ ሊቀመንበር ሆነው ከተመረጡበት ጊዜ አንስቶ ሀገር ጥለው እስኪሰደዱ ድረስ ያለው ሂደትን በምናብ እየታሸ ታሪካዊ ክስተቶችን ተዳሰዋል:: መንግሥቱ ኃ/ማርያም የሀገር ፍቅር ሳይሆን ያላቸው የስልጣን ጥማት እና ሁልጊዜም እርምጃዎችን የሚወስዱት የስልጣን ጊዜያቸው ለማራዘም እንደሆነ እና በቀለኝነት የፖለቲካ ስልት እንዳደረጉት ተገልጿል:: በቀለኝነትን የፓለቲካ ስልት ያደረገው ከልጅነቱ ጀምሮ በመልኩ ይደርስበት በነበረው በደል እና ግፍ እንደሆነ ሲያስረዱ "መንግሥቱ ግን በአካል ያዩት የቀለም መድልዎ ውስጥ ውስጡን መዝምሏቸዋል" (የቄሳር እንባ፣106) በማለት ሥነልቦናዊ ትንተና ያደርጋል:: የመንግሥቱ ኃ/ማርያም የበቀለኝነት እና የጭካኔ ውሳኔዎች ደራሲው እንደገለጸው ከሥነልቦና ጋር የተያየዘ መሆኑን ለማረጋገጥ እራሱን ችሎ ሌላ ጥናት የሚያስፈልገው ሃሳብ ነው:: ነገር ግን አንዱ የፋክሽን ባህርይ እውነታን ከምናብ ጋር በማዋሃድ በሚታወቁ ታሪኮች ወይም ግለሰቦች ላይ በፊት ከነበረው በተለየ መልኩ አዲስ እይታን መፍጠር ነው:: *የቄሳር እንባ* ስለ ኮሎኔል መንግሥቱ ኃ/ማርያም አዲስ እይታን ፈጥሯል ማለት ይቻላል:: መንግሥቱ ኃ/ማርያም ከሀገር ፍቅር ይልቅ የሥልጣን ጥም እንዳለባቸው፣ የሳቸውን ስርዓት ብቻ ሳይሆን የሳቸውን ሃሳብ የሚቃወም ሰው እንዲገደል እንደሚያደርጉ፣ ሰዎች ወይም የስራ ባልደረቦቻቸውን ሲያስገድሉ "የእጃቸውን ነው ያገኙት" እንደሚሉ እና ስልጣናቸውን ለማራዘም የማያደርጉት ነገር እንደሌለ

ተገልጿል። ይሄ እና የሚያደርጓቸው ነገሮች ከሥነልቦና ጋር በተያያዘ ችግር ምክንያት መሆኑ ስለ መንግሥቱ ኃ/ማርያም አዲስ እይታ ነው።

## 3.2.1. የፈጠራና የእውነታ ውህደት በ *ቆሳር እንባ* እና በ *የሱፍ አበባ*

በዚህ ንዑስ ርዕስ ክፍል የሚቀርበው ትንተና ከላይ ከቀረበው ትንተና የሚለየው ለማንጸርያ በምጠቀማቸው ሃሳቦች ብቻ ነው። ትንተናዬን ከ*የሱፍ አበባ* ማሳያነት ስጀምር *የሱፍ አበባ* ላይ በዋና ገጸባህርይ ሰመረ በኩል አብዛኛው የኢሕአፓ እውነታ ከፈጠራ ጋር ተዋህዶ ቀርቧል። አቢዮት አደባባይ አለም አቀፍ የላብ አደሮች በዓል ኢሕአፓ ደርግን እና መኢሶንን የሚያወግዙ የተለያዩ መፈክሮችን እና መዝሙሮችን ያሰማበት ነበር። በዚህም ምክንያት ከፖሊስ ጋር ግጭት ውስጥ ገብቶ ብዙ ወጣቶች የተገደሉበት፣ለእስር እና ለድብደባ የተዳረጉበት መሆኑ እሙን ነው። ይህንንም *የሱፍ አበባ* ላይ እንደሚከተለው ተገልጾ እናያለን

> "ስለዚህ የጋራዡ ሠራተኞች በሙሉ የሄዱት ለዚህ ተልእኮ መሆኑ ገባኝ። ከፖሊስ ጋር ግጭት እንደማይቀር ገመትኩ። ልክ ይሄንን ሳስብ መንፈሴ ድንገት እርብሽ አለ.....ቤ_ቲ_የስ? ቅፍፍ ብሎኝ ከወንበሬ ተሽቀንጥሬ ተነሳሁ" (የሱፍ አበባ፣165)

ዋናው ገጸባህርይ ሰመረ የላብ አደሮች በዓል ላይ ሊፈጠር በሚችለውን ክስተት ለፍቅረኛው የተጨነቀ አስመስሎ እውነታውን ይነግረናል። የላብ አደሮች በዓል ላይ የተለያዩ መፈክሮችን የኢሕአፓ አባላት ይዘው በመገኘታቸው ከደርግ ወታደር ጋር ግጭት ውስጥ ገብተዋል። ይሄንንም በቢታኒያ እና በሰመረ በኩል ማየት ይቻላል። በፈጠራው ከሰመረ አኳኋን እና ጭንቀት በቦታው ላይ ሊፈጠር ስለሚችለው ነገር እንድናስብ ያደርገናል። ሌላው የሰመረ ፍቅረኛ ቢታኒያ ሰልፉን ተካፍላ በፖሊስ ዱላ ተደብድባ ሲያያት እንደተበሳጨ እና ባለፈው በተካፈለው የማእከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ ላይ ዘርዑ ክህሸን ለከተማ ህዝብ አመጽ መዘጋጀት አለብን ያለውን ያስታውሳል። በዚህም ድርጅቱ ስህተት መስራቱን እና ዋና ገጸባህሪው ደጋግሞ የሚያነሳውን ኢሕአፓ ከተማ ለቆ ወደ አሲንባ መግባት አለበት የሚለው ሃሳቡ መነሻው ይሆናል። ዘርዑ ክህሸን በትክክል በገሀዱ አለም የነበረ የኢሕአፓ ሰው ሲሆን ደራሲው የኢሕአፓ ስህተት ብሎ ያመነበትን ወይም ሊሆን ይችላል ብሎ ያሰበውን ፈጠራ ጋር አዋህዶ እንደሚከተለው አቅርቧል።

> “በእኔና በኢሳያስ ዓይን ዘርዐ ክህሽንና ክፍሉ ታደሰም ከወንጀሉ አያመልጡም። ድርጅቱን ከተማ ውስጥ አግተው የደርግ ዓይንና ጥርስ እያየ የሚያድር ደካማ ተቋም አድርገውታል። ደርግ ኮስተር ሲል ሊፈጀን ነው ይላሉ። ፈገግ ሲል ደግሞ ኢሕአፓዎችን የፋራን ይመስላቸዋል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን እኔም ሆንኩ ኢሳያስ ሌላ ጥርጣሬ እየተሰማን ነው። “እነዚህ ሰዎች ምናልባት በየራሳቸው መንገድ አሲምባ መሄድ ሳያስፈልገን እዚሁ በአጭር መንገድ ለሥልጣን እንበቃለን ብለው በምሥጢር ድርድር ጀምረው ይሆን?” (የሱፍ አበባ፣175)

ታላላቅ ታሪካዊ ክስተቶችን ከፈጠራ ጋር እየተዋሐዱ አዲስ ተረክ ለመፍጠር ተሞክሯል። በ*የሱፍ አበባ* ላይ በገሀዱ አለም የነበረችውን ጋዜጠኛ የሸዋሉል መንግስቱን የሰመረ የድሮ ፍቅረኛው ብርክታዊት በተሰኘች ገጸባህርይ ተወክላ ቀርባ እናያለን። ይህን እውነታ ከፈጠራ ጋር በመዋሃድ የቀረበው እንደሚከተለው ነው

> “ብርክታዊት የትኛዋ ናት? ጋዜጠኛዋ ናት? ጌታቸው እንደቀልድ ሲጠይቀኝ “አዎ” አልኩት፣ እሷንማ እዚህ እናንተ ግቢ ያለችው ቆንጆዋ ልጅ አንድ የአሥራ አራት አመት ልጅ ይዛ ሄዳ ተራማጅ መጽሐፍት መደብር ውስጥ አስገድላት ተመለሰች አይደል እንዴ?! አፉን አመለጠው” (የሱፍ አበባ፣271)

ከላይ ከፍ ብሎ የቀረበው ሃሳብ የድሮ ፍቅረኛው ጋዜጠኛ ብርክታዊት በአሁኗ ፍቅረኛው ቢታኒያ በቤተ መጻሐፍት ውስጥ መገዳሏን ይገልጻል። ይሄ የፈጠራ ውጤት ነው። ስለዚህ የጋዜጠኛ የሸዋሉል በኢሕአፓዎች የመገደሏን እውነታ በቢታኒያ የመጽሐፍት መደብር ውስጥ እንደተገደለች ከፈጠራ ጋር ተዋህዶ ቀርቧል። ሌላው ኢሕአፓ ሲነሳ አብሮ የሚነሳው ብርሃነ መስቀል በፈጠራ ተለውሶ በ *የሱፍ አበባ* ላይ ጎልቶ ይታያል። የብርሀነ መስቀል ክስ የሚለውን እውነታ ላይ በፈጠራ የክሱን ምክንያት በማቅረብ የብርሃነ መስቀል ታሪክ ላይ ጥያቄ የሚፈጥረው እንደሚከተለው ነው።

> “ብርሃነመስቀልና ጌታቸው ማሩ አንድ ላይ ናቸው። **ደርግንና መኢሶንን ጨምሮ ከሌሎች ግራ ኃይሎች ጋር መተባበር ያስፈልገናል**’ የሚል አቋም

ይዘዋል፡፡ ሌሎቹ በተለይ ዘርዑ፣ተስፋዬና ክፍሉ ታደሰ 'ይህ የማይሆን ነው' ብለዋል (የሱፍ አበባ ፣ 86)፡፡

"አዎ ያንተን ሪፓርት በተለያየ መንገድ ተርጉመውት ሊጠቀሙበት ሞክረዋል፡፡ ብርሃነ መስቀል 'ሪፓርቱ የከተማ አመጽ ሥልት እንደማያዋጣ አሳይቶኛል' ብሎ ተረጎመው፡፡ መፍትሔው '**ከደርግ ጋር መተባበር ነው አለ**' (የሱፍአበባ ፣ 87)፡፡

ታሪካዊ ክስተቶችን እና ታሪክ ያላቸውን የታዋቂ ሰዎች ተረክን ከፈጠራ ጋር በማዋሃድ ተረካቸውን ከፈጠራ ጋር ደባልቆ በፊት የነበረውን ታሪክን ማጥፋት ወይም ጥያቄ ውስጥ ይከታል፡፡ ከዚህ አንጻር ከፍ ብሎ የቀረበውን ሃሳብ ስንመለከት ዋና ገጸባህሪው ሰመረ ጥናት እያዘጋጀ በሚያቀርብባቸው ጊዜያት ሁሉ የብርሃነ መስቀል ሃሳብ ከደርግ ጋር እንተባበር የሚል መሆኑን በመግለጽ ብርሃነ እንደተሳሳተ ይልቁንም የሃሳብ የበላይነትን አጊንቶ በማዕከላዊ ኮሚቴ ውስጥ የነበረውን ቦታ የማስመለስ ፍላጎት እንዳለው ይገልጻል፡፡ ይሄ ሃሳብ በፈጠራ የብርሃነመስቀልን የውስጥ ሃሳብ ጭምር እንድናይ ያደርጋል፡፡ እንዲሁም በ*ቄሳር እንባ* ላይም የመንግሥቱ ኃ/ማርያምን እና የደርግን ታሪክ ከነበረው እውነታ ጋር ፈጠራን ቀላቅሎ ወደ ሌላ አንድምታ ቀይሮታል፡፡ በላይነህ እና ሐምራዊት በተሰኙት ገጸባህርያት አማካይነት ፈጠራው ጎልቶ ይታያል፡፡ የሁለቱን የፍቅር ግንኙነት ለድርሰቱ ውበት ነው፡፡ ይህ ውበትን የፈጠረው ደግሞ እውነታ ከፈጠራ ጋር እየተዋሃደ በመቅረቡ ነው፡፡ ይህንን እንደሚከተለው እንመልከት፡፡

"እሱ ስሜቱ ሲበርድ ቀድሞ ትዝ የሚለው የደህንነታቸው ነገር ይሆናል፡፡ ስለ ድብቁ ፍቅራቸው የሰማ፣ የጠረጠረ ወይም ያማ ሰው ስለመኖሩ ይጠይቃታል፡፡ ኮሎኔል መንግሥቱ ጆሮ ሲደርስ ግን መቼም ታይቶት አያውቅም፡፡ የመኖሪያ ቤታቸው ጀርባ አንድ ቀን ጉዳያቸው ሆኖ አያውቅም፡፡ የመኖሪያ ቤታቸው ጀርባ አንድ ቀን ጉዳያቸው ሆኖ ታይቶት አያውቅም፡፡ በአካልም ዝር ብለው አያውቁም" (የቄሳር እንባ፣67)

ከፍ ብሎ የቀረበው ምንባብ የሐምራዊት እና የበላይነህ የፍቅር ግንኙነት ድብቅ እንደሆነ የሚያስረዳ ነው፡፡ ይህ የፍቅር ግንኙነታቸውን ድብቅ ሆኖ በፈጠራ የቀረበው በኋላ የበላይነህ ማስታወሻ ደብተር ሲጠፋ እና ይህ ድብቅ ፍቅራቸው ሲጋለጥ ሊደርስባቸው ከሚችለው አደጋ ሽሽት ስደት እንዲመርጡ እና የስደቱን ሂደት ለማሳየት እንዲያመች ነው፡፡ ምክንያቱም ፈጠራ

ክስተቶችን ከምክንያት እና ውጤት ጋር አስተሳስሮ ለማቅረብ አመቺ በመሆኑ ነው፡፡ የፈጠራ እና የእውነታ ቅይጥ የጋራ አስተሳሰብ የሆኑ ዘዴዎችን ውድቅ በማድረግ በእውነታ እና በልቦለድ ማካከል ያለውን ልዩነት ያደበዝዛል፡፡ *በ የሱፍ አበባ* ላይ የዳዕሮ ነጋሽ ግድያን ለማውገዝ ሰልፍ ስታስተባብር ቢታኒያ መያዟን እና እሷን ለማስፈታት ሸዋዬ እና ደጀኔ ባወጡት እቅድ መሰረት ሰመረ የመኢሶን ከፍተኛ ባለስልጣን በመሆን እነሱ ደግሞ አጅበውት ፖሊስ ጣቢያ ድረስ ገብተው ምንም እንከን ሳይገጥማቸው ቢታኒያን አስፈትተው ሲወጡ ከገጽ 358 - 363 ይገልጻል፡፡ ስለ ዳዕሮ ነጋሽ እንደሚከተለው ተግልጿል

> “ደግሞም መረጋጋት ነው ያለብኝ፤ የታሰረችው ቢታኒያ እያለች? በዚህ ላይ ጓድ ዳእሮ ነጋሽን አውቃታለሁ፡፡ የስምንት ልጆች እናት ነበረች፡፡ የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት የነቃችና በፖለቲካ ጉዳይ እንደ ንብ የምትለፋ ጽኑ ሴት እናት ነበረች፡፡ ፍርሀት ብሎ አልፈጠረባትም፡፡ ዳእሮ በግርማ ከበደ የተገደለችው ልትወልድ ጥቂት ቀናት የቀሯት የዘጠኝ ወር እርጉዝ ሆና እያለ ነው፡፡እንዲህ ዓይነት የወንጀል ወንጀል……የበደል በደል……የግፎች ሁሉ ግፍ ይሰራባታል ብዬ አልጠበኩም፡፡ ቢሆንም አንድ ቀን በቅጽ በቅጽ የሚጻፍ ታሪክ ትታ የሄደች የጀግና ጀግና ናት”(የሱፍ አበባ፣358)

ከፍ ብሎ የቀረበው ሃሳብ የፈጠራ ውጤት የሆነችው ቢታኒያ የተሰኘችው ገጸባህርይ የዳዕሮ ነጋሽ ግድያን ሰልፍ ስታስተባብር እንደታሰረች የሚያስረዳ ነው፡፡ ሰመረ ደግሞ ቢታኒያ በመታሰሩ ከልክ ያለፈ እንደተጨነቀ እና እራሱን ለማጠንከር የዳእሮ ነጋሽ ታሪክን ለውስጡ በመናገር እራሱን ሲያረጋጋ እናያለን፡፡ የቢታኒያ መታሰር እና የሰመረ ሁኔታ በፈጠራ ከዳእሮ ነጋሽ ግድያ እውነታ ጋር ተዋህዶ ነው ቀርቧል፡፡ የዳእሮ ነጋሽ ግድያ እውነታ በተለያዩ ዲስኮሮች ላይ የሚነሳ እና የሚታወቅ ነው፡፡ ይህንን ለማሳያነት *ያትውልድ መጽሐፍን* እንመልከት

> “ልትወልድ ቀናት የቀራትን የብርሃነ ሰላም ማተሚያ ቤት ባልደረባ የስምንት ልጆች እናት ዳሮ ነጋሽ እስከ እርግዝናዋ የገደለ አገዛዝ ደርግ ነው፡፡ የሠራተኛ ማህበር መሪው ጀግናው ማርቆስ ሀጎስና የኢሕአፓ አመራር አባል ቆራጡ ዶክተር ተስፋዬ ደበሳይ ደርግ ከመጋቢት 14 ቀን እስከ መጋቢት 17 ቀን 1969 ዓ.ም. ባደረገው የቤት ለቤት አሰሳ ከተሰዉ ብርቅዬ የሴቶች፣ የላብ አደሩና

> የኢትዮጵያ ሕዝብ አለኝታዎች ናቸው፡፡ ሁሌም ስንዘክራቸው የደርግ አገዛዝን ገዳይነትና አረመኔነት በማስረገጥ ነው (ያት፣ ቅጽ 3፣ ቁጥር 4፣ገጽ 5)

ታሪክን በሥነጽሑፍ ውስጥ የሚወክሉበትን መንገዶችን ደራሲዎች ብዙውን ጊዜ የድህረ ዘመናዊ ሥነጽሑፍ ቴክኒኮችን ፍራግመንቴሽን (fragmentation) እና intertextuality ይጠቀማሉ፡፡ በዚህ መሰረት ከላይ የቀረበው ምንባብ ላይ ደራሲው የዳዕሮ ነጋሽን ታሪክን *ያትውልድ* መጽሐፍ ላይም መመልከት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ሀብታሙ አለባቸው ለመጀመሪያ ጊዜ በ2015 ዓ.ም ፋና ኤፍ ኤም ላይ ቀርቦ ባደረገው ቃለ ምልልስ ላይ *የየሱፍ አበባ* ልቦለድን ለመጻፍ *ያ ትውልድ* እንዳነሳሳው ገልጿል፡፡ ስለዚህ ከፍ ብሎ የቀረበውን የመጽሐፉ ቅንጭብ መሰረት በማድረግ ሀብታሙ የፈጠራ እና የእውነታን ውህደትን ለማሳየት ከድህረዘመናዊ ሥነጽሑፍ ቴክኒኮች መካከል በይነአሀድን ተጠቅሟል ማለት እንችላለን፡፡ በተጨማሪም በ*ቁሳር እንባ* ላይ በላይነህ በተሰኘው ገፀባህርይ እንደ ደራሲ በግልጽ የድርሰቱ መጨረሻውን እና የድርሰቱን ርዕስ  እንደሚከተለው ይነግረናል፡፡

> “ቁሳር ማስለቀስንም ማልቀስንም ያውቅበታል፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ወደ ውጪ የሚሄዱ ልጆቹን እየሸኘ ለማልቀስ አልታደለም፡፡ በብሔራዊ ውትድርናና በቀይ ሽብር ላለቁት ልጆቹ ነው ያለቀሰው፡፡ ግን ግን ጥቁሩ ቁሳር  ለራሳቸው የሚያለቅሱት መቼ ይሆን? ጊዜውን መገመት ከባድ ነው፡፡ የማይቀር መሆኑን ለመተንበይ ግን የ6ዓመት ልጅ መሆን በቂ ነው” (የቁሳር እንባ፣188)፡፡

ከፍ ብሎ የቀረበው ሃሳብ 1) የድርሰቱን ርዕስ በድርሰቱ ውስጥ ይነግረናል፡፡ 2) የድርሰቱን መጨረሻ በድርሰቱ ይነግረናል፡፡ ቁሳር እያለ የሚገልጸው መንግሥቱ ኃ/ማርያምን ነው፡፡ መቼ ይሆን ቁሳር ለራሳቸው የሚያለቅሱት? ብሎ እራሱ ጠይቆ እራሱ ይመልሳል፡፡ በወቅቱ ለዘመቻ እየተባለ ብዙ ወጣቶች ከቤተሰቦቻቸው ተለይተው በግዳጅ ሲሄዱ እና በቀይ ሽብር ብዙ ወጣት ሲያልቅ እናቶች ማልቀሳቸው የገሀዱ እውነታ ሲሆን ይህን እውነታ ከፈጠራ ጋር አዋህዶ በመተንበይ የድርሰቱ ማብቂያ ላይ ለሚያቀርበው ምናባዊ ውጤት መነሻ ሆኗል፡፡ የድርሰቱ ማብቂያም የሚሆነው ወያኔ ወደ አዲስ አበባ እየተጠጋ ሲሄድ መሸነፋቸው ሲገባቸው ቁጭ ብለው ሲያነቡ እንደሆነ እናያለን

“ወደ ጀርባቸው ዞር አሉ። ትንሽ ራቅ ብሎ አንድ ድንጋይ ታያቸው። ሄደው ቁጭ አሉበት። እንባቸውን መቆጣጠር አልቻሉም። ግንፍል ብሎ መጣባቸው። ጉንጫቸውን እያቋረጠ ወርዶ ሱሪያቸው ላይ ተንጠባጠበ። አብረዋቸው የነበሩት ባለስልጣናት ግን አላለቀሱም። የፈረሰው ቤት የእሳቸው ብቻ ነበር” (የቁሳር እንባ፣374)

ይሄ ደግሞ ደራሲው ፣ ልክ እንደ ፈጣሪ ሳይታይ የድርሰቱን መጀመሪያ እና መጨረሻው በማወጅ የድርሰቱ ዓለም ውስጥ መግባት ብቻ ሳይሆን ድርሰቱ ፈጣሪ እንዳለው እና ድርሰቱ እውነታ ከፈጠራ ጋር ተዋህዶ እንደቀረበ ይገልጻል። በተመሳሳይ መልኩ *የሱፍ አበባ* ላይ ሰመረ የድርሰቱን መጨረሻ እና የድርሰቱን ርዕስ “የሱ_ፍ_አበ_ባ? አልኩ ለራሴ ሳይታወቀኝ በውስጤ አንዳች አደጋ ጋር እያያዝኳት። የሱፍ አበባ?!” (የሱፋአበባ፣144) በማለት የመጽሐፉን ርዕስ ይነግረናል። በሌሎች ቦታዎች ላይም የሱፍ አበባን እና ኢሕአፓን እንድ ላይ እያያዘ ለቋሚ ኮሚቴ በሚያዘጋጀው ጹሑፎች ላይ ሲያቀርብ እናያለን

“ታዲያ ኢሕአፓ ከየት አመጣው? ጭንቅ አለኝ። የሥልቱን ደካማነት በ”ሱፍ አበባዊነት”ጽሑፌ ላይ እንዴት እንደምተነትነው ማብሰልሰል  መርገፍ ስጀምር ኢሳያስ ከት ብሎ ስቆ ትኩረቴን ቀለበሰው” (የሱፋአበባ፣228)።

ከፍ ብሎ የቀረበው ሃሳብ ይህ የድርሰቱን ልቦለድነት ይጠቁመናል። ሰመረ ለማዕከላዊ ኮሚቴ ጥናት እያለ የሚጽፋቸው ነገሮች በሙሉ እኛ የምናነባቸው ስለሆኑ በድርሰቱ ውስጥ ያሉ ድርሰቶች ናቸው። እንዲሁም በላይነህ የተሰኘው ገጸባህርይ ወደ ሞስኮ እየጻፈ የሚልካቸውን ጽሑፎች እና ለመንግሥቱ ኃ/ማርያም ጥናት አዘጋጅቶ በሪፓርት የሚያቀርብላቸው ጽሑፍች የጽሑፍ ውስጥ ጽሑፎች ናቸው። በላይነህ የተሰኘው ገጸባህርይ ደራሲው ነው ማለት ይቻላል። በድርሰቱ ውስጥ በላይነህ በማስታወሻ ደብተሩ ላይ የሚጽፋቸው ነገሮች በሙሉ የድርሰቱ ድርሰት ሲሆኑ እውነታ ከፈጠራ ተዋህዶ የቀረበባቸው ናቸው። በላይነህ በማስታወሻ ደብተሩ ላይ ሲጽፍና የጻፋቸውን ሃሳቦች በድርሰቱ ውስጥ ከአንባቢያን ጋር እንደሚያነብ ከዚህ በታች እንመልከት

“በላይነህ ጣሪያ ጣሪያውን ተመለከተ። ብድግ ብሎ ወደ መስታወቱ ሄደ። የፊቱን ገጽ አስተዋለ። ጠይምነቱ የጨመረ መሰለው። የተቆላለፈ ለስላሳ ጸጉሩን በጣቶቹ በጠር በጠር አደረገ። ተመልሶ ወደ ወንበሩ መጥቶ

ጽሑፉን ቀጠለ......፡፡**ጥር 26 ቀን በ1969 በደርግ ውስጥ የነበሩት ነቢያት ፍጻሜ ሆነ፡፡ ሰባቱ አባላት 'አብዮቱና ዲሞክራሲ' እዚሁ ደርግ ውስጥ መጀመር አለበት ብለው ተነሱ፡፡ ሞት ምላሻቸው ሆነ**...........”( የቄሳር እንባ፣92)

“የበላይነህ ሃሳብ ወደ ጀኔራል ታሪኩ አሟሟት ተመለሰ፡፡ የቀረበባቸውን ክስና የተፈጠረውን ውዝግብ በደንብ ተከታትሎታል፡፡ ከጀርባው እንደተጋደመ በኮድ ቁልፍ የሚዘጋ ማስታወሻ ደብተሩን ከኮሞዲኖው ላይ አነሳው፡፡ ትላንት ስለ እሳቸው የጻፈውን ትዝብት መልሶ አነበበው.......፡፡ ጀኔራል ታሪኩን የገደሉት በገዛ ማመልከቻው ላይ ነው.....” (የቄሳር እንባ፣233)

ከፍ ብሎ የቀረበውን ምንባብ በሶስት መንገድ ማየት ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው በላይነህ የተሰኘው ገጸባህርይ ደራሲው መሆኑን እና በመጀመሪያው ምንባብ ላይ አጽንዖት የተሰጠው ጽሑፍ እውነታ ሲሆን ደራሲው ይህንን እውነታ ያቀረበው ደግሞ በበላይነህ ጽሑፍ ነው፡፡ ይህም ማለት በጽሑፍ ውስጥ ጽሑፍ ከፈጠራ ጋር አዋህዶ ነው፡፡

በደርግ ታሪክ እና በመንግሥቱ ኃ/ማርያም ታሪክ አንባቢ እንዳይሰላች በላይነህ እና ሐምራዊት የተሰኙ ገጸባህርያትን አንዳንድ ንግግራቸውን እና ተግባራቸውን በፈጠራ መልክ ቀርቧል፡፡ በላይነህ ደብተሩ በመጥፋቱ ምክንያት ከሐምራዊት ጋር ስደትን መርጠው ሱዳን እስኪደርሱ ድረስ ያለውን ሂደት የተገለጸበት መንገድ የአንባቢያንን ትኩረት ሰቅዞ የሚይዝ በመሆኑ አንባቢያን አንድን የልብወለድ ሥራ እያነበቡ መሆናቸውን ያውቃሉ ወይም ይረዳሉ፡፡

“ሻንጣዎቻቸውን አንግበው ሲያወጡ ድቅድቅ ጨለማ ዋጣቸው፡፡ ፍጹም ጭልልታ፡፡ ተጫን የሐምራዊትን እጅ ይዞ እየመራ ወሰዳቸው፡፡ ደንቀፍቀፍ እያሉ ተከተሉት፡፡ የሚያልፉት መሬት ሁሉ የሆነ አንድ ዓይነት እንቅፋት አስቀምጦ ነው የሚጠብቃቸው፡፡ ጠጠር......ድንጋይ......አመድ.....ቁጥቋጦ፡፡ ከሃያ ደቂቃ ባነሰ ጊዜ ክምር ድንጋይ ከተማን ለቀው ወጡ፡፡ ሹክሹክታ.......ወሬ.....ጨዋታ ብሎ ነገር የለም፡፡ ከወዲያ ወዲ የሚያላጋ ረጅም ቁልቁለት ወረዱ” (የቄሳር እንባ፣346)

### 3.2.2. የማህበራዊ እውነታ በቁሳር እንባ እና በየሱፍ አበባ

በዚህ ንዑስ ርዕስ ክፍል የሚቀርበው ትንተና “social” እውነታዊነት በሥነጽሑፍ የሚነሱ ርዕሰ ጉዳዮችን ፣ ማህበራዊ ጠቀሜታ ያላቸው የዕለት ተዕለት የሰው ልጅ የሥራ ሁኔታዎችን የሚገልጽ ነው። እንዲሁም እንደ መደብ ግጭት፣ ዘር እና የፆታ ልዩነት፣ ኢንደስትሪላይዜሽን እና የካፒታሊዝም ተፅእኖ በህብረተሰብ እና በግለሰቦች ላይ ባሉ ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር ሃሳቦችን ለማሳየት ከልቦለዶቹ ተቀንጭቦ ቀርቧል። በመጀመሪያም የመደብ ልዩነትን ለማሳየት *የቁሳር እንባ* ላይ የቀረበውን ሃሳብ እንመልከት።

> “*መንግሥቱ እዛው አከባቢ ነው ያረፈው። ከልጆች ጋር ኳስ መጫወት ጀመረ። ከመካከላቸው አንደኛው ልጅ የጋዝ ቸርቻሪው ልጅ ነው። መንግሥቱ ሁለት ግብ በደቂቃ ልዩነት አስገባባቸው ይኸው ልጅ ተናደደ።* ***ማን እሚባል ባላባት ነው ይሄን ባሪያ ገዝቶ ያመጣብን?*** *አለው በጩኸት። የቡድኑ ሳቅ ፈነዳ። መንግሥቱ ቦግ ብሎበት ልጁን ሄዶ አነቀው። ጥርሱን ሊያራግፈው ሲል አባቱ እየሮጠ ሄደው መንግሥቱን ያዙት። ‘ልትገለው ነው እንዴ* ***ልጄ፣እንዳንተኮ ድርብ አጥንት የለውም፣ የጨዋ ልጅ ነው....***’ *ብለው አፈጠጡበት። ውስጡ እንደ ድንች ብስል ብሎ ተቀቀለ። ሱቅ ተልኮ ሲሄድ ደግሞ ሌላ ነገር ገጠመው፣* ***‘መች የመጣሽ መሸጦ ነሽ?’*** *አሉት ባልና ሚስት በንቀት እየተመለከቱት*”( የቁሳር እንባ፣104)።

ከፍ ብሎ የቀረበው ምንባብ ላይ መንግሥቱ በልጅነቱ የታችኛው መደብ ክፍል ልጅ በመሆኑ እና በመልኩ ይደርስበት የነበረውን ነገር ያሳየናል። ደራሲው ይህንን ሁኔታ በመንግሥቱ ያሳየን እንጂ በማህበረሰባችን ውስጥ መልኩ ጠቆር ያለ እና መልከ ጥፉ የሆነ ሰው ብዙ ስነልቦናዊም ማህበራዊም ጫና ይደርስበታል። የታችኛው መደብ ክፍል እንደ ጠንካራ ፣ ሁሉን ነገር እንደሚችል እና ምንም ቢሆን እንደማይጎዳ (ቆዳው ጠንካራ ) ይታሰባል። ይህ አስተሳሰብ ደግሞ ያላቸው የላይኛው መደብ ክፍል ሲሆኑ ብዙውን ጊዜ የጉልበት ስራ አሊያም ሌላ ጠንካራ ስራ እነዚህን ክፍሎች ያሰሯቸዋል። ማህበራዊ እውነታ በሥነጽሑፋዊ ጽንሰ ሃሳብ ውስጥ ያለው ማህበራዊ እውነታ ማህበረሰቡን እና ሁኔታዎችን በእውነት ለመወከል የሚሞክር ዘውግ በመሆኑ ይህንን በገሃዱ ዓለም ያለውን ማህበራዊ እውነታ ከፈጠራ ጋር ተዋህዶ ቀርቧል ማለት ይቻላል። ይህ ከፍ ብሎ የቀረበው ሃሳብ በኛ ሀገር ያለ ችግር ብቻ እንዳልሆነ ለማሳየት መንግሥቱ ከሀገር በወጡበት ጊዜም እንደተከተላቸው ለማሳየት በዚህ መልኩ ቀርቦ እንመለከታለን።

> “ከተመረቀ ከሁለት ዓመታት በኋላ ወደ አሜሪካ ተላከ። አሜሪካ የጥቁሮች ገሃነም ሆና ጠበቀችው ጥቁሮች ያነሳሉ፣ ይጮሃሉ፣ መንገድ ዘግተው ይቀመጣሉ። ነጮች ባገኙት ቦታ ሁሉ ያሳድዷቸዋል፣ይወግሯቸዋል፣ይሰቅሏቸዋል። ጥቁሮች አልተበገሩም። የሲቪክ

> መብቶቻቸውን ለማስከበር መፋለም ቀጠሉ። በዚህ ጊዜ ጀግናዋ ጥቁር ሮዛ ፓርከር ተፈጠረች"(የቄሳር እንባ፣105)።

የማህበራዊ እውነታ ብዙውን ጊዜ በሥነጽሑፍ የማህበረሰቡን ጉድለቶች እና ውድቀቶችን በማንሳት ለማሄስ ያመቻል። እንዲሁም የድሆችን ትግል ፣የገዢዎች ሥርዓት እና በጾታ የሚደርሱ ጥቃቶችን ለማሳየት ያገለግላል። ይህንን *የቄሳር እንባ* ላይ ሐምራዊት የተሰኘችው ገጸባህርይን ወስደን እንመልከት።

> "ሐምራዊት መጀመሪያ የመደፈር፣የመዋረድ፣ዝቅ የመደረግ ስሜት ለአፍታ ነዲድ እሳት ጭሮ ቦግ አደረጋት። ቀጥሎ የወንድና የጊዜው አረመኔነት በንዴት አንገበገባት። ኃይለኛ የቁጣ እንፋሎት ጠበሳት። ይህ በተራው አንክስ እያለ ወደእሷ አቅጣጫ ከሚመጣ መልአከ ሞት ጋር አፋጠጣት"(የቄሳር እንባ፣70)

ከፍ ብሎ የቀረበው ምንባብ ሐምራዊት ከትምህርት ገበታዋ ተመልሳ ቤት ስትሄድ የደርግ ሹመኛ ሻምበል ይማም ሽማግሌ ልኮ ሊያገባት ሲል የተሰማት ስሜት ነው። እሱን ከማግባት ማንም እንደማያስጥላት በጉልበት እንደሚወስዳት እና ያለፍላጎቷ እንዳገባችው የቀረበ ሲሆን ይህ ደግሞ በማህበረሰቡ ውስጥ ያለ እውነታ ነው። ይህንን እውነታ ሻምበል ይማምን አስፈሪ እና ጨካኝ የደርግ ሹመኛ አድርጎ ገጸባህርይውን በመቅረጽ ሐምራዊት ያለፍላጎቷ ስታገባው ከማህበረሰቡ እውነታ ጋር ተዋህዶ ቀርቧል።

የማህበራዊ እውነታ የገዢዎችን ሥልጣን ለማሳየት ወይም ለመተቸት ያገለግላል። ይህንንም ሃሳብ ከ *ቄሳር እንባ* በተወሰደ ቅንጭብ እንመልከት።

> "መንግሥት የመፍጠር መብትንና ዕድልን በሞኖፓል ይዞታል በሕዝቡ ትከሻም ላይ እንደ ሬሳ ተጋድሞበታል። በጣም ከመግዘፉ የተነሳ ቦርጭና ቂጡ ከብዶት መላወስ ያቃተው መንግሥት ሆኗል። መሪዎቹ በተለያየ ዘዴ ሊያንቀሳቅሱት ይሞክራሉ። ወይ ፍንክች የአባ ቢላዋ ልጅ! ሆኖባቸው ቁጭ ይላል። ኀርቫቼቭ ይህንን ክስተት በአንድ ቃል አጠቃለሉት። "ልግመት ሶሻሊዝም....!" (የቄሳር እንባ፣48)

ከፍ ብሎ የቀረበው ምንባብ ላይ በላይነህ የተሰኘው ገጸባህርይ ስለ መንግሥቱ ሲያስብ በራሺያ ስብሰባ ላይ የተነሳውን ሃሳብ እና ለወደፊቱ ለሚጽፋቸው ነገሮች መነሻ የሚሆነውን ሃሳብ ስያገኝ እንመለከታለን። ይህን "ልግመት ሶሻሊዝም" የሚለውን ሃሳብ በመያዝ ስለ መንግሥቱ ሥርዓት እና አገዛዝ እየተቸ በዝርዝር ያቀርባል።

ማህበራዊ እውነታን በመጠቀም ከሥነጽሑፋዊ ቴክስቱ ውጭ ያለውን ዓለም በፈጠራ መርምሮ የማህበረሰቡን የዕለት ተዕለት ተግባር ማሳየት ይቻላል። ይህንን ሃሳብ *የሱፍ አበባ* ላይ ስንመለከት የኢሕአፓ ህቡዕ አባላት ለተለያዩ ተልዕኮ እንደሚሰማሩ እውነት ነው። ይህን እውነት በመውሰድ ለተልዕኮው በሄዱበት ወቅት በሚያገኟቸውን አንዲት እናት ከሥነጽሑፋዊ ቴክስቱ ውጭ ያለውን ዓለም በፈጠራዎቹ መርምሮ የገጠሩን ህይወት፣የገበሬውን ደግነት፣ ለጋስነት እና ሰው ወዳድነት ያሳያል። በተጨማሪም የገጠሩን የማህበረሰብ ክፍል ማህበራዊ ህይወትን እንዴት እንዳሳየን እንመልከት።

> "በሉማ፣ታጠቡ....በ'ኛ ባህል ምግብ ቀርቦ መገልገል ነውር ነው። ታጠቢ፣ የ'ኔ ልጅ....በይ! የቁጣ ያህል ተጫኑን። እንዲህ ዓይነቱን የበዛ ልግስናና ደግነት አዲስ የሚሆነው ምናልባት ለቢታኒያ ነው። ይሉኝታና የውለታ ብዛት አሳቀቃት። እኔ እና ጀማል ገጠሩን ስለምናውቀው አልተሳቀቅንም። እንጀራው በትልቅ ዝርግ ሰሃን ከፊት ለፊታችን በአነስተኛ ጠረጴዛ ላይ ቀረበ። የሞሰቦ ክዳን ሲነሳ ንድፍ ጥጥ የመሰለ ነጭ ጤፍ እንጀራ። በወይዘሮ ማስተዋል ቤት የምንበላው እንጀራ የንጣት ጥግ ይመስለኝ ነበር። ይሄ ይበልጣል" (የሱፍ አበባ፣339)።

# ምዕራፍ አራት

## ማጠቃለያ

ይህ ጥናት በ*ቁሳር እንባ* እና በ*የሱፍ አበባ* የፈጠራና የእውነታ ውህደትን ተንትኖ ለማሳየት ሙከራ የተደረገበት ነው። ከላይ በትንተናው መረዳት እንደተቻለው በ*የሱፍ አበባ* እና በ*ቁሳር እንባ* ልቦለዶች ላይ ፈጠራና እውነታ ተዋህደው ቀርበዋል። ትንተናውን ለማጠናከር ከሀዲስ ታሪካዊ ሂስ ንድፈ ሃሳብ ጋር በማዛመድ የፈጠራና የእውነታ ውህደት ተተንትኗል። *የቁሳር እንባ* ላይ ዋና ገጸባህርይ ሁነው የተሳሉት መንግሥቱ ኃ/ማርያም የህይወት ታሪካቸው ከደርግ ታሪክ ጋር ተያይዞ የቀረበ ነው። ሆኖም በመንግሥቱ ኃ/ማርያም ላይ በገሀዱ አለም ከሚታውቁ ክስተቶች ጋር ፈጠራን በመቀላቀል አዲስ እይታን የፈጠረ ልቦለድ ነው። በተጨማሪም ስለመንግሥቱ ኃ/ማርያም የማይታወቁ ታሪኮችን ለመዳሰስ የተሞከረበት እና ጨቃኝ ስልጣን ወዳድ ተደርገው የቀረቡበት ልቦለድ ነው። የፈጠራ እና የእውነት ውህደት በልቦለድ እና በእውነታ መካከል ያለውን ድንበር ያፈርሳል። እንዲሁም በላይነህ እና ሐምራዊት በተሰኙ የፈጠራ ገጸባህርያት አማካይነት የደርግ ስርዓትን እና ዘመኑን ማየት ተችሏል። በተለይ በላይነህ የተሰኘው ገጸባህርይ የሚጽፋቸው የሚያዘጋጃቸው ጥናቶች እውነታ ከፈጠራ የተዋሀደባቸው መሆናቸውን ከላይ በትንተናው ክፍል መረዳት ተችሏል። በየሱፍ አበባ ላይ ደግሞ የሰመረ እና የቢታኒያ የፍቅር ታሪክ የምናባዊነት ውጤት ሲሆን ከኢሕአፓ የታሪክ እውነታ ጋር ተዋህዶ መቅረቡን መመልከት ተችሏል።

ሀብታሙ አለባቸው ታላላቅ ታሪካዊ ክስተቶችን ከምናባዊ ውጤት ጋር እያዋሃደ አንባቢያን ሳይሰላቹ እውነታና ፈጠራ በማይለይበት መልኩ አስተማስሎ እንዳቀረበው በትንተናው መረዳት ተችሏል። በገሀዱ ዓለም ያሉ እና የነበሩ ሰዎችን በገፀባህርይነት በመጠቀሙ ሁለቱ በቀላሉ እንዳይለዩ አግዞታል። ኢሕአፓ ‹ሲነሳ አብሮ የሚነሳው ብርሃነ መስቀል በምናባዊ ፈጠራ ተለውሶ በ*የሱፍ አበባ* ላይ ጎልቶ ታይቷል። አንድን እውነታ ከፈጠራ ጋር ቀላቅሎ በማቅረብ የድርሰቱ መጨረሻ ክፍል ላይ ፈጠራው ጎልቶ እንዲወጣ መጀመሪያ ላይ ተዋህዶ የቀረበው ፈጠራ እውነት ለማስመሰል ሲቀርብ በሁለቱም ልቦለዶች ላይ መመልከት ተችሏል። ታሪክም ሆነ ልቦለድ ንግግር በመሆናቸው እውነታን ከንግግር የመፈለግ ሂደት ነው።

በልቦልዶቹ ውስጥ በፈጠራቸው ገፀባህርይነት አማካይነት እውነታውን ከፈጠራ ጋር አዋህዶ በሚያዘጋጁት ጥናታዊ ጽሑፍ ውስጥ ይገልጻል፡፡ በአጠቃላይ ምናባዊነት ታሪክና ልቦለድን በማዋሀድ በኩል ትልቅ ሚና እንዳለው ከትንተናው መረዳት ይችላል፡፡ እንዲሁም *የሱፍ አበባ* እና *የቁሳር እንባ* የፈጠራና የእውነታ ውህደት ጎልቶ እንደሚታይባቸው በትንተናው ተግልጿል፡፡

# ዋቢዎች


ሀብታሙ አለባቸው:: (2008):: *የሱፍ አበባ*:: አዲስ አበባ፣ ፋር ኢስት ትሬዲንግ::

:: (2013):: *የቁሳር እንባ* :: አዲስ አበባ፣ አሳብ አሳታሚ::

ታደለች ኃ/ሚካኤል :: (2012):: *ዳኛው ማነው*:: አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያን ግራፊክና ህትመት::

ትዕግስት ፍሰሀ:: (2013) :: *የፈጠራና የእውነታ ውህደት ከደንቢያ ጎንደር እስከ ዋሽግተንዲሲ*:: ለኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች) እና ሥነጽሑፍ ለመጀመሪያ ድገሪ ማሟያነተ የቀረበ ጥናት:: (ያልታተመ):: ባህርዳር፣ባህርዳር ዩኒቨርስቲ::

ዮሐንስ አድማሱ:: (1961):: *የሥነጽሑፍ ጉዞ፡ መነን መጽሔት* :: ከገጽ 1-4::

ነፃነት ማስረሻ:: (2010) :: *የድህረ- ዘመናዊነት የስነ- ጽሁፍ መገለጫዎች በ "የስንብት ቀለማት*:: ለአማርኛ ሥነጽሑፍ የኤም.ኤ.ዲግሪ መርሐ ግብር ማሟያ የቀረበ ጥናት(ያልታተመ):: ባህርዳር፣ ባህርዳር ዩኒቨርስቲ::

አስማማው ኃይሉ:: (2003 ):: *ኢሕአሠ* :: አዲስ አበባ::

የልዩ አቃቤ ጽ/ቤት:: (2000):: *ደም ያዘለው ዶሴ*:: አዲስ አበባ::

አንተነህ አወቀ:: (2016):: *ዳግም ንባብ በአልወለድም*:: Ethiopian Journal of Langage, Culture and Communication, 1 (1),53-69.

አንዳርጋቸው ፅጌ:: (2011):: *ትውልድ አይደናገር እኛም እንናገር* (ቅፅ 1):: አዲስ አበባ፣ ነጻነት አሳታሚ ድርጅት::

ገነት አያሌው:: (1994 ):: *የሌተና ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ትዝታዎች*:: አዲስ አበባ፣ ሜጋ አሳታሚ::

ጸደይ ወንድሙ ። (2007) ። *ብሌን፡ የኢትዮጵያ ደራስያን ማህበር የሥነጽሑፍ መጽሔት፡፡* ቅጽ 1፡፡ ቁጥር 2፡፡ ከገጽ 3-21፡፡ አዲስ አበባ፤ ኤክሊፕስ አሳታሚ፡፡

Abdulazim, N, E. (2016). *POSTMODERNISM THEORY.* https://www.researchgate.net/publication/303812364.

Adjei, A. (2018). *Historical Imperialism in Science: A Theory of Relationship b/n History and ther disciplines*. *International Journal of history and cultura studies*, 4 (1),10-46.

Agron, Y, G. (2021). *Fact and Fiction in Autoconfession: A Theoretical Confrontation.* Journal of Educational and Social Research, 11 (6). https://creativecommons.org/licenses/by-nc/4.0/.

Dobie, A.B. (2012). *Theory into practice: An Introduction to Literary Criticism* (3rd ed). USA, WadSworth.175- 200.

Dave, A. (2019). *Social Realism in English Literature*.The Refereed & pree Review International Journal,3 (39),11-14.

David, Carter. (2006).*Literary Theory* (2nd ed).Pocket Essentials. 119- 123.

David, Lewis. (1978). Truth in Fiction: The Story Continued. *Australasian Journal of Philosophy*,71(1), 24-35.

Dirk, V, R. (2020, April). Historiographic Metafiction as a Postcolonial Narrative Strateg in Michael Ondaatje's Warlight (publication number 300315) MA Thesis English Language and Culture School of Humanities, University

of Eastern Finland.

Doug, M and Jack, C. (2017). Bearing Witness: Essay in non-our of Brij V. Lal. Australian National University Press.

Epner, L. (n.d). *socialist Realism: Theory Versus Reality.* 113-115.

Furay and Salevouris. (1988).The Methods and Skills of History: A Practical Guide. ISBN

Greenblatt, S. (2000). *Practicing New Historicism*. The University of Chicago.

Culler, J. (2000). *The Literary Theory*. New York: Routledge.

Habib, M.A.R. (2005). *A History of Literary Criticism: From Plato to the Present*. Oxfored: Blackwell Publishing.

Hayden, White. (1978). The Historical Text as Literary Artifact. Johns Hopkins.University Press. 81- 100.

……………………… . (2014). *The Practical Past*. North Western University Press.

Herman, Paul. (2011) . *Hayden White.* London polity press .

Hossein, Sabouri. (2018). Postmodernism, Philosophy, and Literature. Journal of Philosophical Investigations,12 (24).

Linda, Hutcheon. (1988). *Poetices of Postmodernism*. New York and London: Routledge.

Lovecraft, H.P.,Supernatural Horror in Literature, book, Penguin Books, 1927

Currie.M.(2013). *Metafiction* (2nd ed). New York and London: Routledge.

Mary, Klages. (2006). *Literary Theory: A Guide for the Perplexed*.Continuum

International Publishing group, New York.

Michale, Brian. (1987). Postmodern Fiction. New York and London: Routledge.

Misrak Tenna Adafre. (2019, Dec). Postmodernism in Selected Ethiopian Diasporic Novels in English. A Thesis in the Department of Foreign Languages and Literature for the Degree of Doctor of Philosophy in Literature.

Patricia, Waugh. (1984). Metafiction: The Theory and Practice of Self-Conscious Fiction. New York and London: Routledge.

Paul, Coates. (1983). *The Realist Fantasy Fiction and Reality since Clarissa*. The Macmillan Press.

Sheeba. (2018). *Postmodern literature: Practices and Theory*. https://www.researchgate.net/publication/328449584.

Stacie, F. (n.d). Imagining Fact and Fiction.

Taghizadeh, A. (2014). A Theory of Literary Realism. Theory and practice in Language studies,4(8).1628-1635.

Tyson, L. (2006). *Critical Theory Today: A User-Friendly Guide* (2nd ed). New York and London: Routledge.

Williams, M. (n.d). American Literary Realism and Mark Twain's Early Fiction.53-72.

Xiaotang, Lyu. (2021).An Introduction to New Historicism. Advances in Social Science, Education and Humanities Research, volume 543.

https://tesfabelaynehh.blogspot.com.